


CamScanner

# የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ

በዶ/ር ፈቀደ አግዋር

2013 ዓ.ም

CamScanner

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
© All Rights Reserved

በዶ/ር ፈቀደ አግዋር

# የልብ ጠጋኝ ማስታወሻ

1ኛ ዕትም ነሐሴ 2013 ዓ.ም
2ኛ ዕትም መስከረም 2014 ዓ.ም
3ኛ ዕትም ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ሞባይል፡- 0911 86 02 16
ኢ-ሜይል ፡ kefedb@gmail.com

Telegram- Fekede Agwar
Instagram- Fekede Agwar

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

የሽፋን ዲዛይን - ሳሙኤል ሀይሉ ( ሠዓሊ )
የውስጥ ገጽ ዲዛይን - መሰረት አደነው

## ማውጫ

1. ሀፍረት እና ስኬት ______ 12
2. አልፋ እና ኦሜጋዬ ______ 25
3. ዓለምን ያስደመመው የልብ ውስጥ እጢ ______ 41
4. ልብ እየመታ ልብ ሲጠገን ______ 51
5. የሮዶተርስ ጋሌጣኖ ______ 60
6. ታሪክ በአጋጣሚ ______ 68
7. የመንታ ዘለላ ______ 76
8. ጀግናዬ ______ 84

9. የራስን ቤተሰብ ማከም ........ 109
10. ደም መሸናትን ያስቆመው የልብ ቀዶ ጥገና ........ 119
11. የሰማያዊ ህጻናት ህክምና በኢትዮጵያ ........ 124
12. ላያስችል አይሰጥ ........ 135
13. አትረፍ ያለው ........ 144
14. ውበት ሲፈነዳ ........ 157
15. ቡናና ጊዮርጊስ በልብ ህክምና ጣቢያ ........ 167
16. ምቱን ደገስኩለት ........ 173
17. ሳጣ ሰገበት ........ 180



# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ዛሬ ላይ በመድረሴ ጠብቆ ላቆየኝ እና ከነበሙኝ ከፋም ሆነ አስቸጋሪ ጊዜያት አሳልፎ ለዚህ ቀን ላበቃኝ አምላክ ምስጋና ይግባው። በጥረቴ ሁሉ የፈጣሪ በረከት ባይኖረው ለዛሬው በረከትም ባልበቃሁና የነጠሙኝን ፈተናዎች ባላለፍኩኝ ነበር። በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ እና ደረጃ ውስጥም ሆናችሁ ለረጅም የኑሮዬ መስመር ከጎኔ የቆማችሁት ቤተሰቦቼ፤ አቅማችሁ በፈቀደ አስፈጋችሁ ለዚህ አብቅታችሁኛልና ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሳችሁ።

ለትምህርቴ እና ለስራዬ ስኬት ስትሉ የእናንተን ምቾት ሰውታችሁ መንገዴ እንዳይሰናከል፤ቢቀጥልም ሲደክመኝ እያበረታችሁ አቅም ሰጣ አቅም የሆናችሁኝ ባለቤቴ እና ልጆቼ በጣም እንደምወዳችሁ እወቁልኝ። በተለይ ባለቤቴ መለይ መሰፍን ቅዳሜ የለ እሁድ፤

ምንም የለ ቀን፤ የአዘቦት የለ የበዓል ቀን ሳይለይ ከቤት በምርቅበት የዘወትር ህይወቴ እንደ እናትም እንደ አባትም ሆነሽ ቤቴን መርተሻል፤ እየመራሽም ነው። እንዳንቺ አይነት የሚረዳኝ በለቤት በማግኘቴ የሚሰማኝ ደስታ ወደር የለውም።

አንድ ልባችሁን አምናችሁ የሰጣችሁኝ ታካሚዎቼ ለእናንተ ያለኝ ቦታ ልዩ መሆኑን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ። ካለንበት የህክምና ደረጃ አንጻር የልብ ቀዶ ጥገና ውስብስብነት እና ህክምናው የሚሰጠው ከውጭ በሚመጡ በጎ አድራጊዎች ለረጅም ዘመን ከመቆየቱ አንጻር የእናንተን እምነት ማግኘት ከባዱ ፈተና ነበር። በሀገራችን የመጀመሪያውም ሆነ ትልልቅ የልብ ቀዶ ጥገናዎችን በሀገራችሁ ምድር እና በሀገር ቤት ሙሉ እውቀት እንዲሰራ የፈቀዳችሁ ጀግኖቻችን ናችሁ። በተገኘውም አመርቂ ውጤት እንኳን ደስ አላችሁ። ፈጣሪ ቀሪ ዘመናችሁን ይባርክ ዘንድ እመኛለሁ። በእናንተ ምክንያት በተለኮሰው ሻማ ዛሬ የብዙዎች ህይወት መለወጥ የእለት ተእለት ክስተት ለመሆን ችሏል።

ዛሬም እንደ ሁሌው ከእኔ ጎን ቆማችሁ የዚህን መጽሀፍ የየራሳችሁ ታሪክ ለማጋበብ ወይም ለመስጣት ፍቃደኛ በመሆናችሁ ደስ ብሎኛል፤ ከዚያም ባሻገር ገንቢ ሀሳብ ሰጥታችሁ ታሪካችን ስላዳበራችሁ አመሰግናለሁ። ሲቀጥልም ስሜታችሁን በገዛ ፈቃዳችሁ ከታሪኩ መዉረሻ ላይ ስላሰፈራችሁ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።



የልብ ማእከል በኢትዮጵያ በተለይም መስራች የሆኑት ዶ/ር በላይ አበጋዝ ዘላቂ መፍትሄ የሆነውን የሀገር ልጆችን እውቀት በልብ ቀዶ ጥገና ዙርያ ለማብቃት የዘመናት ትግል አድርገው በመጨረሻም ፍሬ አፍርቶዋል። እኔም አንዱ የዚህ ትግል ፍሬ በመሆን ሙሉ በሙሉ የውጭ ዜጋ ድንበር የነበረውን የልብ ቀዶ ጥገና ሰብረን ገብተናል። ያለ ልብ ማእከል እና ያለ ዶ/ር በላይ አበጋዝ ህልም ራሴን እዚህ ቦታ ላይ ማሰብ ይከብደኛል። ልብ ማዕከልም ካለበት ችግር ወጥቶ አብቦ እና ተስፋፍቶ ትልቅ የአፍሪካ የልብ ህክምና ማእከል እንዲሆን ምኞቴ ነው። ለዶ/ር በላይ አበጋዝም ረጅም እድሜና ጤና እመኛለሁ።

ይህችን አጭር ማስታወሻዬን ለመጻፍ እንድነሳሳ የመጀመሪያውን ትልቅ ጉልበት የሆንከኝ እና ብርታትን ሰጥተህ ወደዚህ ሀሳብ ያስገባኸኝ እንደ ታላቅ ወንድሜ የማየህ ዶ/ር ሰንታየሁ ፀጋዬ ይኸውልህ ምስጋናዬንም ስጦታዬንም ተቀበል። እንዲህም ሲል ነበር ያነሳሳኝ "የምርምር ፅሁፎችን እንደምትፅፍ አውቃለሁ ነገር ግን ይህንን አዲስ ድንበር ከጀመርክ ጀምሮ ብዙ ትልልቅ ስራዎች እንደሰራህ እናውቃለን። ታድያ ለምን እነዚህን ስራዎች ሰውኛ እና ተነባቢ በሆነ መልኩ ፅፈህ ለታሪክ የማታስቀምጠው?" ብሎ ነበር ውስጤ የነበረውን ስሜት እንዲለኮስ ያደረገው። በመቀጠል የስራ ባልደረባና ጓደኛዬ የሆንከው አቶ ሀይለሚካኤል ይስሀቅ (ሀይልሽ) በየጊዜው ሞራሌ ዝቅ ሲል ከፍ እያረክ አበርትተኸኛል። ከቆምኩበት እንድራመድ ገፍተኸኛል። አመሰግንሃለሁ። እወድሀለሁ።

የተዘረከረከውን የወረቀት ፅሁፌን አስብረሽ ተቀበልሽኝ በተጣበበ የስራ ጊዜ እና ጫና ውስጥ ሆነሽ ጹሁፌን በኮምፒዩተር የከተብሽልኝ ማህደር ፈቀደ (ማፂ) ከልብ የመነጨ እና ወደር የሌለው ምስጋናዬን ተቀበይኝ።

እጅግ ብዙ ሩጫ በበዛበት በዚህ አለም ኑሮ የኔን የኑሮ ራስ ምታት ለማረም እና ለመምከር ጊዜያችሁን የሰዋችሁልኝ ውድ የሀገሬችን ንጉሴ አሀፈያን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ተቀበሉኝ። በዚህ አጋጣሚ ለረጅም ጊዜ ሳከብርህ እና ሳደንቅህ የቆየሁት ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ ጹሁፌን ስለገመገምክልኝና እንድተዋወቅህ ስለፈቀድክልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። የዚህን መጽሀፍ ሽፋን ዲዛይን ለተጠበብክበት ወንድሜ እና ጓደኛዬ ሰአሊ ሳሙኤል ሀይሉ (ሳሚ) አከብርሀለሁ፤ እወድሀለሁ፤ አመሰግንሀለሁ። እንዲሁም መጠነ ሰፊ የቃላትና የፊደላት እርማት ለሰራህልኝ ጋዜጠኛና ደራሲ ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ተቀበል።

በመጨረሻም በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የልብ ቀዶ ጥገናዎች የተከናወኑበት ሶስቱን ሆስፒታሎች እና ሙሉ የስራ ባልደረቦቼን ከልዩ አክብሮት ጋር ለማመስገን እወዳለሁ።



# መግቢያ

መጋናኛ አካባቢ ከሚገኘው ፓኖሮማ ሆቴል ውስጥ አራተኛው ሀገር አቀፍ የጡት ካንሰር አመታዊ ጉባኤ ላይ በውቅቱ አጠቃላይ የቀዶ ጥገና ሀኪም ሆኜ ከምሰራበት ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሀዋሳን ዩኒቨርሲቲ አሰራር በተመለከተ አቀረብኩኝ። በስብሰባው ላይ የየክልሉ የጤና ቢሮ ሃላፊዎችና የዩኒቨርሲቲ ሀላፊዎች ተገኝተዋል። በምሳው የእረፍት ጊዜ የደቡብ ክልል ጤና ቢሮ ሀላፊ የነበሩትም በስብሰባው ላይ ነበሩና አንድ ላይ ከታደምንበት የምሳ ጠረጴዛ ላይ አብረን ተሰየምን። በመቀጠል እንዲህ አሉኝ። "ወደኔ ቢሮ የመጣ አንድ ደብዳቤ አለ። እንዳንተ አይነት አቅም ያለውና ወጣት ሰው ቢያገኘው ደስ ይለኛል።" አሉኝ። ሲያብራሩልኝም "ደብዳቤው በጤና ጥበቃ በኩል ሆኖ ከልብ ማእከል ነው የመጣው። ለመሆኑ የልብ ቀዶ ጥገና መማር ትፈልጋለህ?" ብለው ያልጠበኩት ጥያቄ ጠየቁኝ።

ለምን ይዋሻል የልብ ቀዶ ጥገና ህይወቴ የጀመረው በዚህች ቀን ነበር ብል ማጋነን አይሆንብኝም። በሀገሬ ውስጥ የሌለ እና በትምህርት ቤትም ሆኜ ሲከወን ያላየሁትን ነገር እንዴት ልመኝ እችላለሁ? ያላዩትን ሀገር አይናፍቁትም።

ወደ ህንድ ሀገር ሄደን ለሰስት ዓመት የሚቆይ የልብ ቀዶ ጥገና ትምህርት እንደምንከታተል ታቅዶ የሰነዶች መረጃ ልውውጥ ከህንድ ሀገር እየተካሄደ ሳለ እኛ ደግሞ በልብ ማእከሉ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ከውጭ ከሚመጡ የበጎ አድራጊ የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን ጋር እየተማርን እንሰራለን። መቼ እንደምንሄድና የአካሄዳችን ሁኔታ ሳናውቅ በተስፋ እንጠባበቃለን።

በአመቱ ኢጋማሽ አካባቢ ከአሜሪካ ሚኒያፖሊስ ሚኖሶታ የመጣ አንድ ቡድን ጋር ለ10 ቀን የሚቆይ ስራ ተጀመረ። ሁሌም እንደምናደርገው እንግዶቹን ለማስደሰት በትትርና የ10 ቀኑን የቀዶ ጥገና ስራ በአብዛኛው በማየትና አልፎ አልፎ እድሉ ሲሰጥ አጋዥ በመሆን ተሳተፍን። የበጎ አድራጊው ቡድን ወደ አሜሪካ ሲመለስ ቀዶ ጥገና የተሰሩትን ታካሚዎችን መከታተል ቀጣይ ስራችን ይሆናል። በእንዲህ ሁኔታ ኑሮ እየቀጠለ ሳለ አንድ ቀን በልብ ማእከል ስብሰባ ተጠራን። የተጠራንበትም ምክንያት ከአሜሪካ መጥቶ የነበረው ቡድን ከመካከላችን ሁለት ሰዎችን ሙሉ የህንድ ሀገር ወጭ ችለው ለማስተማር እንደወሰኑ ተነገረ። እኔም አንዱ የነርሱ ምርጫ



እንደነበርኩ ተነገረኝ። እነሆ ወደ ልብ ቀዶ ጥገና ጉዞ አንድ እርምጃ ፈቀቅ አልኩኝ። የተስፋ ጉዞ ተጀመረ።

ለአንድ አመት በልብ ማእከል እየተማርንና እየሰራን ከህንድ ሀገር ዶክመንታችን አልቆ እስኪመጣ ቆየን። በወርሀ ነሀሴ ሁሉም አልቆ በስድስት ሰው የተዋቀረው ቡድን የህንድ ግዛት ወደሆነችው ባንጋሎር ጉዞ ሆነ። ከረጅም አድካሚ የቅብብሎሽ ጉዞ በኋላ በሚቀጥለው ቀን እኩለ ቀን ላይ ሰስተኛው የህንድ ትልቁ ከተማ ባንጋሎር ገባን። የምንማርበት ናራያና ኢንስቲትዩት ኦፍ ካርድያክ ሳይንስ (narayana institute of cardiac science) ከከተማው መውጫ ላይ የሚገኝ ነገር ግን በህዝብ የተጨናነቀ የመኖርያ አካባቢ ነው። በሰላም መግባቴን ለቤተሰቤ ለማሳወቅ ስልክ መደወል ነበረብኝና ከሆስፒታሉ ጀርባ ከሚገኘው መኖሪያችን ወጥቼ ሄድኩ። በሰላም መግባቴን ከነገርኳቸው በኋላ ማወቅ ያቃተኝ ከበድ ሲቃ ደርሶ ተናነቀኝ። ርቄ መሄድ ይሁን ያልጠበኩት እይታ ከፍተኛ ግርግር ረብሾኝ ተንሰቅስቄ አለቀስኩኝ። ባለቤቴ በወቅቱ ብታጽናናኝም ትቸት ይመጣል የሚል ስሜት በእኔም በእሷም ዘንድ ተሰምቶን ነበር። እነሆ ያ ሁሉ ታልፎ የተፈራው ሳይሆን ለዚህ በቃን። እግዚአብሔር ይመስገን።

ከዚህ በመቀጠል የምታነቡት ጽሁፍ በሀገራችን መሬት እና በሀገራችን እውቀት የልብ ቀዶ ጥገና ሲጀመር እና ሲጎረምስ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ከራሱ ከቀዶ ጠጋኙ የተበረከተላችሁ ነው። መልካም ንባብ።

# 1

# ሀፍረት እና ስኬት

ከጠዋቱ 5፡00 ሰዓት ገደማ ነበር በተለምዶ "ሩዋንዳ ማዞሪያ" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከሚገኝ አንድ የልብ ህክምና ክሊኒክ ለምክክር (consultation) ተጠርቼ ነበር። ከመኪናዬ ወርጄ ወደ ክሊኒኩ እየዘለቅሁ ሳለሁ ስልኬ ጮኸች። ስልኩን አየሁት፤ የማውቀው ስልክ ነበር። አንስቼ "ሀሎ" እንዳልኩ የጠበኩት ሀሎ ድምፅ ሳይሆን የሚያለቅስ የወንድ ልጅ ሲቃ ነበር የጠበቀኝ። የሚያለቅሰው ለራሱ አልነበረም። አዎ የሚያለቅሰው ከአንድ ዓመት በፊት የልብ ቀዶ ጥገና ላደረገችው እና ሊያገባት ላሰባት እጮኛው ነበር።

**ከአንድ አመት በፊት (2010 ዓ.ም)**

ከአንድ አመት በፊት ልብ ማዕከል የሚገኘው ስራ በታዬ ሆኜ

በሚቀጥሉት ቀናት ልሰራ ስላሰብኳቸው ቀዶ ጥገናዎች እያወጣሁ እያወራሁኝ ባለሁ ታካሚ ተመላላሽ ክፍል (OPD) እንደሚፈልገኝ ተነገረኝ። በዚህ ባልተለመደ ሰዓት ታካሚ የሚያመጣ ቢሆንም ስራዬን ለማቋረጥ ተገደድኩ። በፍጥነት ደርሼ የምትፈልገኝን ታካሚ አገኘኋት። ቀደ ሲል የሚያምር ፈገግታ ከጨዋነት ጋር ይታየኛል። ከልብ ሕመሟ ጋር ያሳለፈቻቸውን ከ10 በላይ አመታት በስፋት እና በዝርዝር አጫወተችኝ። እንቅልፍ እንደሌላት ጭምር እንዴት ኑሮዋ እንደሚጎዳት አስረዳችኝ። ምርመራችንን ከጨረስን በኋላ የልቧን ችግር ተረዳን። በግራ የልብ በር ላይ ከቶንሲል ጋር ተያይዞ በሚከሰት ችግር በሚደጠገን መልኩ ተጎድቷል። በመሆኑም ከመጥበቡም በሻገር ወደኋላ ማፍሰስም ያሳያል። ይህች በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ የምትገኝ ወጣት እንደሆነው የልቧ በር ከፊኛ ከመጥበቡና ከማፍሰስ በሻገር የልብ ምቷ የተዛባ ነበር። ይህም Atrial Fibrillation ተብሎ የሚጠራው የተለመደ የልብ ምት መዛባት ሲሆን በእንዲህ ዓይነት የልብ በሽታ ተጠቂዎች ላይ በአብዛኛው ይከሰታል። ይሁን እንጂ የዚህች ወጣት ልብ የተሸከመው በሽታ ብቻ አልነበረም። የልጅነት ፍቅሯን ያገኘችበትን አፍቃሪዋን አግብታውና ልጅ ወልዳለት መኖር ትልቁ የህይወቷ ዓላማ ነበር። ይህን ለማሳካት የሚያስፈልጋትን ቀዶ ጥገና ከፍላጎቷ ጋር ማጣጣም ያስፈልግ ነበር።

እንዲን የልቧን በር መቀየር አስቸጋሪ አልነበረም። ይልቁንም ደም ለማቅጠን የምንወስደው (Warfarin) በመባል የሚታወቀው



መድኃኒት ለማርገዝ እና ለመውለድ አስቸጋሪ ማድረጉ ነበር። በልብ በር ላይ የሚቀየሩት የሽፋሽ ዓይነቶች ሁለት ሲሆኑ የብረት በር የሚገጠምላቸው Warfarin መውሰድ ግዴታቸው ነው። ይሁን እንጂ ከሠውነታችን ጋር ተመሳሳሎ (Tissue Valve) የሚገጠሙ ሽፋሽ የሚገጠምላቸው ታካሚዎች ግን ደም ማቅጠኛ ሊያስፈልግ የሚችልበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን ይህች ያልታደለች ወጣት ግን የልብ ምቷ ገና ከጅምሩ በመዛባቱ ምክንያት የደም ማቅጠኛ መውሰድ ግዴታዋ ይሆናል።

በመጨረሻም መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ሁለት ቀዶ ጥገና በማድረግ ብቻ ነበር። ይኸውም መጠገን የማይቻለውን የልቧን በር ከሠውነት ጋር ተመሳሳሎ በሚገጠ (Tissue Valve) በሚባለው ሽፋሽ መቀየር እና የተዛባውን የልብ ምት የሚያስተካክል ተጨማሪ የልብ ቀዶ ጥገና (Maze Procedure) መስራት ነበር።

**ከሦስት አመታት በፊት (2008 ዓ.ም)**

ወደ እንግሊዝ ሀገር ሀገር የሄድኩት የሦስት ዓመት የልብ ቀዶ ጥገና ለመማር ነበር። በዚህ የሠው ልጅ እንደ ማሽን በቀን ከ35-40 ቀዶ ጥገና በሚያስፈልበት የልብ ቀዶ ጥገና ማዕከል የመማር ዕድል በማግኘቴ ከልቤ ብዙ ተሰምቶኛል።

በመጀመሪያው ወር ምደባዬ የጎኑ የልብ ሕክምና ክፍል ውስጥ

(ICU) ክፍል ተመደብኩ። በዚህም ክፍል ከልብ ቀዶ ጥገና የወጡ ታካሚዎችን መከታተል ዋና ስራዬ ነበር፡የ40 ቀን ዕድሜ ሆኖ የተመደብኩበት የጽኑ የልብ ሕክምና ክፍል የሕንዶች ኩራት በሆነውና በልብ ቀዶ ጥገና አንቱ በተባለው የልብ ቀዶ ጠጋኝ ዶ/ር ፒቪ ራኦ (DR. PV. Rao) ሀኪም ክፍል ውስጥ ነበር።

የሚጠበቅብኝን ትህትና እና ዲሲፕሊን ጠብቄ ከመስራት በሻገር የዶ/ር ፒቪ ራኦ (DR. PV. Rao) ቀዶ ጥገናዎች መልመድና ብቁ ሆኖ መገኘት ከባድ ነበር።

የሚያስቸግሩ ትልልቅ ቀዶ ጥገናዎችን በቀን ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት ሲሰራ ማየት የተለመደ ነበር። ይገርመኛል፤ ሰየው ደስ ይለኛል፡ እሱ ግን አይቶኝ የሚያውቅ እንኳን አይመስለኝም ነበር።

የእለቱን የቀዶ ጥገና ስራ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ወደ ጽኑ ታማሚ ክፍል (ICU) ይመጣል። ፈጣን የህሙማን ጉብኝት ያደርጋል። ከሕንዶቹ የልብ ሕክምና ስፔሻሊስቶች (cardiologist) እና የጽኑ ህሙማን ስፔሻሊስት ሀኪሞች (intensivist) ጋር አውርቶ፤ የሚፈለገውን ትዕዛዝ ሠጥቶ ይሔዳል። እኔም በዚህ መካከል የምችለውን ለመማር ጥረት አደርጋለሁ። ኑሮ በዚህ መንገድ ለሁለት ወር ቀጠለ።



የተለመደው ሌሊት መነሳት ከ1፡30 በፊት ሆስፒታል መገኘት ዶ/ር ፒቪ ራኦ (DR. PV. Rao) ወደ ኦፕሬሽን ክፍል ከመግባቱ በፊት የሚያደርገውን ከቀዶ ጥገና የወጡ ታካሚዎች ጉብኝት ራውንድ (Round) ላይ ዝግጁ ሆነን ለመገኘት ሽር ጉድ እንላለን። ታካሚዎችን እናያለን፤ የህሙማን ፋይል እናገላብጣለን፤ ስለ ቀዶ ጥገናው ለማንበብ እንጥራለን። በዚህም ቀን እንደተለመደው ፈጣን የህሙማን ጉብኝት ተደርጎ አለቀ።

ማንነቴንና ከየት እንደመጣሁ አያውቁኝም ያልኩት የሕንዶቹ የልብ ቀዶ ጥገና ኩራት ወደ እኔ ዞር ብሎ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ። "አንተ ቀዶ ጠጋኝ ነህ አይደል? እኔ የልብ ቀዶ ጥገና እንዳስተምርህ ትፈልጋለህ? መልስህ አዎ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ እኔ ወደምሰራበት ቀዶ ጥገና ክፍል ግባ። ከእኔም ስር ሆነህ በእኔ ስራ ትማራለህ" አለኝ። የሰማሁትን ነገር ለማመን ተቸግሬ ነበር፡ በአንድ ጊዜ እንዴት ይሔ ሁሉ ነገር፡ ያቀኛል ብዬ ያልጠበኩት ሰውዬ በክንፉ ስር አድርጎ እስከ መጨረሻው ድረስ ሊያተምረኝ እንደሚያፈልግ በአደባባይ ተናገረ። ተደመምኩ። ወደሚሰራበት የቀዶ ጥገና ክፍል ወስዶ ከሁሉም የቀዶጥገና አባላት ጋር በፍፁም ጨዋነት አስተዋወቀኝ።

ታዲያ ከዚህ በየቀኑ ተዓምር ደጋግሞ ከሚሰራ ቀዶ ጠጋኝ ሀኪም ጋር ለሦስት ዓመታት ሰርቼ ከመጣሁ በኋላ ብዙ ነገሮችን ለመስራት ስነሳሳ ያለምክንያት አልነበረም።በዚህ ሆስፒታል ውስጥ የልብ ምትን

CamScanner

የሚያስተካክለውን Maze Procedure በብቸኝነት የሚሰራውም ደግሞ ዶ/ር ፒቪ ራኦ (DR PV Rao) ነበር። በሦስት ዓመት የትምህርት ቆይታዬ በደርዘን ለሚቆጠሩ ጊዜያት ረዳት ቀዶ ጠጋኝ ሆኜ በዚህ የቀዶ ጥገና ተካፍያለሁም፤ ሰርቻለሁም። ዛሬም ይህንን የቀዶ ጥገና ለመስራት ስወስን በባዶ ሜዳ ላይ ያለእውቀት እና በድፍረት አልገባሁም። እናም እኔ መስራት እንደምችል ለራሴ ነገርኩት፤ ከዚያም ያለውን አማራጭ ለታካሚዬ ገለፅኩ። እኔና የሙያ ባልደረባዬ በአንድ ወገን ታካሚዋና እጮኛዋ በሌላ ወገን ተቀምጠን ስለምርጫዎቹ በሰፊው ተነጋገርን። እኔም ሁሉንም የቀዶ ጥገና አይነቶች ከነደካማ እና ጠንካራ ጎናቸው በሰፊው አስረዳሁ። እነርሱም ሁሉንም ካዳመጡና ከመረመሩ በኋላ ምርጫቸው የደም ማቅጠኛ (Warfarin) የሚባለውን መድኃኒት ለማስወገድ እና የትዳር ሀሳባቸውን በልጅ ለማጀብ የሚያስችላቸውን መረጡ። በዚህም መሰረት ከሰውነት ጋር ተመሳሳዩ የሚገጠመውን (Tissue Valve) እና የልብ ምትን የሚያተካክለው (MAZE PROCEDURE) ቀዶ ጥገና እንዲሆንላቸው ጠየቁ። የሚመጣውንም ማንኛውም የጎንዮሽ ችግር በተለይም የደም መፍሰስን ተቀብለው ፈረሙ።

*****



እ.ኤ.አ በ1994 Cox እና ጓደኞቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ94% በላይ ስኬታማ የሆነ የልብ ምት መዛባትን የሚያስተካክለውን (Maze Procedure- Cox -I) ለዓለም ካስተዋወቁ በኋላ የብዙዎችን ጥያቄ የመለሰ ቀዶ ጥገና ሆኗል። (7)

ይሁን እንጂ ይኽ ቀዶ ጥገና አስቸጋሪ የደም መፍሰስ ሊያመጣ ስለሚችል እና ለመቆጣጠርም አስቸጋሪ በመሆኑ በዓለማችን እጅግ በጣም ጥቂት በሆኑና የረጅም ዓመት ልምድ ባላቸው የልብ ቀዶ ጠጋኞች ዘንድ ብቻ የሚደፈር ቀዶ ጥገና ነበር። በልብ ጠጋኞችም ዘንድ መለስተኛ የልብ ንቅለ ተከላ (Mini Transplant) በመባል የሚጠራ ሲሆን፤ የግራ ልብን ሙሉ በሙሉ ነቅሎ እንደገና መትከልን የሚጠይቅ አስፈሪና ውስብስብ ቀዶ ጥገና ነው።

ታዲያ በአፍሪካ ለዚያውም ከሰሃራ በታች (Sub Saharan Africa) ባለ አንድ ወጣት የልብ ቀዶ ጠጋኝ ይሔ እንዴት ሊታሰብ ይችላል? እንዴትስ ተብሎ ይፈፀማል?

*****

ለቀዶ ጥገናው በቂ ዝግጅት አደረግን ደምም በብዛትና በዓይነት አዘጋጀን ሠባት ሰዓት የፈጀው የልብ ቀዶ ጥገናው በድል ተጠናቀቀ፤ በውጤቱም በፍፁም በልጠበቅነው መንገድ የልብ ምቷ ተስተካከለ፤ የማራ ልቧ በር MITRAL VALVE ከሰውነት ጋር ተመሳስሎ በሚሰራው (Tissue Valve) ተቀየረ። ከቀዶ ጥገና በኋላ የነበራት ቆይታ ፍፁም ሰላማዊ ሆነ።

በውጤቱ ታካሚዋ፣ እጮኛዋ እና ቤተሰቦቿ በፍፁም ተደሰቱ። እኛም በውጤታችን ኩራን፤ ተደሰትን። እኔም የልብ ቀዶ ጥገና በሀገሬ ምድር በጀመርኩበት በመጀመሪያ ዓመት እንዲህ ዓይነት ትልቅ ስኬት ማግኘቴ ያስጠበኩት ነበር። መምህሬን እያስታወስኩ፤ አመሰገንኩ፤ ከአስር ቀን በኋላ ታካሚያችን ከሆስፒታል በሰላም ወጣች የልብ ምቷም የተስተካከለ ሆነ። ስለዚህም የዚህች ወጣት ትዳርም አብሮ ታከመ።

ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ እጮኛዋ ደውሎ እየተንሰቀሰቀ እያለቀሰ የፍቅረኛውን ሕይወት በቁፍ ላይ መሆኑን እንዲሁም ኩላሊቷ እየደከመ እንደሆነና ጥቁር አንበሳ መተኛቷን ነገረኝ። ላብ አጠመቀኝ። ትንሽ ዝም አልኩኝ፤ መልስ አጣሁ፤ አፈርኩኝ፤ ኩራቴ ሁሉ ገደል ገባ፤ ተሸማቀቅኩኝ። እጮኛዋን የቻልኩትን ያህል ላረጋጋው ሞከርኩና ወደ ጥቁር አንበሳ በረርኩ። በሆስፒታሉ ተገኝቼ ከሀኪሞቹ ዝርዝር መረጃ ከወሰድኩ በኋላ ሁኔታውን ተረዳሁ። ችግሩ ገባኝ። የቀየርንላት Tis-



sue Valve ኢንፌክሽን (Infection) አጋጥሞታል። በዚህ ምክንያት ማፍሰስ የጀመረ ሲሆን ደም ማነስ ተደምሮ ኩላሊቷም በቋፍ ላይ ሆነ። ስለዚህም የኩላሊት እጥበት (Dialysis) ያስፈልጋት ነበር። እጮኛዋ ፀበል እንጂ የኩላሊት እጥበት (Dialysis) በፍፁም አትደረግም አለ። ከብዙ ንትርክ እና ጭቅጭቅ በኋላ የወጣቷን ሕይወት ለማዳን የኩላሊት እጥበት (Dialysis) ተጀመረ። በዚህም ጊዜ ደም እየወሰደችና ከፍተኛ የኢንፌክሽን መድሀኒቶች እየተሰጣት ነበር። በየቀኑ ኢንፌክሽኑ ለውጥ ማምጣት ጀመረ። ከሦስት የኩላሊት እጥበት (Dialysis) ፕሮግራም በኋላ ኩላሊቷ ጥሩ መሻሻል አሳየ። መሽናትም ጀመረች። ለስድስት ሣምንታት የኢንፌክሽን ሕክምናዋንም በሆስፒታል ተኝታ ታክማ ጨረሰች።

ከበሽታዋ አገግማ ከጥቁር አንበሳ ስትወጣ የትዳር አጋሯ ግን ተለይቷት ጠበቃት። እሷ በነበረችበት ስቃይ ጊዜም ከጎኗ አልነበረም፤ ከወጣች በኋላም በአማላጅ ከአንዴም ሁለቴ ተጠርቶ ቢለምን አሻፈረኝ አለ። "የእኔና የአንቺ ነገር አበቃ" አለ። የተፈጠረውን ነገር ሳውቅ ሀፍረቴ ጨመረ። ያሁሉ ልፋት አስፈላጊ አልነበረም። በብረት ቫልቭ (Mechanical Valve) ቀይሬ፤ ሌላ ቀዶ ጥገና ሳያስፈልግ አሁን የገባችበት ኢንፌክሽን ሳይከሰት ዋርፋሪን እየወሰደች እንደ እድሏ መኖር ትችል ነበር። "አንተ ጀብደኛ!" ብዬ ራሴን ገሰፅኩ።

ክትትላችንን አጠናክረን ቀጠልን፤ በተቻለ አቅም ቶሎ ቶሎ

ለማየት አጭር ቀጠሮ አደረግን፤ በአዲስ አበባ ውጪ ለሚመላለስ ታካሚ ወጪውም ሆነ ድካሙ ቀላል አይደለም። በዚያ ላይ አሁን እንደበፊቱ ከእጮኛዋ ጋር ሳይሆን በእድሜ ከገፉት እናቷ ጋር ነበር የምትመላለሰው። ይህንን ሳይ የበለጠ ያመኝ ነበር።

ቀናት፣ ወራት ዓመታት አለፉ። ሰውነትዋ ቀስ በቀስ ተመለሰ። ምንም እንኳን እንደገና የልብ ቀዶ ጥገና በማካሄድ ኢንፌክሽን የነካውን የልብ በር (MITRAL TISSUE VALVE) በብረት ቫልቭ ለመቀየር ህክምና አቅርቦቱ የነበረ ቢሆንም ቤተሰቦቿ አደጋውን (Risk) መቀበል ባለመፈለጋቸው ምክንያት ሳይሰካ ቀረ።

እኔም በውስጧ ሲቀፋ፣ ውበቷ ሲመለስ ደስ አለኝ። ደባብ ብላ አንድ ቀን ማርገዝ እና መውለድ እንደምትፈልግና የሚወዳት እና የምትወደው ጓደኛ እንዳላት አጫወተችኝ። የእኔም መልስ "ይበጅሽ፣ አፍቅሪው" ነበር። ቀጥሎ ጥሏት የጠፋው የበፊት እጮኛዋ በአማላጅ ልጅ እየጠና መሆኑንና የልጅነት ፍቅራቸው እንዲቀጥል እየተማጸነ መሆኑን ነገረችኝ።እኔም "የፍቅር አምላክ ፍርዱን ይስጥ" አልኳት።

የህን አስቸጋሪ ጊዜ ባለፈች አመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይህች ወጣት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ተኝታ እንደገና ደውላችልኝ፤ ሆዴን ቦር ቦር እያለው ምን ተፈጠረ በማለት ጥያቄዬን አቀረብኩኝ።



ነገር ግን ዛሬ ይህች ወጣት የደወለችልኝ የወንድ ልጅ እናት መሆኗን እና በሰላም መገላገሏን ልትነግረኝ ነበር።

ጊዜ አላጠፋሁም ነበር፤ በሩጫ ከልብ ማዕከል ወጥቼ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስድስተኛ ፎቅ በፍጥነት ሔድኩኝ። አቅፌ ሳምኳት። ሕፃኑንም ባለማመን መንፈስ ጉብቼ አየሁት። ትልቅ ሸክም የቀለለኝ መሰሎ ተሰማኝ። ያሰብኩት ተሳካ፤ ያለምኩት ደረሰ፤ የሚለውን ዘፈን ማን ነበር የዘፈነው?



ሥዕል ፲፫ ዶ/ር ፒቪ ራኦ በህንድ ቤንጋሎር ናራያና የልብ ህክምና ማእከል ከፍተኛ የልብ ቀዶ ጥገና ሲሆን በልብ ድካምና የልብ ጉቀለ የበለ ዐይ ስፔሻሊስት ናቸው፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በበጎፈቃድ ከኛ ሃገር አደርገው የልብ ቀዶ ጥገናን እውቀት ቀልበውኛል።






ሥዕል ፲፬ የልብ ማእከል በኢትዮጵያ በጥቁር አንበሳ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ ለልብ ቀዶ ጥገና በሀገሪቱ ብቸኛ እና በመሳርያ በብቃት የተሟላ ቤት ነው።

# 3

# አልፋና ኦሜጋዬ

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስከ ሌተናል ኮሎኔል ማዕረግ ድረስ ያገኘው ዶ/ር ጆን ጊበን (Dr. John Gibbon) ሲወርድ ሲወራረድ ከመጣ የሀኪም ቤተሰብ ዘር የተወለደ ነበር። የአጠቃላይ ቀዶ ጥገና ተማሪ በነበረበት በሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ (Harvard) ውስጥ ስለ ለልብ ቀዶ ጥገና መሰረት የጣለ አንድ አጋጣሚ ተከሰተ። ታሪኩ እንደዚህ ነበር አንዲት ሴት የሀሞት ጠጠር ቀዶ ጥገና ከከናወነች በኋላ ከፍተኛ የሆነ የረጋ ደም ወደ ሳምባዋ የደም ቧንቧ በመሄድ ሕይወትዋ አደጋ ላይ ይወድቃል። በድንገት ወደ ቀዶ ጥገና በመጣበት ደረቷን በመክፈት በሳንባዋ የደም ቧንቧ ውስጥ የነበረውን የረጋ ደም ማውጣት የነበረ ቢሆንም ቀዶ ጥገናው የተመራው አስተማሪው በነበሩት በዶ/ር ቸርችል



(Churchill) ነበር። ይህ ከፍተኛ ትግል የተደረገበትና ረጅም ሰአት የፈጀው ቀዶ ጥገና የሴቲቷን ሕይወት ማትረፍ ሳይቻልበት ቀረ።

በወቅቱ (1931) ተማሪ የነበረው ዶ/ር ጆን ጊበን (John Gibbon) አጋዥ ቀዶ ጠጋኝ በመሆን የተሳተፈ ሲሆን በቀዶ ጥገናው ክንውን ላይ ደስተኛ አልነበረም። በቀዶ ጥገናው ደም የበዛበትና በግልጽ እይታ የሚከወን አልነበረም ነበር። ዶ/ር ጆን ጊበን (John Gibbon) በዚህ ሁናቴ ህይወትዋን ያጣችውን ታካሚን ለረጅም ጊዜ ሊረሳት አልቻለም ነበር። እናም አንድ ሀሳብ በአይምሮው ተሰረፀ፣ እንዲህም ብሎ ተናገረ። የዚህችን ሴትና የዚህን ዓይነት ኦፕሬሽን ለመስራት አንድ ማሽን ያስፈልጋል ይህም ማሽን በኦፕሬሽን ወቅት የልብን ስራ ተክቶ የሚሰራ ማሽን መኖር አለበት። እናም የደም ዝውውርን የልብን ስራ ተክቶ ለሚሰራው ማሽን በመስጠት ደም አልባ የተሳካ ሠርጀሪ መስራት ይቻላል አለ።

ትምህርቱን አጠናቆ ወደ Pensylvenia research ማዕከል ሲመለስም የጠነሰሰውን ሃሳብ ይዞ ወደ ላብራቶሪ ገባ። በዚሁ ላብራቶሪ ውስጥ ብዙ ድመቶችን መስዋዕት እያደረገ ምርምሩን ቀጠለ። ይሁን እንጂ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በመሃል በመከሰቱ ወደ ጦር ግንባር በመሄዱ ምርምሩን እንዲያቋርጥ ተገደደ። በግዳጁም እጅግ የበዙ ቀዶ ጥገናዎችን ሲሰራ ቆይቶ የኮሎኔልነት ማዕረግ ይዞ በህይወት ተመለሰ። ከዓላማው ፈቀቅ ያላለው ዶ/ር ጆን ጊበን (John Gibbon)

ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ ጊዜ ሳይጠፋ በቀጥታ ወደ ጀመረው ምርምር ገባ።

በ1973 በሳተመው ጹሁፍም ይህንን ማሽን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ የአንዲትን ድመት ህይወት ለአራት ሰዓት ማቆየት መቻሉን መግለጹ ይታወሳል። እነሆ ከብዙ አመታት ትግል በኋላ በ1953 የ20ኛው ክፍለ ዘመን ትልቁ አብዮት የሆነውን የልብንና የሳንባን ሥራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን ለዓለም አስተዋወቀ። (2,3)

አሁን ግን ላብራቶሪ ውስጥ በድመት ላይ ሳይሆን የሰራውን ማሽን በሰው ልጆች ላይ ማሳየት ይጠበቅበት ነበር። ይህንንም ያደረገው በአንዲት የ 18 ዓመት ወጣት ሴት ላይ ሲሆን በተፈጥሮ የልብ ቀዳዳ (Atrial Septal Defect, ASD) የመዝጋት ቀዶ ጥገና በመስራት ነበር። በዚህም ቀዶ ጥገና ስኬታማ የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራ ማሽን ለአለም ማበርከቱን አሳየ። ይህ የ20ኛው ክፍለ ዘመን አብዮት በየሀገሩና በየአመቱ እየተሻሻለ በመሄድ የሚሊዮኖችን ህይወት የታደገ የልብ ቀዶ ጥገና መሰረት ሆነ።

እነሆ በሀገራችንም ይህንን የልብንና የሳምባን ሥራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን በመጠቀም በሀገራችን ልጆች ብቻ በሀገራችን መሬት እንዴት እንደተፈፀመ ጀባ ልበላችሁ። በግንቦት ወር መጨረሻ 2009 ዓ.ም በልብ ማዕከል በኢትዮጵያ የሚዲካል ዳይሬክተር በር



የየክፍሉ ኃላፊዎች በተገኙበት ስብሰባ ላይ አንድ ጉዳይ ለመወሰን ተሰብስበናል። ምንም እንኳን ከህንድ ሀገር ትምህርቴን ጨርሼ ከመጣሁ ገና 15 ቀን ቢሆነኝም በእኔ የሚመራው ሙሉ የኢትዮጵያ ቀዶ ጥገና ሕክምና ቡድን ቀዶ ጥገና ለመጀመር እንዲችል ለመወሰን ነበር።

ይህ የሆነበት ምክንያት በሀገራችን ልብን ከፍቶ እና አቁሞ የመስራት ሂደት ከውጭ ሀገር በሚመጡ የበጎ አድራጎት ቡድን (Mission) የሚደረግ ብቻ በመሆኑ ነበር። እናም ዛሬ በዚህች ታሪካዊ ቀንና ስብሰባ ያለምንም የውጭ ዜጋ ተሳትፎ በተሟላ የሀገራችን ቡድን የልብ ቀዶ ጥገና ይጀመር ለማለት፣ በጋራ ለመወሰን እና ከማንም ግለሰባዊ ተጠያቂነት ለማምለጥም ጭምር ነበር።

ከህንድ ሀገር በመጣሁ ማግስት ያለምንም እረፍት ከአሜሪካ ሀገር የመጣን የበጎ አድራጊ ቡድን Mission እንዳግዝ ተደረገ። በዚህም 12 የልብ በሮችና አንድ የተዘጋ የደም ቧንቧ የመክፈት ቀዶ ጥገና አከናውነን። ቡድኑ የ10 ቀን ቆይታን ሲያጠናቅቅ በሰጠው ግብረ መልስ "ዶ/ር ፈቀደ አግዋር የልብ ቀዶ ጥገና ማከናወን ይችላል። የበጎ አድራጊ ቡድንም (missionaries) መጠበቅ አያስፈልጋችሁም" ብለው ለሆስፒታሉ ሀላፊዎች ግምገማቸውን ሰጡ።

ምንም እንኳን ያለኝ የትምህርት ማስረጃ እና ከኢትዮጵያ ምግብ

CamScanner

የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን (Dacii) ያገኘሁት የ"መስራት ትችላለህ" ወረቀት በመሠረቱ በቂ ቢሆንም፣ በሆስፒታሉ የልብ ቡድን ይህ በአሜሪካው ቡድን የተሠጠው ግብረ መልስና እንደመጣሁ ከዚሁ ቡድን ጋር በሰራኋቸው ቀዶ ጥገናዎች የተገኘው ውጤት ሁሉም የሆስፒታሉ አባል በእኔ የመስራት አቅም ላይ እንዲወስን አስቻለው። በሁሉም ሰው ፊትም ላይ ጥሩ ስሜት ነበር።

ነገር ግን በስብሰባው ላይ ልረሳው የማልችለው አንድ ሀሳብ ቀረበ። ይህም "እኛ ምን የሚያስቸኩለን ነገር አለ? ለምን ታካሚ እንደዚህ እየሰበሰብን ፈረንጆች (Foreigner) ሲመጡ ቢሰራ አናደርግም? እኛ ለዚህ ብቁ አይደለንም" የሚል ማብራሪያ እና ማስፈራሪያ ሀሳብ ቀርቦ ነበር። እኔም ይህ ሀሳብ የዚያንን ዕለት ባይወድቅ ኖሮ ዛሬም ድረስ ተምሮ እንዲፈተማረ ፈረ እና አድማ ልካችንን የልብ ቀዶ ጥገና አጋዥ እንጂ መሪ የልብ ቀዶ ጠጋኝ መሆን ባልቻልን ነበር። እኔ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ አይደለሁም የሚለው ሀሳብ ብቻውን ቀርቶ ወደቀ። ከአገር ተቃውሞ ውጪ የልብ ቀዶ ጥገና በሀገራችን ልጆች እየተመራ በሀገራችን መሬት እንዲሰራ ተወሰነ።

እኛም (Team Ethiopia) የመጀመሪያውን የልብ ቀዶ ጥገና ለመስራት እዚህ ዝግጅት እና መሰናዶችን ተጀመረ።የልብ ማዕከል በኢትዮጵያ ለዚህ ቀን ለመብቃት ረጅም አመታት መጓዝ ነበረበት። የዚህ ቀን ትርጉም እጅግ ብዙ ቢሆንም በዋነኝነት ከየአቅጣጫው



ለሚወረወርበት ትችት እና ተቃውሞ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መልስ የሰጠ ሆኗል። ይህ በመላው ኢትዮጵያውያን የተመሰረተው ያማረና የተሟላ ቤት የፈረንጆችን መምጣት ሳይጠብቅ የእለት ተግባር እንዲፈጽም የሚያስችለው ትልቁ መሰረት ነበረና ነው።

እሁድ ከምሽቱ 12:30 አካባቢ በማዕከሉ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ሆኜ የሚደቃውን የልብ ምቴን እያዳመጥኩ በላብ እየወረዘ ያለውን እጄን እንደ ፊቴን ቀጥሎ ደግሞ አንገቴን አሽበታለሁ። የመረጥነው ቀዶ ጥገና ቀላል የሚባል ሲሆን በተፈጥሮ የልብ ክፍተትን መዝጋት ነበር። ጭንቀቴ እና ሀሳቤ የሆነ በታ ላይ "የስርዓት እክል (System Failure) ቢከሰት ምን እናደርጋለን" ነበር? ምክንያቱም የሀገራችን ታሪክ የመጀመሪያው የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን በመጠቀም የልብን ክፍት ቀዶ ጥገና የመስራት ሂደት በሙሉ የሀገራችን ቡድን ስለነበረ ነው።

በፍርሃቴ እና በድካሜ መጠለያዬ ወደሆነው አምላኬም የሄድኩት ይህንን ጫና መቋቋም የሚያስችል አቅም ለመጠየቅ ነበር።በመንፈሳዊ ሀይወቱ ጠንካራ ሠው አይደለሁም። ነገር ግን መደበቂያዬም ማምለጫዬም፣ ዛሬም፣ ትላንትም፣ ነገም ፈጣሪዬ ነው። ለዚህም ተንበርክኬ ተማፀንኩ። "Make it or Break it" አልኩኝ ለራሴ።

ይህች ወጣት ብሩህ ፈገግታ እና ዓይንን ሰርስረው የሚገቡ ብሩህ ዓይኖች አሏት። ከሁሉም በላይ የሠው መውደዷ እና ተጫዋችነቷን እወድላት ነበር።ባለፉት ስምንት ዓመታት ከሆስፒታል ሆስፒታል በስትትል ስትንከራተት ወደ "ውጪ ሀገር መሄድ አለብሽ" ከመባል በሽገር እዚህ ግባ የሚባል መፍትሔ አላገኘችም ነበር። ከበሽታ በላይ ስቃይ የሚሆነው በቀላሉ መወሰን አለመቻል ምርጫ ማጣት፤ ተስፋ ማጣት ከባድ ነበር። ይህች ወጣት ለምንስ አንድ ልቧን ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚሰራ ሲስተም ትሰጣለች? ለምንስ ሲባል እኔን ታምነኛለች? ለምን ወደ ውጭ መሄድን አልፈለገችም? በቂ መልስ አልነበረኝም።

ሰኞ ጠዋት ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ከመግባቴ አስቀድሜ ወደ ማረፊያ ክፍል ሄጄ ታካሚዬን ጎበኘኋት። በህመም፣ በጭንቀት፣ በፍርሀት እንዲሁም በእንቅልፍ እጦት የገረጣ ፊት ተመለከትኩኝ። በዚህ ቀን ያየሁት የዚህች ታካሚዬ ምስል ከአዕምሮዬ ጓዳ ከማይጠፉ አሳዛኝ ስዕሎች አንዱ ሆኖ ተቀምጧል።

በዚህ ታሪካዊ ቀዶ ጥገና የአዲስ አበባ ነዋሪ የሕግ ባለሙያ በጥሩ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የሚሰራና በጠያቂዎች የተከበበ ታካሚ መቆሪጥ ከባድ የአዕምሮ ጫና ውስጥ የሚከት ነበር። ይሁን እንጂ ለመስራት የመረጥነው ቀዶ ጥገና የተፈጥሮ የላይኛው የልብ ክፍል ክፍተት የሆነውን (atrial seotal defect, ASD) የሚባለውን ነበር። ዛሬ ላይ ይህን መስሪያ መጠቀም ልብን ከፍቶ ከሚሰሩ ቀዶ ጥገናዎች



የላይኛው የልብ ክፍል ክፍተት (ASD) ቀላል ነው ይባላል። ይሁን እንጂ "በዚህ የልብ ቀዶ ጥገና መስክ ቀላል የሚባል የልብ ቀዶ ጥገና የለም" የሚል አባባል በባለሙያው ዘንድ ይዘወተራል።

በዚህ አጋጣሚ በህንድ በንጋሎር Banglore በትምህርት ላይ እያለሁ በዚሁ ዙሪያ ስላጋጠመኝ አንድ ሁኔታ ላጫውታችሁ። በመጨረሻው ዓመት አካባቢ (የ3ኛው አመት) ትምህርቴ ላይ ነበርኩ። ቀኑ ደግሞ ቅዳሜ ነበር። በዕለቱ አስተማሪዬ ስምንት ቀዶ ጥገና በአንድ ቀን ለመስራት ፕሮግራም (schedule) ያደርጋል። እብደት ይመስላል በፍጹም እንደማይሳካ ግልፅ ነው። ቢያንስ አራቱን እንደሚሰረዙ እና ለሚቀጥለው ሳምንት እንደሚዛዋወሩ ጠርጥረን ነበር። እኔ ደግሞ ዋና አጋዥ (Assistant) ነኝ ። ይሁን እንጂ በአብዛኛው የቅዳሜ ፕሮግራም ግማሽ ቀን በመሆኑ ሌሎች የቀዶ ጥገና ክፍሎች ከሰዓት በኋላ ክፍት እንደሚሆኑ ይታወቃል።ሲቀጥል አብዛኛው እንደኔ አይነት ተማሪና አጋዥ (Assistant surgeon) ሠራተኞች ከሰዓት በኋላ ስራቸውን በሚያጠናቅቁት ክፍሎች ምክንያት ስራ አይኖራቸውም። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች መስራት ስለሚፈልጉ ብቻ የእገዛን ጥያቄ ሲቀርብ ሁሉም በደስታ ነበር የሚቀበሉት። በመሆኑም ከስምንቱ አምስቱ የላይኛው የልብ ክፍል ክፍተት የሆነውን (atrial seotal defect,ASD) ነበርና በየክፍሉ ተከፋፈሉ። እኔም ሁለት ደርሶኝ ሠርቼ ጨረስኩኝ። የሚገርመው ምንም መሠናክል ሳይገጥመን እዚህም

CamScanner

እዚያም እየተደፎጥን ከምንቱን ቀዶ ጥገናዎች ምሽት 2:00 ሰዓት ላይ አጠናቀቅን። እኔም በጣም ዝዬ እና ደክሜ ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ።

በበነጋታው እሁድ ስለነበር በአብዛኛው ጊዜ አልጋዬ ላይ ማሳለ ቀን አሳልፍ ነበር። ነገር ግን ቅዳሜ ምሽት ፅኑ ሕሙማን ታካሚ ክፍል ተረኛ የነበረችው ኢትዮጵያዊ ዶክተር ነበረችና ጠዋት ላይ ደውላ ቀሰቀሰችኝ። ምንም በለመጠራጠር ትናንት ከተሠሩት ውስጥ አንደኛው የላይኛው የልብ ክፍል ክፍተት የሆነው (atrial septal defect, ASD) ችግር ማጋጠሙንና እንደገና እኩለ ሌሊት ላይ ቀዶ ጥገና እንደተደረገ ነገረችኝ።

እነጋጋዴም ያው ከገቱ ውጪ ሌላ ሰው አይሆንም የሚል ለራሳችን የምንሰጠው የበታችነት መንፈስ ነበረው። ግራ ገባኝ እርግጥ ነው ለብቻዬ የሁለት ታካሚዎችን የላይኛው የልብ ግድግዳ የተፈጥሮ ቀዳዳ (ASD) ሰርቻለሁ። ሌላ ሁለት ደግሞ መምህሬን የማገዝ (Assist) ቀዶ ጥገና አድርጊያለሁ። ግን እኔ የሰራሁት ችግር ቢገጥመው መምህሬ አይደለም እንደዚህ ትልቅ ነገር ተፈጥሮ፤ ለትንሽዋ ነገር እንኳ ደውሎ ነው የሚያጥረርኝ። እና ለምን አልተደወለም? እርግጠኛ ሆኜ መልስ ማግኘት አልቻልኩም።

ብርቅዬዎን እሁድ እንዴት ቆጥቢ እንደማሳልፍ እኔ ነኝ የማውቀው። ግና ከጠዋቱ እንደዚህ ተረብሼ ቀን ሙሉ እያበድኩ ከምውል ተነ



ተነስቼ ልብሴን ለባብሼ ወደ ሆስፒታል ሄድኩ። ስፈራ ስቸር ወደ ፅኑ ሕሙማን ታካሚዎች ክፍል ገብቼ ትናንት እኔ ዋና የልብ ቀዶ ጠጋኝ ሆኜ የሰራኋቸውን ታካሚዎቼን ለይቼ አየኋቸው። አዎ፤ እኔ የሰራኋቸው ሁላም እንደሆኑ አረጋገጥኩ። ለሌሎች ሕፃናት የተሰጠው አንደኛው የላይኛው የልብ ግድግዳ የተፈጥሮ ቀዳዳ (ASD) ላይ ነበር ችግሩ ያጋጠመው። በመሆኑም ማታ በድጋሚ ዋናው መምህራችን ገብቶ ችግሩን ቢፈታውም እንዲ ጉዳት ደርሶ ነበርና ይህ ሕፃን ታካሚ 88 ቀን ICU ውስጥ ማቀቀ። ኩላሊቱም ደክሞ የኩላሊት እጥበት (Dialysis) ላይ ሆነ፤ አዕምሮውም ወደ ቀድሞው አልተመለሰም ነበር። እንግዲህ የልብ ቀዶ ጥገና ቀላል የለውም ይሉሃል እንዲህ ነው።

የልብ ማዕከል በኢትዮጵያ ሆስፒታል መስራችና የህፃናት የልብ ሃኪም የሆኑት ዶ/ር በላይ አበጋዝ ለዚህ ለዛሬዋ ታሪካዊ ቀን መድረስ የከፈሉት መስዋትነት እና የታገሉት ትግል በራሱ አንድ ትልቅ መፅሀፍ ይወጣዋል። የኢትዮጵያ የልብ ህክምና ቡድን ከምልመላው እስከ ፍፃሜው የትምህርት ቤት ቆይታው መጠነ ሰፊ መሰናክሎች ተደቅነውበት የነበረ ቢሆንም በዶ/ር በላይ አበጋዝ ልዩ ጥንቃቄ እና ጥበብ ለዚህ ቀን በቅቷል። ነገር ግን የዚህን የዛሬውን ታሪካዊ ቀን ጫና መቋቋም ተስኗቸው ይመስላል በጊዜ ከሆስፒታል ወጥተው ወደቤታቸው ከተቱ። ምናልባትም ማንኛውም ነገር ቢከሰት የሚመጣውን የስሜት መዘበራረቅ ለለማሳየት ይሆናል። "ፈረስ

ያደርሳል እንጂ አይዋጋም" የሚለው አበበል የዛሬውን እለት በትክክል ይገልጸዋል።

ከአስር ዓመታት በላይ ሆስፒታሉን በኃላፊነት (CEO) ሆነው የመሩት አቶ ሀፍይ ዛፊ በጭንቀት ተወጥረዋል። በሆስፒታሉ ላይ የሚወረወረውን ፍላጻ በሙሉ በቅድሚያ የሚመክቱት ኃላፊያችን የዛሬው ድል ለቀጣዩ የስራ ዘመናቸው ትልቅ እፎይታ መሆኑ ይገባቸዋል። ለዚህም ይመስላል ለቀዶ ጥገና ክፍል ኃላፊዋ በየደቂቃው ያለንበትን ሁናቴ እንድታሳውቃቸው ያደረጉት። ስልካቸው በጮኸ ቁጥር ልባቸው ይደቃል። ከቀኑ 6:00 ሰዓ የጮኸው ስልካቸው ሁለተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው ቀዶ ጥገና ክፍል ነበር።

*****

ከሣምንት በላይ ቀዶ ጥገና ክፍሉንና እቃዎችን ስናዘጋጅ የቆየንበት ሰዓት አልፎ ቀዶ ጥገና ቀንና ሰአት ደረሰ። እነሆ በሀገራችን የልብ ቀዶ ጥገና ታሪክ ፊት በአንድ የልብ ቀዶ ጥገና ዙርያ የሀገር ልጆች ብቻ ከበው ታዩ። ሁላችንም በአንድ ክፍል በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ታካሚያችንን መሀል አስተኝተን ተገኘን። መተያየት፣ መጠራጠር፣ ፀጥታ፣ በአብዛኛው ቀዶ ጥገና ሰዓት ላይ ይስተዋል ነበር። ከስራው



ከብደት እና አስቸጋሪነት በላይ አሉባልታን ማሸነፍ ስቃይ ነበር። በዚህ ታሪካዊ የመጀመሪያ የልብ ቀዶ ጥገና የዚህችን ወጣት የተፈጥሮ የላይኛው የልብ በር ክፍተት ሰው ሰራሽ ግድግዳ (FENESTRATED SAUVAGE PATCH CLOSURE) በማድረግ በስኬት አጠናቀቅን።

ይህንን የተመለከተችው ቀዶ ጥገና ክፍል ሀላፊያችን የሆነችው ሲ/ር ረሺዳ በክፍሉ ውስጥ ወደሚገኘው ስልክ አመራች። እንዲህ ስትልም ለሆስፒታላችን ሀላፊ ለሆኑት ለአቶ ሀፍይ ተናገረች። "ኦፕራሲዮኑ ደስ በሚል ሁናቴ በሰላም ተጠናቋል፤ እስካሁንም ባሳለፍኩት የስራ ልምድ የትኛውም ፈረንጅ ከዚህ በተሻለ ቅልጥፍናም ሆነ ጥራት ሲሰራ አላየሁም" በማለት የምስክርነት መንፈስ ጭምር ያለበት መልእክት አስተላለፈች።

እንዚያ የስቃይ ሰዓታት አልፈው ቀዶ ጥገና ያለምንም እንከን በሰላም አለቀ። የቀዶ ጥገና ብቃት ሳይሆን አጠቃላይ ሲስተም ተፈትሾ አለፈ። እነሆ ሀገራችን በራሷ ልጆች በሀገሯ አፈር ላይ የመጀመሪያውን የልብ ቀዶ ጥገና በስኬት አጠናቀቀች። ታካሚያችን በፅኑ ታማሚ ክፍል ውስጥም ሰላማዊ ቆይታን አደረገች። በአምስተኛው ቀን ታካሚያችን በሰላም ወደቤቷ ገባች።

በመጀመሪያዋ ታካሚ ስቃይ ብዙ ስቃዮች "እፎይ!" አሉ። በዚህ አስፈሪ እና አስቸጋሪ ስሜት ያለፉ የባለሙያዎች ስቃይ የብዙ

ተከታይ ባለሙያዎች ስቃይ ተወገደ። ከአሁን በኋላ ቀጣይ ባለሙያዎቹ በዚህ አስፈሪ ስሜትና ጫና ውስጥ ሳያልፉ በቀጥታ ስራቸውን ብቻ ወደማሰብ ይገባሉ። እዚህ ይህ የመጀመሪያ ስቃይ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ስቃዮችን አስወገደ። ዛሬ ሰዎች ከስቃያቸው ለመዳን በምርጫቸው ከፈለጉ በሀገራቸው፣ ካሻቸው ወደ ሌላ ሀገር የመሄድ እድል አላቸው። ነገር ግን እንደከዚህ ቀደሙ ተገደው ምርጫ አጥተው አለመሆኑ በዚህች ስኬታማ ስራ ተበሰረ።

የሆስፒታሉን መስራች ዶ/ር በላይ አበጋዝን ጨምሮ ሁላችንም የሆስፒታሉ ሰራተኞች በደስታ ጮቤ ድሉን አጣጣምን። በአሜሪካ ሚኒያፖሊስ የሚገኘው friends of children heart fund of Ethiopia በኦፊሴላዊ ድህረገፁ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ የሀገር ልጆች የልብና ሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን በመጠቀም የልብ ቀዶ ጥገና መክፈቷን ዘገበ። ይህ ድርጅት በበጎ አድራጊ ቡድን መልክ በየጊዜው በዘመቻ መልክ እየመጡ ቀዶ ጥገና ከመስራት በሻገር አብዛኛውን በልብ ማዕከል የሚገኘውን የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን በመመልመል፣ ቀጥሎም ውጭ ሀገር ልኮ ያስተማረ ትልቅ ባለውለታ ድርጅት ነው። (4)

*****



ይህ የመጀመሪያ ስራ በምንም ምክንያት ባይሳካ ኖሮስ? በሀገራችን ላይ በልብ ቀዶ ጥገና ቀላል ሆነ ከባድ ምንም ሊከሰት እንደሚችል የመማርያ መጽሐፍቶችን ያትታል። እናማ በስብሰባው ላይ የተነሳው የልዩነት ሀሳብ በደምሳሳው ትክክል ነበር ይባላል። ስለዚህ ሌላ እድል ይሞከር የሚል ጀግና ይኖራል ብዬ አላስብም። እኔም የዚህ ቀዶ ጥገና አለመሳካት ብቻ ሳይሆን ለሰላሳ አመት በትምህርት ቤት ያጠናሁበትን ስራዬን ላጣ የምችልበት ሁኔታ ነበር። ለዚህም ነበር በዚህ አልፋና ኦሜጋዬ በሆነው የመጀመርያ ስራ ራሴን ለእርድ እንደቀረበ የአብረሃም በግ አድርጌ የማስበው የነበረው።

ይህች ፍንድቅድቅ ታካሚያችን መልኳም ቅላቷም ተመልሷል፡ እህል ጠልታ የነበረች ልጅ ዛሬ እንዳሻት አማርጣ መመገብ ችላለች። ደግሞ ብሎ ሰውነትዋ ያለ ቅጥ እንዳይወፍር በመጠንቀቅ ላይ ትገኛለች። በሰበብ አስባቡ እየተነሳ የሚነዘንዛት የራስ ምታት ጥሏት ከጠፋ ዓመታት ተቆጠሩ። ዛሬ ላይ ይህች ታካሚያችን በየዓመቱ የተሰራችበትን እለት ለመዘከር በሆስፒታሉ ተገኝታ ከሆስፒታሉ ሰራተኞች ጋር በመሆን ኬክ ትቆርሳለች። 5ተኛ ኬኳንም በሰላም ቆርሳለች። እነሆ ለሀምሳኛው ኬክ ቆረሳ በሰላም ያድርስሽ ብለን ተመኘን።



2/ምስል ፱፤ በሙሉ የሀገር ልጅ የተዋቀረው የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን በሀገራችን ታሪክ የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን (Heart lung machine, HLM) ማሽን በመጠቀም የመጀመርያ የተሰራውን የልብ ቀዶ ጥገና ሲሰራ የተነሳ ፎቶ (ሰኔ 5 2009 ዓ.ም)።





2/ምስል ፲፤ የአለም የደረሰበትን የልብ ቀዶ ጥገና ቴክኖሎጂዎችን ያሟላ የልብ ማዕከል በኢትዮጵያ የልብ ቀዶ ጥገና ክፍል በሙሉ የሀገር ልጅ በስራ ላይ ሆኖ ይታያል።

# 2

# ዓለምን ያስደመመው የልብ ውስጥ ዕጢ

በአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ አንዲት ገጠራማ መንደር ውስጥ የተወለደችው የ27 ዓመት ወጣቷ ሴት የአንድ ልጅ እናት ነበረች። ከ16 ወር በፊት የልጅ እናት የሆነችው ይህች ሴት ትሉ ትሉ መድከምና አተነፋፈሷ ራሷን እየሳተች በመቸገሯ ወደ ልብ ሕክምና ማዕከል ትላካለች።

የልብ አልትራሳውንድ ምርመራ ውጤት እንደሚያሳየው በቀኝ ልብ የታችኛው ክፍል ውስጥ ትልቅ እጢ በቅሎ ይታያል (RIGHT VENTRICULAR MASS ARISING FROM THE INTERVENTRICULAR SEPTUM። በመሆኑም ከቀኝ ልብ ወደ ሳንባ መውጫ የሚወስደውን



የደም ስርን በከፍተኛ ሁኔታ ዘግቶታል (RIGHT VENTRICULAR OUTFLOW TRACT OBSTRUCTION) ። በልብ ማዕከል ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ቆይታዬ በቀኝ ልብ የታችኛው ክፍል ውስጥ እንዲህ ዓይነት ዕጢ አጋጥሞኝ አያውቅም ነበር። በየሁት ነገር መገረም ተሰማኝ። ያስገረመኝ ጉዳይ ይህ ዕጢ በአንድ ሌሊት አልመጣም። ለብዙ ዓመታት አብሮ የነበረ ዕጢ መሆኑ ግልጽ ነው። ከታሪኳ እንደምንረዳው የአንድ ዓመት ከ4 ወር ህፃን ልጅ አላት፤ እንዴት ይህ ዕጢ አያለ በሰላም ተገላገለች? "ማርያም በሸልም አወጣቻት" ማለት ይህቺን ነው። ተጨማሪ ለቀዶ ጥገና የሚረዳን ምርመራ አደረግን። ለተሻለ አቀድና ዝግጅት ይበጃሉ ያልናቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉንም አጠናቀቅን። በቀዶ ጥገና ወቅት የልብ ምት መቋረጥ ቢከሰት በሆስፒታላችን ለጊዜው PACEMAKER ስለሌለ በትብሪው ይመረጣል የሚል ሀሳብ የነበረ ቢሆንም በቀዶ ጥገናችን ይህ ችግር ከተከሰተ በሁለት ሳምንት ውስጥ መገዛት እንደሚቻል አረጋገጥኩ። ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ ሊመጣ የሚችል ቢሆንም በዚህ ምክንያት እድሉን መከልከልና ህይወቷን ለአደጋ ማጋለጥ መሆኑን ተከራከርኩ። ቢቀጥል ይህ ችግር ቢመጣ ለሁለት ሳምንት ጊዜ የምንገዛበት ዘዴ በላለን በዚህ መሀል መግዛት እንደምንችል አመንኩ። በመጨረሻም ይህን ያልተለመደ የቀኝ ልብ የታችኛው ክፍል (RIGHT VENTRICULAR) ዕጢ ለመስራት ወሰንኩ።

የ1954ቱ በመጀመሪያው የ Henry Ford International sym-

posium of Cardiovascular Surgery ጉባኤ ላይ የተገኘው ዶ/ር Craford በዓለማችን የመጀመሪያ የተባለውን የልብ ውስጥ ዕጢ ማውጣቱን አሰወቀ። ከስዊዲን Stockholm የተገኘው ዶ/ር Craford የስዊዲኖች የልብ ቀዶ ጥገና ፈርጥ መሆኑን ታሪክ ያሳያል። በቀረበው ጥሁፍም የመጀመሪያውን የልብ ውስጥ እጢ ማውጣት የቻለው የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን የHEART LUNG MACHINE (HLM) በመጠቀም ነበር። ምንም እንኳን ከሁለት ዓመት በፊት Bahanson and Newman inflow inclusion technique (HLM ሳይኖር ማለት ነው) ተጠቅመው ከልብ ውስጥ ዕጢ ያወጡ የነበረ ቢሆንም በ24ኛው ቀን የዚህች ታካሚ ሕይወት በድንገት ሊያልፍ ችሏል።

የስዊድኖቹ የመጀመሪያ የልብ ቀዶ ጠጋኝ Professor Clarence Craford የመጀመሪያው የልብ ውስጥ እጢ ታካሚ የሆነችው ይህች የ40 ዓመት ሴት የግራ ሰውነት ክፍሏ እየደነዘዘ እና ብዥ ብዥ እያለባት ትቸገራ ነበር የመጣችው።

በወቅቱ የነበረው ብቸኛ የምርመራ ዓይነት (Angiogram) በቀጥታ መርፌውን ከግራ የጀርባ ክፍል ወደ Left atrium በመውጋት ዕጢውን ከቦታው ማወቅ ቻሉ። እናም የዚህችን ሴት የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን የHEART LUNG MACHINE (HLM)



በመጠቀምና ልብን በማቆም ከላይኛው የልብ ክፍል ዕጢውን በተሳካ ሁኔታ አወጡ። የዕጢው ምርመራ በፓቶሎጂ MYXOMA መሆኑ ተረጋገጠ። ለዓመታት ታካሚዋ በጥሩ ጤንነት ዘለቀች። እንግዲህ ይህ የስዊድኖች የመጀመሪያው የልብ ቀዶ ጥገና ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን የHEART LUNG MACHINE (HLM) በመጠቀም Clarence Craford የስዊድን የልብ ቀዶ ጥገና አብዮት ነው።

በወቅቱ የዚህ ታሪካዊ ቀዶ ጥገና የመጀመሪያ ረዳት (1st Assistant) የነበረው ሌላኛው የዓለማችን ፈርጥ የልብ ቀዶ ጠጋኝ Senning እንደፃፈው "በወቅቱ እጅግ ብዙ ቴክኖሎጂ ባልነበሩበትና ሳይንሱ አሁን ያለበት ደረጃ ባልደረሰበት ወቅት ይህ ቀዶ ጥገና ሲሰራ እጃቹን በፍጥነት የግራ የታችኛውን ልብ ክፍልን (LEFT VENTRICLE) በመያዝ ልብ እንዳይለጠጥና አየር ወደ ሠውነት እንዳይሔድ" መያዝ ነበረብኝ ይላል። (5,6)

ታዲያ ዛሬ ላይ የዚህች ወጣት ዕጢ ምን አዲስ አደረገው? ዋነኛ ምክንያቶቹ ይህ ዕጢ የበቀለው በላይኛው ሳይሆን በታችኛው የቀኝ ልብ ጡንቻ ላይ ሲሆን ሌላኛው የበቀለበት ቦታ የቀኝና የግራ ልብን በሚለየው በታችኛው ግድግዳ IVS ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ መሆኑ ነበር። በዚህም ምክንያት በቀዶ ጥገና ወቅት እና ከቀዶ ጥገና በኋላ

ብዙ የጎንዮሽ ችግር ሊፈጠሩ ይችላሉ። ሌላኛው ትልቁ ጥያቄ የዚህን ዕጢ ምንነት ከዚህ በላይ ከቀዶ ጥገና በፊት ለማወቅ አለመቻሉ ነው።

የሠው ልጆች በሥራ ገበታ ላይ የሚገጥማቸውን ፈተና በሙሉ በትምህርት ቤት ተምረው ይወጣሉ የሚል ዕምነት የለኝም። እኔም ብሆን ይህን ዓይነት ዕጢ በዓመት ከ 7000-8000 የልብ ቀዶ ጥገና ከሚሰራ ቤት ተምሬ እንኳን ልንሰራው ቀርቶ ሠምተነው አናውቅም ነበር። ነገር ግን ፅኑ ዕምነቴ ሁሉም በየሙያው የሚማረው ሁሉንም ማሸነፍ የሚችልበት ማሰቢያ መንገድና Basic Principle ነው ብዬ አምናለሁ።

በዚህ አጋጣሚ በሙያዬ የገጠመኙን የፕ/ር አስራት ወልደየስ ተሞክሮ ላንሳ። በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1970ዎች እኚህ የቀዶ ጥገና ሐኪም የልብ ቀዶ ጥገና ይሰሩ ነበር እየተባለ በስፋት ይነገራል። እርግጥ ነው በወቅቱ በሀገራችን የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን የHEART LUNG MACHINE (HLM) እንደሌለ እርግጥ ነው። ስለዚህ ልብንና ሣንባን አቁመው ልብን ከፍተው ቀዶ ጥገና እንዳልሰሩ እሙን ነው። ታዲያ ምን ነበር የሰሩት?

አሁን ላይ ከቶንሲል ሕመም ጋር ተያይዞ የሚመጣ የልብ በር መጥበብ በሀገራችንም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ሁሉ የተንሰራፋ የልብ በሽታ ነው። በምእራባውያን አለም ይህ በሽታ ሙሉ በሙሉ



በሚባል ደረጃ የተወገደ ሲሆን፤ በሀያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ ግን ዋነኛ የሚባል የልብ በሽታ ነበር። እስከ 1953 በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራ ማሽን ባልነበረበት ወቅት ዶ/ር ሮበርት ከትለር በ1929 በጎርጎሮሳውያን ካላንደር በግራ ጎን በመግባት ልብ ሳይቆም ሣንባም እየሰራ የHEART LUNG MACHINE (HLM) ጥቅም ላይ ሳይውል ጣትን በመጠቀም ብቻ ይህንን ሽልሽ ለማስፋት የመሞከር ስራ ለአለም አስተዋወቁ። ይኸም ቀዶ ጥገና Closed Mitral Valvotomy (CMV) ይባላል። በዚሁ ዘርፍ Robert Glover የተባለ የፊላደልፊያ ቀዶ ጠጋኝ በዚሁ በመጀመሪያ የ1954 የ Henry Ford International symposium of Cardiovascular Surgery ላይ በልብ በር ጥበት ላይ የሰራውን ስራ አቅርቦ ነበር። ባቀረበው ፁሁፍ 750 ታካሚዎች ላይ ከ1929 በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር አንስቶ የተሠራውን የጠበበ የልብ በርን የማስፋት ቀዶ ጥገና (finger fracture technique for mitral stenosis) ነበር።

ታዲያ ይህ ቀዶ ጥገና ነበር በሀገራችን በፕ/ር አስራት ወ/የስ በ1970ዎቹ ሲሰራ የነበረው። ይህ ቀዶ ጥገና በሀገራችን ሊሰራ የቻለው በዚህ ሙያ ሰልጥነው ሣይሆን ባላቸው የአጠቃላይ ቀዶ ጥገና እውቀት ተጠቅመው በሀገራችን በስፋት የተንሰራፋውን ይህንን ችግር ለመፍታት ባደረጉት የግል ጥረት ነው። እኔም እድለኛ ሆኜ በዚህ ሙያ የሠሩትን አንድ ታማሚ ከ42ዓመት በኋላ በ61 ዓመታቸው

አማኝቻቸው ነበር። ታድያ ይህን በድጋሚ የጠበበን የልብ በር የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን የHEART LUNG MACHINE (HLM) በመጠቀም በብረት ማስኪያ ሽልሽ ቀይረነዋል። የትውልድ የዱላ ቀባብሎሽ ይሉሃል እንዲህ ነው።

*****

የዚህ ያልተለመደ የቀኝ የታችኛው ልብ ክፍል ዕጢ ቀዶ ጥገና ተጀመረ። ደረት ከፍተን የደም ዝውውርን ለማሽን የመስጠት የመጀመሪያ ሂደት ተጠናቀቀ። በመቀጠል ልብ እና ሳንባን በማቆም የቀኝ የላይኛው የልብ ክፍል (Right atrium) ከፈትን። በዚህ በኩል ያለውን የልብ በር በመክፈት ዕጢውን ማየት ጀመርን። ድንጋጤዬ ጨመረ፤ ልብ ምቱም እንደዚያ፤ ተስፋ የምቆርጥ ስሜት እና የማንወጣው ትልቅ አደጋ ውስጥ መሆናችን ታወቀኝ። ምክንያቱ ደግሞ ዕጢው ከጠበኩት ውጭ ሆኖ ስላገኘሁት ነበር። ከጠበኩት ውጭ እጅግ ጠጣር በጣም ትልቅ እና ሰፊ መሰረት ላይ የተኛ በመሆኑ ነበር። እንዴት አድርጌ ነው ይህን ጉድ የማላቅቀው? ዕጢው ከቀኝ በር አንስቶ እስከ የቀኝ ልብ መውጫ በታውን ሞልቶታል። ደረትን ከፍተን፣ ልብን አቁመን ልብን ከከፈትን በኋላ እንዴት ብዬ በምን ሰበብ ላቋርጠው? "አላደርገውም" ስል ለራሴ ቃል ገባሁ። "ምንም ወደ ኋላ የለም፤ ወደፊት" አልኩት። የተሰማኝን



ስሜት ሳልደብቅ ለጠቅላላው የቀዶ ጥገናው አባላት አሳውቅኩ። እጅግ በጣም ረጅም ቀን እንደሚሆን፣ በሰላም የማጠናቀቃችን እድል ያነሰ እንደሆነ፣ በብዙ ችግር ውስጥ ልንወድቅ እንደምንችል ሲከፋም ታካሚያችንን በህይወት ይዘን ላንወጣ እንደምንችል አስረዳሁ። ሁሉም ሰው በድንጋጤ ውስጥ ወደቀ። ነገር ግን ተስፋ የመቁረጥ ስሜቱን ስላልወደዱት ሊያበረቱኝ ሞከሩ።

ዕጢውን በሙሉ ለማውጣት የቀኝ የታችኛው ክፍልንም መክፈት ግዴታ ነበረ። አንድ ጊዜ ከላይ፣ ሌላ ጊዜ ከታች እያደረግን ዕጢውን ከመሰረቱ ማላቀቅ ጀመርን። በአንዱ አቅጣጫ ሲቸግረን ወይም አደጋ የሚከሰት ሲመስለን በሌላ አቅጣጫ እያደረግን ለሰዓታት ታገልነው። ከሰዓታት ትግል በኋላ እንደ ሀልም እውን አልመስልህ እያለኝ ሙሉ በሙሉ አላቅቀን ማውጣት ቻልን።

ይህ በራሱ ትልቅ ስኬት ቢሆንም ስራው ግን ከማለቅ ገና ሩቅ ነበር። በተለይ የከፈትነውን የቀኝ የታችኛውን ልብ መዝጋት በራሱ አስፈሪና ትልቅ ቀዶ ጥገና ነበረ። ደረጃ በደረጃ የከፍትነውን ዘግተን ስንጨርስ ልብና ሳንባ በራሱ እንዲሰራ ለቀቅነው። የልብ ምት የተፈጥሮ ስልቱን የጠበቀና ያልተዛባ ነበር። አስደማሚ ውጤት፣ የተፈራው ሁሉ ሳይከሰት ቀረ። ብዙ የመድኃኒት እርዳታ ሳያሻት የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ ከሚሰራው የHEART LUNG MACHINE (HLM) በሰላም ተላቀቀች። የፈራናቸው ችግሮች በሙሉ ሳይከሰቱ ከ6 ሰዓት ቆይታ በኋላ ታካሚያችን ጽኑ ታማሚ ክፍል ደረሰች።

CamScanner

በሆስፒታላችን ሰላማዊ የአንድ ሳምንት ቆይታ አድርጋ ወደ ቤቷ ገባች። በቀዶጥገናው የወጣው ዕጢ በስነ ደዌዎች ሁሉ የናሙና ምርመራ ተካሄደበት። የምርመራውም ውጤት ሁላችንንም ያስደመመ ሆነ። የፓቶሎጂ ውጤቱም MATURE CYSTIC TERATOMA IN THE RIGHT VENTRICLE ይሰኛል።በቀላል ቃላት ሲቀመጥ የጥርስ፣የአንጎል፣የሳንባ፣የቆዳ እና የመሳሰሉት ሴሎች ያለበታቸው በልብ ውስጥ በቅለው ተገኝተዋል እንደማለት ነው። የዚህም የኦፕሬሽን ሂደት እና የናሙናው ውጤት በዓለማቀፍ መጽሔት ላይ ወጣ። በዚህ አይነት በታ፣ እድሜ እና ሁኔታ እንዲህ አይነት ዕጢ በዓለማችን ሁለተኛው ለመሆን በቃ።እነሆ ይህንኑ ጽሑፌን ተከትሎ ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት በአካል ተገኝቼ ጽሑፌን እንዳቀርብ ጥሪ ይጎርፍልኝ ጀመረ።





3/ምስል ሀ፤ በዚሁ ታሪካዊ ቀዶ ጥገና ወቅት ዕጢው በላሳሚ የሚያስለው እና በቀኝ የታችኛው የልብ ክፍል (right ventricle, attached on the interventricular septum) በቅሉ የነበረው እጢ በቀዶ ጥገና ከወጣ በኋላ።

# 4

# ልብ እየመታ ልብ ሲጠገን

በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ዛሬ የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራው ማሽን ያለስራ ጥጉን ይዞ ተቀምጧል። ያለወትሮው በተጠንቀቅ በሚባል ሁኔታ የሚገጠሙት መሣሪያዎች ተገጥመውለታል። ከቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ በ30 ሜትር ርቀት ላይ ይታያል። የልብ የቀዶ ጥገና ሰመመን ሰጪ ሐኪሞች ከወትሮው በተለየ መልኩ ሁለት አንጋፋና ልምድ ያላቸው እየተጋገዙ የታካሚውን ሁኔታ በከፍተኛ አትኩሮት፣ ሰከንድ በሰከንድ፣ ደቂቃ በደቂቃ፣ እየተከታተሉ እንደሁኔታው መልስ ይሰጣሉ። ያለወትሮ ፊታቸው ወርዛቷል፤ አይናቸው ላይ መፍጠጥ ይስተዋላል።

እኔም በሀገራችን ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ልብ ሳይቆም፣ ሳንባ



ሳይቆም፣ ልብ እየመታ፣ የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን መጠቀም ሣይስፈልግ፣ የሚሰራውን የልብ የደም ስሮችን የመክፈት ቀዶ ጥገና (off pump coronary artery bypass graft) መሪ ቀዶ ጠጋኝ ሆኜ እየመራሁ ነው። ከፊት ለፊቴ ያለው ረዳት ቀዶ ጠጋኝ አይቶ በማያውቀው ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ከሁኔታው መረዳት አያዳግትም፡ ልብ እየሮጠ ይህንን የ1 ሚ.ሜ ቅጥነት ያለውን የደም ቧንቧ ላይ ቀዶ ጥገና ሲያግዝ (assistant surgeon) የመጀመሪያው በመሆኑ ግር ብሎት ነበር። ለመማር ጥረት በማድረግ እና በከፍተኛ ማገዝ ስሜት ውስጥ ሆኖ የምትሮጠውን ልብ አደብ ለማስገዛት ይውተረተራል።

በቀዶ ጥገናው ላይ አብራን የቆመችው ነርስ በቶሎ ቶሎ እና በትኩረት ሳይቋረጥ የምናዘውን ትዕዛዝ ለመፈፀም በጭንቀት ውስጥ ሆና ትከውናለች።

ክፍሉ ውስጥ ከሠመመን መሳሪያዎች፣ ደም ከሚመጡ ማሽኖችና አልፎ አልፎ እኔ ከማቀርባቸው ጥያቄዎች ውጪ፣ ፍፁም ፀጥታ ሰፍኖበታል።

ዋና እና ትልቅ የሚባለው የልብ የደም ቧንቧ (left anterior descending artery, LAD) ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ተዘግቶ ነበር። ከተዘጋበት ቦታ አልፈን አዲስ የደም ስር ለመትከል የሚያገለግለውን

LIMA (Left Internal mammay artery) ከደረት ጡት ስር በመጀመሪያ ወስደን ጨረስን። ቀጥሎም ይህንን የደም ቧንቧ ከሚዘጋበት አልፈን የመትከል ሂደት (Distal anastomosis) ተጀመረ።

እንግዲህ ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር ያለው እዚህ ጋ ነውና ጭንቀታችንም የበዛ ነበር። ከ3.5 እጥፍ በላይ አጉልቶ በሚያሳየው መነፅሬ (loop) እየተረዳሁ ግንባሬ ላይ ሆኖ በሚንቦገቦገው ብርሃን እየታገዝኩ ይህንን ማይክሮ ቀዶ ጥገና በከፍተኛ ጥንቃቄ ለመከወን እንጥራለን። ከሚረጨው ልብና ከሚደማው ደም ጋር በረዳት ሀኪሙና ከጎኔ በቆመችው ነርስ እየታገዝኩ የመጨረሻውን ምዕራፍ እና ዋነኛውን ለቀዶ ጥገና ክፍል ለመስራት እየታገልን ነው። ይሳካ ይሆን?

በዓለማችን በብዛት ከሚሰሩ ቀዶ ጥገናዎ በግንባር ቀደምነት የሚጠራው ይኸው የደም ስርን ነቅሎ ወይም አዘዋውሮ በተዘጋው የልብ የደም ስር ላይ መትከል (Coronary Artery Bypass, CABG) ቀዶ ጥገና ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በከፍተኛ ሁኔታ እያሽቆለቆለ ይገኛል። ምክንያቱ ደግሞ ያለ ቀዶ ጥገና ደረት መክፈት ሳያስፈልግ በፍርንትት በኩል በሚላክ ሽቦ በቪዲዮ እየታዩ የተዘጉ የልብ የደም ቧንቧዎችን መክፈት እየተለመደ በመምጣቱ ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ ቴክኖሎጂ አቅም በላይ የሚሆንበት ሁኔታ ሲከሰት ወደ ቀዶ ጥገና መግባት የግድ ይሆናል። (7)



የእኛም የዛሬ ታካሚ እና እጣ ፈንታ ወደ ቀዶ ጥገና መሄድ እንዲሆን እጣ ፈንታው የሆነው በጋጠመው ሁኔታ ነበር። የተዘጋው የደም ቧንቧ ለዋናው የልብ ጡንቻ ክፍል ደም የሚያቀርበው የደም ቧንቧ ነበር። ከዚህም በሻገር ይህንን ጥናት ለማድረግ የሚደረገው የCoronary Artery Angiogram (CAG) በወቅቱ በበቂ ሁኔታ ለማድረግ ያልተቻለበት ሁኔታ ተፈጠረ። ምክንያቱ ደግሞ የደም ስሮችን ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች በተለየ እንዲያሳይ የሚሰጠው የ Contrast መድኃኒት በታካሚው ላይ አለርጂ ፈጠረ። በመቀጠል በሂደቱ ላይ እያለ የታካሚው ሕይወት በተደጋጋሚ አደጋ ላይ ወደቀ።

ስለዚህም ችግሩን ከማወቅ በሻገር የተዘጋውን የደም ቧንቧ ለመክፈት የሚያስችል ስራ መስራት አልተቻለም። በመሆኑም የመጨረሻው መፍትሔው የልብ ቀዶ ጥገና እንዲሆን ተደረገ።

ይህን የተዘጋ አንድ የደም ቧንቧ፤ ነገር ግን ዋና የሚባለውን የደም ስር የቀዶ ጥገና ሂደት በሁለት መንገድ መከወን ይቻላል። አንደኛው መንገድ ልብና ሳንባ ሳይቆም ልብ እየመታ (off pump coronary artery bypass graft) ሲሆን፤ ሁለተኛው መንገድ ልብ እና ሣንባ ቆሞ የሚሰራው ነው (on pump coronary artery bypass graft)። ነገር ግን ይህንን ቀዶ ጥገና ልብ እየመታ ቢሰራ እና ውጤቱ ያማረ ከሆነ ልብ ቆሞ ከሚሰራ ቀዶ ጥገና የሚመረጥበት ብዙ ጥቅሞች ነበሩት። ሲቀጥልም እንዲህ ዓይነት ወጣትና ሌሎች ብዙ ተጓዳኝ በሽታ

የሌሉበት የተመቻቸ ታካሚ ማግኘት ከባድ ነበር። እናም ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ደህና ዓይነቱን ቀዶ ጥገና ልብና ሳንባ ሳይቆም ልብ እየመታ ለማድረግ (off pump coronary artery bypass graft) ሰዓቱ አሁን ነው ብለን ወሰንን።

እለቱ አርብ ነበር። በተለምዶ ዋናው መምህራችን አርብ ከሰአት ጀምሮ ለእረፍት ወደ ትውልድ አገሩ ይሄዳል ነበር። ቅዳሜና እሁድን በዚያው አረፍት አድርጎ ሰኞ በጠዋት ይገኝ ነበር። ይሁን እንጂ ፕሮፌሰራችን በሰአት መጣበብ ምክንያት ያልጨረሰው አንድ ቀዶ ጥገና ቀርቶ ነበርና ዋና ረዳት ለነበረው ሀኪም በአደራ እንዲሰራ እድል ይሰጠዋል። እና በዚህ እለት ሁለተኛው የዶ/ር PV. Rao ረዳት የሆነውና በልብ ቀዶ ጥገና ለ7 ዓመት ያገለግል የነበረው ሐኪም በዕለቱ አንድ ማንነቱን የሚያስመሰክርበት ትልቅ እድል ተበረከተለት። በነገራችን ላይ በህክምና ሙያ እንደዚህ ያሉ ወርቃማ እድሎችን በብቃት እና በስኬት ማሳየት ዋነኛ የዕድገት መሰላል ነው።

በዕለቱም እኔ የዚህ ሐኪም ረዳት ሆኜ ተሰየምኩ። ምንም እንኳ ትልቁ መምህራችን (Dr. Pv Rao) በሌሎች የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ የነበሩት ሲኒየር መምህሮች ችግር ከገጠመው እንዲረዱት የነገሩ ቢሆንም ለዚህ ሀኪም ግን "ትሰራዋለህ፤ ይህንን መስራት አያቅትህም" ነበር የተባለው። በዚሁ ቀን ለዚሁ ሐኪም እንዲሰራ የተሰጠው ቀዶ ጥገና ዛሬ ልክ እኔ በሀገሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረኩት ዓይነት ቀዶ ጥገና



ሲሆን ልብ እየመታ አንድ የደም ቧንቧን ማስከፈት Bypass ማድረግ ነበር።

ስለዚህም በተለምዶ አርብ ቀን በዚህ የቀዶ ጥገና ክፍላችን ውስጥ ሁለት ቀዶ ጥገና የሚሰራ ሲሆን አንዱን ቀዶ ጥገና እስከ እኩለ ቀን ዋናው ፕሮፌሰራችን ይጨርሳል። ሁለተኛው ቀዶ ጥገናም በስሩ ለሚገኙት ረዳት የልብ ቀዶ ጠጋኞች ይተውላቸውና ይሔዳል። እነዚህም ረዳቶች ከደመወዛቸው በላይ ደስታ የሚሰጣቸው ይህንን የተሰጣቸው ኃላፊነት በሰላምና በድል ማጠናቀቅ ነው። እንዲህም እንዲያ እያሉ ወደ ዋና የልብ ቀዶ ጠጋኝነት ያድጋሉ።

የምሽት ቀዶ ጥገና ነበርና ድካምም ጀማምሮን ነበር። ይህ ቀዶ ጥገና በባህሪው ከፍተኛ መረጋጋትን ትኩረትና የአዕምሮ ብስለት (Calm, Cool and Composure) የሚጠይቅ ነው። ቀዶ ጥገናው በፍፁም ሊያልቅ አልቻለም። እናም ምሽቱ በጣም ሲገፋ፤ አደራ የተቀበሉ መምህሮች ወደ እኛ ክፍል ጎራ ማለት ጀመሩ። እናም "ምነው ችግር አለ እንዴ" አሉ ። ጥሩ ሁኔታም እንዳልነበረ ሲረዱ እገዛ አደረጉልን። ከዚያም በሻገር ልብ እየመታ ተጀምሮ የነበረው ቀዶ ጥገና ችግር ውስጥ በመግባቱ ልብና ሣምባ ቆሞ እንዲሰራ ተወሰነ።

እናም ይህን ፈተና ማለፍ ያልቻለው ሐኪም እነሆ ዛሬም ድረስ ለ 11ዓመታት አጋዥ የልብ ቀዶ ጠጋኝ (Assistant Cardiac Surgeon) ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል።

CamScanner

ከ1960-1970 ብዙ የተሳካ የልብ ቀዶ ጥገና የተካሔደበት ዘመን ነው። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ልብ እየመታ የተሰራው ቀዶ ጥገና ሆኖ ይጠቀሳል።

በዓለማችን በአሁኑ ሰዓት በቀዶ ጥጋኞች ዘንድ ልብ እየመታ (Off pump CABG) እና ልብና ሣንባን አቁሞ On Pump CABG በሚሰሩት ቀዶ ጥገናዎች ዙርያ የተለያየ አመለካከት አለ። ለምሳሌ በአሜሪካ 80% የልብን የደም ስሮች የመክፈት ቀዶ ጥገናዎች (CABG) ልብና ሣንባን አቁሞ (On Pump CABG የሚሰራ ሲሆን 20% ደግሞ ልብ እየመታ (Off pump CABG) የሚሰራ ነው። በሕንድ ደግሞ (70% - ልብ እየመታ (Off pump CABG) 30% ልብ እና ሣንባ ቆሞ የሚሰራ ነው። ለዚህም የሚያጋጩትን ምክንያት እንጥቀስ ቢባል ከአንድ መጽሐፍ በላይ ቦታ ስለሚፈልግ ለጊዜው ብናልፈውም ሁሉም የራሱ የሆነ በቂ ምክንያት እንዳለው ማወቅ ያስፈልጋል።

የተጀመረ ነገር ያልቃልና በብዙ ውጥረት ውስጥ ሆነን እነሆ ደስ ብሎን አስጨናቂውና ዋናው የቀዶ ጥገና ስራ በሰላም ጨረስን። እነሆ ከሁለት ሰዓት በኋላ ሁሉም ሰው በተረጋጋ መንፈስ መተንፈስ ጀመረ። መሳቅ፣ ማውራት፣ ተጀመረ። ዋናው የቀዶ ጥገና ክፍል ከለቀ በኋላ ቀጣዩ ሂደት ገብቶ ነበር። እናም እየተሳሳቅን ደስ እያለን ቀሪውን ቀዶ ጥገና ሰርተን ጨረስን።



ምንም እንኳን በፅኑ ታማሚ ክፍል ውስጥ ቀላል የማይባል ጊዜ ቢያሳልፍም በትጋት ተወጣነው። እናም በቅርብ ጊዜ የአንድ ልጅ አባት የነበረውን ታካሚያችንን ከአራስ ሚስቱ ጋር በሰላም ወደ ቤቱ መሸኘት ቻልን።

ዛሬ ከአንድ ዓመት በኋላ ከዚሁ በ40ዎቹ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ጎልማሳ ጋር ተደዋወልን። ምክንያቱ ደግሞ ወቅቱ የኮቪድ-19 ዓለምን ያሸበረበት ነውና ብዙ ታካሚዎቼ ጋር በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ብዙ ነገሮችን በስልክ እንከታተል ነበር ። እናም በሀዘን ተጎድቶ በተሰበረ ስሜት ውስጥ ሆኖ ሲያወራኝ "ምነው?" አልኩት። በአንድ ሳምንት ብቻ አባት እና እህቱን በሞት መነጠቁን ነገረኝ። በሆስፒታል ውስጥ እሱን ህይወት ለማትረፍ ሲረበረቡ አውቃቸው ነበርና እጅግ አዘንኩኝ። ከዓመት በፊት የዚህ ታካሚ ሕይወት በቋፍ ነበረች፤ የታሰበውና የተፈራው ሣይሆን ያልታሰበው ተከሰተ።

CamScanner



ፋምየፈ ሀ/ በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን ልብ እየመታ የልብ የደም ስርን መከፈት (off pump coronary artery bypass graft, CABG) የተሳተፈው የሀገር ልጅ ከድል በኋላ ለማስታወሻ ኬክ በመቁረስ የተነሳው ፎቶ። የልብ ማዕከል በኢትዮጵያ (2012 ዓ.ም)።



# 5

## የሮይተርሱ ጋዜጠኛ

በአሜሪካ ኒውዮርክ የሀኪሞች ማህበር ምክትል ፕሬዝዳንት የሆነው ሀኪም በቀጥታ ስልክ እያናገረኝ ነው። የሚያናግረኝ በአማርኛ ሲሆን ኢትዮጵያ ተወልዶ ያደገ ጉምቱ ሀኪም ነበር። የሚያናግረኝ ደግሞ በእድሜ ስለገፉት የ90 አመት የእድሜ ባለፀጋ ስለሆኑት አባቱ ነበር። ዛሬ አባቱ የልብ የደም ስሮቻቸው ተዘግተው የልብ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው ተነግሯቸው ነበር።

ከስምንት ዓመት ገደማ በፊት በአሜሪካ ሳሉ እንዲሁ የልብ የደም ስሮቻቸው ተዘግተው ያለ ቀዶ ጥገና በፍረንትት በሚገባ ሽቦ የልብ የደም ስሮቻቸው መከፈት ተችሎ ነበር። ዛሬ ላይ የደም ስሮቻቸው ደረጃ ተሻግረው እና ከፋኛ ጠበው መፍትሄው ቀዶ ጥገና ብቻ ሆኗል።

ታድያ በ90 አመት እንዴት ሊሆንላቸው? ሲቀጥል የልብ ቀዶ ጥገና፤ ከልብም ደም ስሮችን የሚከፈት ባይፓስ (coronary artery by-pass graft surgery) ቀዶ ጥገና ይሰጥ ይሆን?

*****

እድሜያቸው ከሰማንያ አመት በላይ በሆኑ በዚሁ የልብ የደም ስር መዘጋት (coronary artery disease) በገጠማቸው ላይ ቀዶ ጥገናው ተገቢ ነው ወይስ በዝምታ ሞታቸውን መፍቀድ ይገባናል? በማለት የሚጠይቀው በኢስታንቡል ቱርክ በአዘንና ጓደኞቹ የተሰራ አንድ ጥናት እንዲህ ይላል። ከ 2002-2011 በጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር በ101 እድሜያቸው ከ80 በላይ በሆኑ ታካሚዎች ላይ ይህ ቀዶ ጥገና ተካሂዷል። በውጤቱም ቀዶ ጥገናው ከተሰራላቸው በኋላ 91% በአንድ አመት፤ 83% በሦስት ዓመት እና 69% በአምስት ዓመት በተሻለ ህይወት እንዳሉ ያሳያል። በመቀጠልም "ቀዶ ጥገናው በተሰራ 30 ቀን ውስጥ 17% ሕይወታቸውን አጥተዋል" ይላል። በማጠቃለያውም የሰው ልጆች ምንም እንኳን እድሜያቸው ከ80 በላይ ቢሆንም በዚህ ቀዶ ጥገና ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በግልፅ ያስቀምጣል።



አሮጌውን አመት አጠናቀን አዲሱን ዘመን ለመቀበል ሽር ጉድ በሚባልበት ሽርፍራፊ እምከቱ ቀኖች ውስጥ ነበርን። ከአርባ አመት በላይ በሮይተርስ ጋዜጠኝነት ምስራቅ አፍሪካን በሙሉ አክለው ያገለገሉት የዛሬው የ90 አመት የእድሜ ባለፀጋ ጋዜጠኛ በአንድ የልብ ሕክምና ሆስፒታል በፅኑ ታማሚ ሕክምና ክፍል ውስጥ ተኝተዋል። ከተደረገላቸው የልብ የደም ስር ምርመራ (coronary angiography) ቀዶ ጥገና ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ተነገራቸው። እኔም ዛሬ በዚህ ሆስፒታል የተጠራሁት እና የተገኘሁት ይህ ቀዶ ጥገና በሀገራችን ማሰብ ይቻል እንደሆነ ልጠየቅ ነበር።

በአልጋቸው ዙርያ በፍቅርና በስስት የሚያዩዋቸው ቤተሰቦች ከበዋቸዋል። ከሀገር ውስጥም ከውጪም የመጡ ቤተሰቦች በዚህንም በስንብት በሚመስል መልክ ከበው ዓይን ዓይናቸውን ይመለከቱ ነበር።የተደላደለ ሕይወት ያሳለፈ ቤተሰብ ስለመሆናቸው ከአጥንታቸው ስፋት፣ ከቁመታቸው ርዝመት እና ከፊታቸው ወዝ መገመት አያዳግትም ነበር። ታድያ ከእነዚህ ጎሊያዶን ከሚያከክሉ ሰዎች መካከል የወንድማቸውን ሕይወት ሊታደግ ይችላል የተባልኩት የዳዊትን ጠጠር የማክለው ሀኪም ድንገት ብቅ አልኩኝ።

በቦታው የተገኘሁት የሕክምና ምርመራውን አይቼና አጥንቼ እንዲሁም የሕክምና ታሪካቸውን ሙሉ በሙሉ በከማቸው ሀኪም አማካኝነት ሪፖርት ካዳመጥኩ በኋላ ነበር። በልጅነቴ ይሁን በአካላቴ

አለመግባባቶ የተገረሙ የሚመስሉት ቤተሰቦች በትኩረት ይመለከቱኝ ነበር። የእኔ የትኩረት አቅጣጫ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ያረፈው የየካቲት 12ን የአርበኞች በዓልን የሚያከብሩትን አዛውንቶችን የሚያስታውሱን የሚመስሉት ታካሚ የ90 ዓመት አዛውንት ላይ ነበር። ችምችም ብሎ የቀይ ዳማ ፊታቸው ላይ የተኛው ነጭ ፂማቸው ልዩ ግርማ ሞገስ አላብሷቸዋል።

ውሳኔዬን አሳወቅኳቸው። ለመስራት የሚያግደን ምንም ነገር እንዳላየሁ ነገርኳቸው። እድሜን ከሰጡኝ ቆዳ ጥገናውን መስራት እንደምችል አስረዳኋቸው። ከልባቸው ውጪ በለው የተቀረው ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎች አሰራር ደህንነተኛ ነበሩ። እናም "እድሜ ማስፈራሪያ ሳይሆን ቁጥር ብቻ ነው" (age is just a number) የሚለውን የትምህርታችንን ብሂል በማከል ፈርጠም ብዬ አስረዳኋቸው። ውሳኔያቸውንም በቤተሰብ መክረው ሲጨርሱ እንዲያሳውቁኝ ነግሬ ተለየሁ።

የአዲሱን ዓመት እንቁጣጣሽ በዓል ባከበርን ማግስት በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ግዛቶች የሚኖሩ የታካሚው አዛውንት ቤተሰቦች በስልክ አጣደፉኝ። የጥያቄያቸው ዋንኛ አቅጣጫ በጥርጣሬ ላይ ያተኮረ ነበር። "እውን እንደዚህ አይነት ቆዳ ጥገና በኢትዮጵያ ይሰጣል? በዚህ ዕድሜስ ቆዳ ጥገናው ውጤታማ ሊሆን የሚችልበት እድል አለ ወይ? ይህንን ለመከወን የሚያስችል እውቀትና አቅም አለ ወይ?



የሚል መንፈስ የነበራቸው ነበሩ። እንደዚህ ያሉ ጫናዎች በሚሰራው ሀኪም በራስ መተማመን ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉት በጎ ያልሆነ አሉታዊ ጎን እንዳላቸው እርግጥ ነው። ነገር ግን የቤተሰብን በስራችን ላይ መተማመንን ለማሳደር ሲባል ያለመታከት ሁሉንም የስልክ ጥሪ ረጅም ጊዜ እየወሰድኩ አስረዳ ነበር።

በሀብት ሀብት ያላነሱቸው፣ ከእውቀት፣ እውቀት ያላነሱቸው፣ ከሀገርም የቱንም ሀገር ቪዛ ያላጡት እኚህ ቤተሰቦች የእድሜ ጠገብ አባታቸውን ሕይወት እንድንታደግ ለሀገር በቀል እውቀት አሳልፈው ሰጡ። እኛም ኃላፊነታችንን ተረክበን ለቆዳ ጥገናው የሚደረገውን ዝግጅት አፋጠንነው።

*****

ረፋድ አካባቢ የተጀመረው የዚህ ቆዳ ጥገና ዝግጅት እኩለ ቀን ላይ ተጠናቆ ቆዳ ጥገና ልንጀምር ሆነ። ነገር ግን አንድ አስደንጋጭ እና ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ። ከምንታጠቃቸው መሳሪያዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛ የሚባለው የማጉሊያ መነፅር (loop) በቆዳ ጥገና ክፍሉ ውስጥ አልነበረም። ይህ አይነቱ ቆዳ ጥገና ደግሞ ያለዚህ መነፅር የማይሞከር ነበር። ታድያ የት ረሳሁት? ሳምንቱን ሁሉ

ሀሳቤና ጭንቀቴ ሙሉ በሙሉ የወሰደው ይህን ኦፕሬሽን በስኬት እንድናከናውን የሚረዳንን አያግዳጉዱን ጥቃቅን ጉዳዮችን ያለምንም እንከን ለመፈፀም በብዛቱ ከርሜአለሁ። ይሁን እንጂ ማንኛውንም ቀዶ ጥገና በማንኛውም ሆስፒታል ስሰራ በጭንቅላቴ ላይ የማስቀምጥ መነፀር ግን ተለይቶኝ አያውቅም ነበር። በሌሎች ሀገሮች የናወዘው አዕምሮዬ ታዳይ ምክሬን በአገሬኛው ሆስፒታል ረስቼው ኖሯል። ሀፍረቱን ተከናንቤ ዶክተሩን ቀዶሬ ሹልክ ብዬ ወጥቼ ወደ መኪናዬ ሄድሁ። መኪናዬን በፍጥነት አያሽከረከርኩኝ ከስቀመጥኩበት ሆስፒታል በፍጥነት ደርሼ መነፀሬን ይዤ ተመለስኩኝ።

እውነቱን ለመናገር በቀዶ ጥገናው ወቅት የገጠመህ ከበድ ፈተና ምን ነበር ብትሉኝ ከዚህ ውጪ ትዝ የሚለኝ ጉዳይ አልነበረም። የ90 አመት አዛውንት በመሆናቸው ሁለቱንም የተዘጉትን የደም ስሮች ያለፍነው በእግራቸው በጋበድነው የደም ስር (saphenous vein) ነበር። ብዙ የመድሃኒት እርዳታ ሳያሻቸው በሰላም ከቀዶ ጥገና ወጥተው ፅኑ ታማሚ ክፍል (ICU) ደረሱ።

በአምስተኛውና በስድስተኛው ቀን እኚህ የዘጠና ዓመት አዛውንት ከዚህ የልብ ቀዶ ጥገና በኋላ ከአልጋ ተነስተው በሆስፒታሉ ወለል ላይ ሲሄዱ በመላከት ልዩ ደስታ ፈጠረብኝ። በየዕለቱ በማደርገው ጉብኝት ከዕድሜ ባለፀጋው የሮይተርስ ጋዜጠኛ ጋር ማውራት ያስደስተኝ ነበር። በዚህ ወቅት ነበር ታዲያ አምን ይህን ቀዶ ጥገና ማከናወ



እንደፈለጉና ለመኖር እንደሚችሉ ያጫወቱኝ። ለፍፃሜ ያልደረሰው ነገር ግን ብዙ ያራመዱትን መጽሐፍ መጨረስ ቀሪ የህይወታቸው ዓላማ ነገርና ነው።

በሀገራቸው እንዲህ አይነቱ ስራ ያልጠበቁት ቤተሰቦቻቸውም በዚህ ስራ ለተሳተፉ ሁሉ ስጦታ አበረከቱ። ለእኔም ዘመናዊ የእጅ ሰዓት (APPLE WATCH) ተበረከተልኝ።

እኚህ ቀደምት የሮይተርስ ጋዜጠኛ እና የዕድሜ ባለፀጋ ከዚያ በኋላ በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያ እየቀረቡ ልምዳቸውን ሲያካፍሉ ይታያሉ። በውጭ ሀገር የሚኖሩ ቤተሰቦቻቸውም በየሚዲያው አባታቸውን ባዩ ቁጥር ሊንኩን ለታች በማድረግ ምስጋና ያቀርቡ ነበር።



**3.5X-EF**

5/ምስል ሀ፤ ከዚህ ቀዶ ጥገና አስቀድሞ የረሳሁት የማጉያ የልብ ቀዶ ጥገና መነፅር (LOOPP) ከላይ የምትመለከቱት ሲሆን 3.5 ጊዜ አጥፍ በማጉላት እጅግ ቀጫጩን የሆኑት የልብ የደም ስር ላይ ያለችግር ለመስራት ይረዳል።



# 6

## ታሪክ በአጋጣሚ

የዛሬው እሁድ ጠዋት የቤተሰቤ ቀን ሊሆን አልቻለም። ምክንያቱ ደግሞ በጠዋት ካለብኝ የቦርድ ስብሰባ ባሻገር እኩለ ቀን ላይ ቀን የቆረጥኩለት እስከዛሬ ያልደፈርኩት ቀዶ ጥገና ለመስራት ከተማችን ውስጥ ከሚገኘው ከአንደኛው የግል የልብ ሆስፒታል እቅዳችን ስለነበር ነው። ሌሊት ላይ በህልም ዓለም ከእንቅልፌ ያባነነኝ የመኪናዬ ጎማ ፍንዳታ ምናልባት በቀኑ ስራዬ ላይ ትርጉም ይኖረው ይሆን? እስከዛሬ በኖርኩት ኑሮ አንድም ጊዜ ህልምና ኑሮዬን ለማስተዋል ተጨንቄ አላውቅም። ስለዚህም ከበለፈው የህልም የመፍታት ተሞክሮ የምለው ባይኖረኝም ዛሬ ግን በህልሜ ያየሁት የመኪናዬ ጎማ አተነፋፈስ

ከቆየር በኋላ በሀገሬ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ከምደፍረው ሀይወት ጋር ተዘመደብኝ። ታደያ ከ300 በላይ የልብ ቀዶ ጥገና ከሰሩ በኋላ እንዲህ በሀፊም በኋላ እየመጣ የተጨነቅኩበት ምክንያት ምን ይሆን?

*****

ከሁለት ሳምንት በፊት ከሀዋሳ በረፈራል ወረቀት ወደዚሁ በትርፍ ጊዜ ወደ ምሰራበት የግል ሆስፒታል የመጡት በ60ዎቹ መጀመሪያ እድሜ ተርታ የሚሰለፉ የቤተሰብ ሃላፊ አባት ነበሩ። ወደእኛ ያስመጣቸው የልብ ጉዳይ የውትሮ እንቅስቃሴያቸውን ከማገታቱም በሻገር ስውር እያደረገ ያዘራቸዋል፤ ይጥላቸዋል። ምክንያቱ ደግሞ አንደኛው የግራ ልብ በር (aortic valve) እጅግ በመጥበቡ ነበር፡፡ ይህንን አንድ የልብ በር መቀየር የእለት ተእለት (routine) የምለው አይነት ቀዶ ጥገና ነበርና የወትሮውን ዝግጅት እንዲጀመር አድርጌ ወደቀጣይ ስራዬ ገባሁ።

ለዚህ ቀዶ ጥገና ከሚደረጉ ዝግጅቶች ውስጥ የልብን የደም ስሮች የምናይበት ምርመራ (coronary angiogram) ግዴታ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ እድሜያቸው ገፋ ባሉ ሰዎች ላይ እንዚህ የደም ስሮች ሊዘጉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ነው። ነገር ግን በእራሳ



ዓመት ጥቂት ልምዴ ለቫልቭ ቀዶ ጥገና ዝግጅት የምናየው ይህ ምርመራ የተዘጋ የደም ስር አሳይቶኝ አያውቅም ነበር፡፡

ይህ በሆነ በአራተኛው ቀን ከዚሁ በእረፍት ሰዓቴ ከምሰራበት ከዚሁ ሆስፒታል ደወሉልኝ። በተደረገላቸው የልብን የደም ስሮች ምርመራ (coronary angiogram) አንደኛው የልብ የደም ስር ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ መዘጋቱ (a near complete stenosis of left anterior descending artery) ተነገረኝ፡፡ የአነጋገራቸው እንደምታ በዚህ ሀገር እነዚህ ሁለቱን በአንድነት ስትከውን አናውቅምና ወደሌላ የመፍትሄ ሀሳብ እናፈላልግ አይነት እንደምታ ይመስል ነበር፡፡ እርግጥ ነው በሀገሬ ምድር ሁለቱንም አይነት ቀዶ ጥገና ማለትም የልብን የደም ስሮች አልፎ መተካት (coronary artery bypass graft, CABG) በ33 ታካሚዎች ላይ በከኒድም፣ እንዲሁም የልብ በሮች ቀዶ ጥገና (valve surgeries) ከ200 ጊዜ በላይ ብሰራም በአንድ ታካሚ ላይ እነዚህን ሁለት ትልቅ ቀዶ ጥገናዎችን አከናውኜ አላውቅም ነበር፡፡

ከነጠር እብረዋቸው የመጡትም ከአዲስ አበባም ያሉ ዘመዶች ሁሉም በሉበት በምርመራ ወቅት ስለጋጠመን አዲስ ተጨማሪ ችግር በዝርዝር አስረዳኋቸው። በመቀጠልም ቀዶ ጥገናው በዚህ ምክንያት ቀድሞ ከታሰበው የላቀ አደጋ ሊኖረው እንደሚችልም ጭምር ለሙሉ ቤተሰብ አብራራሁ፡፡ በሙሉ ቤተሰብ ድንጋጤ ሆነ፡፡ በስተእርጅና

እንዲህ ያሉ ሁለት ትልልቅ ቀዶ ጥገናዎች እንዴት ይችሉት ይሆን? ሆኖም እነዚህ ሁለት ከባባድ ችግሮች በማንኛውም ጊዜ ህይወታቸውን ሊቀጥፉ እንደሚችሉ እሙን ነው። ቀዶ ጥገናቸውን ደግሞ ከተሳካ የተሻሉ አድሚ ከጥሩ የኑሮ ጥራት ጋር ይኖራቸዋል።

*****

ዶ/ር Fausto Biancari እና ባልደረቦቹ በ176 የግራ ልብ መውጫ በር ቅየራ (aortic valve replacement) ከልብን የደም ስሮች አልፎ መተከት (coronary artery bypass graft, CABG) ጋር ሲጣመርና ለብቻው ሲሰራ ስለሚመጣው የውጤት ልዩነት በ2013 ባሳተሙት ፅሁፍ ላይ በስፋት አትተዋል።

እህ ጽሑፍ "የግራ ልብ መውጫ በር ቅየራ (aortic valve replacement) ለብቻው ሲሰራ ቀዶ ጥገናው በተሰራ በ30 ቀን ውስጥ የመሞት እድል 3.3% ሲሆን የደም ስሮች አልፎ መተከት (coronary artery bypass graft, CABG) ጋር ሲጣመር በ30 ቀን ውስጥ የመሞት እድል 4.3% ነው" ይላል። በመቀጠልም "ስትሮክ የመከሰቱ እድል ከ1.7% ወደ 2.1% ሁለቱን በሚያጣምረው ቀዶ ጥገና ያድጋል። በመጨረሻም ከቀዶ ጥገናው በኋላ የልብ ስርአተ ምት በመቋረጥ ዘላቂ



ሊያሻ የልብ ምት ባትሪ የማስፈለጉ እድል ከ3.3% ወደ 5.9% ሁለቱን በሚያጣምረው ቀዶ ጥገና ያድጋል" ይላል። (9,10,11)

*****

እንግዲህ ይህንንና ሌሎች ሳይንሳዊ መረጃዎችን አክለን በስፋት ከቤተሰብ ጋር ከተወያየን በኋላ ታካሚውም ቤተሰብም በውሳኔው ተስማሙ። በመጨረሻም አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገን ስናበቃ በእለተ እሁድ ከቀትር በኋላ ለማድረግ ወሰንን።

በዚሁ ቀን ጠዋት የነበረኝ ስብሰባ እየተካሄደ ከቀኑ6:30 ሲሆን መቋጫውን ነበር። ከተሰብሳቢዎቹ በዚህ ሰዓት ስራ እንዳለኝ እንጂ ምን ያህል ያስጨንቀኝ ስራ መሆኑ ያወቀልኝ አልነበረም። በእኔ ቤት ሀሳም ያሳለመኝ እና በመጥፎ የተረገምኩት በመሆኑ ስለምም ምቾትም ነስቶኛል። የመዝጊያ አጀንዳውን እንቀጥቅዝ ለመጨረስ ሞከርኩ። በመቀጠልም ተገቢውን መሰናበት እንኳን ሳልፈፅም ወደ መኪናዬ ከነፍኩኝ። የመገናኛ አቋራጩ መንገድ በመጠቀም አዲሱ የአደይ አበባ ስታዲየም መንገድ ላይ ብቅ አልኩኝ። ወቅቱ ክረምት ነበርና ሰማዩ ጠቁሮ በከፊል ዝናብ እየጣለ ነበር። ከኤድናሞል ቁልቁል ወደታች ወደዋናው የቦሌ መንገድ ከነፍኩ። ዋናውን የቦሌ መንገድ ይዤ እስከ



የመጀመሪያው በታሪካዊው ቀዶ ጥገና የተሳተፈው የሀገር በቀል የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን። በምስሉ እንደሚታየው ሦስት ሴትና ሦስት ወንድ የተቀረ ቡድን ነው (ሰኔ 2013 ዓ.ም)



# 7

## የመንታ ዘለላ

ዛሬ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል የአንድን ጨቅላ ሕፃን የመግባት ውሳኔው ለእኔ ተትቷል። ለመወሰን አስቸጋሪ የሆነብኝ ምክንያት ደግሞ ከ፲ ወር በፊት የአንዲት ሕፃን የልብ ክፍተት ቀዶ ጥገና ስንወስን እናት እና አባት የይሖዋ ምስክር እምነት ተከታይ መሆናቸው እና ልጃቸውም በቀዶ ጥገናው ወቅት ምንም ዓይነት ደምም ሆነ የደም ውጤቶች መውሰድ እንደማትችል ከመጽሐፍ እምነታቸው ጋር እንደሚቃረን ስለነገሩን ነበር፤ በወቅቱ ሁኔታው አስገርሞኝ 'እናትም ሆነ አባት ሀይማኖቱ የግላቸው እንጂ እንዴት አንደበቷን ባልፈታች ሕፃን ላይ ይህንን ሕይወት አድን ቀዶ ጥገናው እንዳይቀጥል የሚያደርግ ውሳኔ ሊያሳልፉ ይችላሉ?' አልኩኝ። እናም ተገርሜ ከማለፍ ባሻገር ምንም ማድረግ

አልቻልኩም። እናም ከቀዶ ጥገና ቡድን አባላት ጋር ቁጭ ብለን መከርን በውሳኔውም ምንም እንኳ ቀላል የልብ ቀዶ ጥገና ቢሆንም ምንም ደም ላያስፈልግ ይችላል ብሎ በድፍረት መግባት እንደሌለብን ተስማምተን ወሰንን። በመሆኑም ሕፃኗን እንደማንሰራት ነግረን ወደ ቤት ላክናቸው።

ታዲያ ይህ በሆነ በወሩ ነበር ቤተሰቦቿ በደም ጉዳይ መስማማታቸውንና ቀዶ ጥገናውን መፍቀዳቸው የተነገረን።በመቀጠል ለቀዶ ጥገናው ዝግጅት ወደ ሆስፒታል አልጋ ክፍል ገባች።

እኛም የወትሮውን ዝግጅት በማጠናቀቅ ሰኞ ጠዋት በቀዶ ጥገናው ክፍል ተገናኘን። ይሁን እንጂ ወዲያው የታካሚዋ ቤተሰብ ጋር ችግር እንዳለ ተነግሮኝ ተጠራሁና ወደዚያ አመራሁ። በቦታው ስደርስ ያገኘኋቸው እናት እና አባት እንደወትሮው ጥንቁቅ ብለው፣ ዘንጠው፣ ተከርክመው እና አምረው ወትሮ በማውቀው ፈገግታ አልነበረም ያገኘኋቸው። ገና ሳያቸው ስቃይ እና ጭንቀት እንቅልፍ ከማጣት ጋር ተዳምረው 36 ሰዓት በስራ የተጎሳቆለ፣ በተረኝነት (Duty) ያደረ ለማጅ ሐኪም መሰሉኝ። የገባኝ መሰለኝ፣ አሳዘኑኝ። ምን እንደ ተፈጠረ እንዲያስረዱኝ ጠየኩኝ። ስርአት በለው፣ በወትሮው ጨዋነት አባት እና እናት የተፈጠረውን አስረዱኝ።

እዎ እንደዚህ አሉኝ።"እኛ ልጃችን ደም ከስፈለገ ትውሰድ አላልንም።



እኛ በሕይወት እያለን ልጃችን ደም እንድትወስድ አንፈቅድም።" ፍርጥም ብለው አረዱኝ።

የእኔ ተራ ተሰጠኝና አስረዳኋቸው። "ምናልባት አንዳንዴ ደም የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሕይወቷ የሚተርፈው ደም በመውሰድ እና ባለመውሰድ ሊሆን ይችላል። በተለይ የደም ሙላት ደረጃ (hemoglobin level) ከ5.8gm/dl በታች ደረጃ ሲደርስ ደም ሳይወስዱ የሚተርፉ ሰዎች እጅግ ትንሽ ነው። ቢቀጥል ደም ብቻ ሳይሆን የደም ውጤቶች (FFP, platelet, cryoprecipitate etc) ሊያፈልጉ የሚችሉበት ሕይወት አድን ሁኔታ ሊኖር ይችላል።እናም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን" አልኩኝ። በጣም ያስደነቀኝ መልስ ተሰጠኝ። "ዶክተር አንተ እና ቡድንህ የቻላችሁትን አድርጉ፣ ደም ሳያስፈልጋት የሚያልቅበትን ሁኔታ አቅማችሁ በፈቀደ አድርጉ። ከዚህ በላይ ከሆነና ሕይወትዋ መትረፍ ያለበት በደም መውሰድ ሁኔታ ውስጥ ከወደቃችሁ ይኸው እኛ ወላጆች ፈርመናል፣ ፈጣሪ የፈቀደው ይሁን" አሉ። እውነቱን ለመናገር እኔም ቃሉን ለመጠቀም ቀፈፈኝ።

ከስራቸው ቁልጭ ቁልጭ የምትለዋን ጣፋጭ ሚጢጢ ሕፃን እያየሁ አይኔ እንባ አቀረረ። እንባዬ ቅርብ ስለሆነ፣ በሀዘንና በቤተሰብ ፊት እንደዚህ ሳለቄ መገኘቴን ተፀይፌ ከፊታቸው ተሰወርኩ።

በፍጥነት ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል በመሄድ ከሙሉ የቀዶ ጥገና አባላት

ጋር ተሰበሰብን። የተሰማኝን ስሜት ሳልደብቅ ነገርኳቸው። ይኸንን የተሸበረ ቤተሰብ ለመርዳት የተቻለንን እናደርግ አልኩኝ። "ሁሉም ውሳኔው የአንተ ነው፤ አንተ ከተስማማህ እኛም የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን" አሉኝ። ዞሮ ዞሮ ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ቀዶ ጥገናችን ከደም መፍሰስ ምን ያህል የፀዳ ይሆናል?" ሲሆን ምንም ደም ሳያስፈልግ ቀዶ ጥገናውን መከወን ትልቁን ሚና ይወስዳል። በመሆኑም እኔ ይህን ተረድቼ ውሳኔዬ ከሆነ፤ በእነርሱ በኩል የሚችሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉ ገለጡልኝ። አዎን ልክ ነበረ።

ነገር ግን አንዳንዴ ደማቅ የልብ ቀዶ ጥገና ላይ የሚገጥም "Hemodilution" የሚባል ሁኔታም ሊከሰት እንደሚችል አሰብን። ይህ ማለት፣ ገና ቀዶ ጥገናውን ለመጀመር እና ልብንና ሣንባን ከማሽን የምናገናኝበት የትቦ ሲስተም (tubing system) በምን ይሞላ (Prime) የሚለው በራሱ ከባድ ፈተና ሲሆን፤ በልብ ቀዶ ጥገና ወቅት እንዳና የተለመደ የደም ማነስ የሚያስከትል ምክንያት ነበር። ያም ሆኖ ይህ ውሳኔውን ወስነንና ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ይህችን የመግታ ሀዋን እንደ ዘለላ ይዘን ገባን።

የልብ በሮችን በመቀየር (Valve Surgery) ላይ በተከሔደ ጥናት የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) እምነት ተከታዮች ደም ሲያስፈልግ ደም የሚቀበሉ ታካሚዎች ይህን ቀዶ ጥገናው በከፈዱ ተከታይ 30ቀኖች ውስጥ ህይወታቸው የማለፍ እድሉ (opera-



tive mortality) 4% ሲሆን የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) እምነት ተከታይ ያለሆኑ እና ደም ሲያፈልግ ደም የወሰዱ የመሞት እድላቸው 2% ነው ይላል። (12,13,14)

ምንም እንኳን ደምና የደም ውጤቶችን የይሖዋ ምስክሮች Jehovah Witness ባይቀበሉትም። እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች በሚገጥም ወቅት ምርጫ አልባ ግን አይደሉም። በመሆኑም የደምን ስራ ተክተው የሚሰሩ የተለያዩ አማራጮች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ (erythopoitin/EPO, Albumin, raFVIIa, autologous auto transfusion & isovolumic haemodilution) የተባሉ የደም ምትኮች ይገኙበታል ። ይሁን እንጂ በሀገራችን አልፎ አልፎ ከምንጠቀመው EPO ውጪ ሌሎች ሲተገበሩ አይሥተዋሉም። የሆነው ሆኖ በውሳኔያቸን ጸንተን ቀዶ ጥገናውን ለመስራት ለቤተሰብ አሳወቅን፤ ደም ቢያስፈልግ እንኳን እንደማንጠቀምም ተስማማን። በመጨረሻም ህጻንዋ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ገባች።ዝግጅቱ አልቆ እነሆ ቀዶ ጥገናው ተጀመረ።

*****

እስፈሪ ፀጥታ የሠፈነበት ከመሆኑም በሻገር በሁሉም አባላት ዘንድ ከአሁን አሁን ምን ተከሰተ የሚል ጭንቀት ከአይናችን ላይ ማስተዋል ይቻላል። በ12 ሲ.ግ ሕፃን ደረት ውስጥ ገብተን ጣቶቻችንን በርቀት መሳሪያዎቻችንን የጣቶቻችንን ቅጥያ በማድረግ በጥንቃቄ ልብ ውስጥ ገብተን የልብ የተፈጥሮ ክፍተት ለመዝጋት እየሰራን ነው።

ዕውቀታችንን እቅማችን በፈቀደ መጠን በዚህች ሕፃን ላይ የሚደረገው ቀዶ ጥገና ደም አልባ እንዲሆን ልዩ ተልዕኮ ይዘን ገብተናል። ማሽኖቹ ከሚያሰሙት የጢጢ ድምፅና አልፎ አልፎ ከሚቅጨለጨሉ የቀዶ ጥገና መሳሪያዎች ውጪ ምንም ድምጽ የለም። ትንፋሻችንን ዋጥ አድርገን ከዚህ ጀብድ አይሉት እብደት ውስጥ በሰላም እንወጣ ዘንድ በስሉትም ጭምር እየተውተረተርን ነበር። ምንም ከማይደማ ግውግ እስኪመስል ድረስ እጅግ በጠራና ደስ በሚል ሁኔታ የቀዶ ጥገና ስርአት እየተካሔደ ነበር። የተፈጥሮ ክፍተቱ ተዘጋ። ልብም ተነስቶ ስርአት ባለው መንገድ መምታት ጀመረ። እንግዲህ የሚቀረው ልብን ከማሽን በማላቀቅ ልብም ሳምባም በራሳቸው እንዲሰሩ ማስቻልና የሚደሙ ነገሮችን የመቆጣጠሩ ጉዳይ ነበር።

እውነቱን ለመናገር እንደዚያን ቀን እጅግ የጠራ ቀዶ ጥገና ሰርቼ አላውቅም፤ ጥንቅቅ ያለ ቀዶ ጥገና። ከ4 ሰዓት በኋላ በሰላም ፅኑ ክፍል ደረስን። ሁሉም ነገር በሠላም መጠናቀቁ ለወላጆቿም ለማብሰር ተቻኮልን። በደስታ ተቃቅፈን ተሳሳምን። ግን መቸኮል እንደሌለብኝ



ይገባም ተሰማኝ፤ ተረጋጋሁ። ዋናውና አስፈሪው የመጀመሪያ የቀዶ ጥገና ቀን በሰላም አለፈ። በሆስፒታላችን በቆየችበት ሰባት ቀኖችም ውስጥ የዚህች ብላቴና ሕይወት ምንም ጠብታ ደም ሳያስፈልገው ነገደና በወላጆችዋ ዕቅፍ ገብታ በፍንደቃ በስድስተኛ ቀን ወደ ቤቷ ገባች።

ለመሆኑ ደም የሚያስፈልግበት አስገዳጅ ሁናቴ ቢከሰት ኖሮ ምን እናደርግ ነበር? እየደማች ስትሞት እናያለን ወይስ የሚደረገው ሁሉ አድርገን ወደ እስር ቤት እሄዳለሁ? መልሱን ለእናንተ ተውኩት።

ቤተሰብም በቀልድ መልክ እንዲህ ሲሉ አመሰገኑኝ። "በመጀመሪያ በድፍረት ውሳኔውን ተቀብለህ ልጃችንን ስላዳንክልን፤ በመቀጠል መንታ ልጆቻችንን ለመለየት ደረቷ ላይ ጠባሳ ስላኖርክልን" ብለው አሳቁኝ።

ከሰምንታት በኋላ ለፈፀምኩት ጀብድ ከዚህችው ሕፃን የእጅ ሰዓት ተበረከተልኝ። ዛሬ ላይ ይህች ህፃን በየቴሌቪዥኑና በየሬድዮው "ልቤን ያመኛል" እያለች ለልብ ማዕከሉ እርዳታ ማስታወቂያ ስትሰራ ትታያለች።



[illegible] ሀ1 የልብ ቀዶ ጥገና ማለት ደም ውስጥ የሚካሄድ ቀዶ ጥገና ነው ማለት ይቻላል፡፡ እናም በዚህ ቀዶ ጥገና ደም ውስጥ በሚካሄድ ሰርጀሪ ደም ሳይፈስ መስራት እንደሚቻል ተመስክሮል፡፡



# ፰

## ''ጀግናዬ''

ሀሙስ ሌሊት ለአርብ አጥቢያ እንቅልፍ በአይኔ አልዞር አለኝ፡ ነገ አርብ ቀዶ ጥገና የለኝም አእምሮዬ ግን ያለ እረፍት ያውጠነጥናል ፍላጎቴ መተኛት ቢሆንም ለወራት ሲንከባለል የመጣው የትልቁ ውሳኔ ማስፈፀሚያ ቀን ቅዳሜ ነበር እነሆ ቅዳሜ በሀገራችን ለመጀመርያ ጊዜ እጅግ ውስብስቡን ቀዶ ጥገና Bental Procedure ለመስራት ቀን ተቆርጧል፡፡

ለወራት የተዘጋጀንበትን ቅድመ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ አጠናቀን ታካሚውም በሆስፒታል ተኝቷል፡፡ እንቅልፍ መተኛት አቃተኝ፡፡ በቀላሉ አዕምሮዬ የሚያፈልቃቸውን የማያልቁ ጥያቄዎችን ለመመለስ ደግሞ

ይገማጫ ኮምፒውተሬን እየከፈትኩ እያለሁ አረጋግጣለሁ፡ በለቤቴም በውድቅት ሌሊት አንዴ ላይ አንዴ ታች ስል እሷም ተነስታ እኔው ጋር ተቀመጠች። በዚህ ጊዜ ነበር አንድ ጥያቄ ያቀረበችልኝ:: "ይህንን ያህል አስቸጋሪ ከሆነ ለምን ኃላፊነት ትወስዳለህ" ለምንስ አትተወውም?" የሚል ጥያቄ ነበር።

*****

Huge Bental የመጀመሪያ የሕክምና ትምህርቱን የተከታተለው London ከሚገኘው ቅዱስ በርቶሎሚዩ ሆስፒታል ሲሆን በልብ ቀዶ ጥገና ስራው ከፍተኛ ዝና በእንግሊዝ ሀገር የመጀመሪያ የልብ ቀዶ ጥገና ፕሮፌሰር ለመሆን በቅቷል።

በእንግሊዝ ሀገር በ1953 ከአሜሪካው የዶ/ር John Gibon የመጀመሪያውን የልብ ክፍቶ ጥገና መሣከቱን ተከትሎ ዶ/ር Huge Bental እንዲሁ Belrose HLM በመጠቀም ጀምረው ነበር። ቢሆንም አስደንጋጭ ውጤት በመከሰቱ የልብ ቀዶ ጥገናው እንዲቆም ተደርጎ ነበር። ይሁን እንጂ በ1959 እንደገና ከደረሰባቸው መሰበር አገግመው የልብ ቀዶ ጥገናን ለመጀመር ችለዋል።



ከዚያም ውድቀት ያገገመው የእንግሊዝ የልብ ቀዶ ጥገና ፕሮግራም (Open Heart Surgery Program) ዓለም ያከበራቸው ጉምቱ የልብ ሐኪሞችና አዳዲስ ግኝቶችን ለዓለም አበርክታለች።

በአንድ በሠላሳ ሦስት ዓመት ወጣት ላይ ባጋጠመው እና በሰራው ቀዶ ጥገና እነሆ የዚህ ጉምቱ የልብ ቀዶ ጠጋኝ ስም የዚህ ቀዶ ጥገና ስም ለመሆን በቅቷል:: ምንም እንኳን ታስቦ ወደ ቀዶ ጥገናው የተገባው Aortic Valve የተበላሸውን አንድ የሚያፈስ ቫልቭ ለመቀየር ቢሆንም ደረት ከተከፈተ በኋላ የታየው ነገር ወደ ኋላ የሚመለስበት አልነበረም። የዋነኛውና ትልቁ የደም ስር (Aorta) የመጀመሪያ ክፍልና መካከሉ ሙሉ በሙሉ እንደ ፊኛ ተለጥጦ ነበር።

ስለዚህም ቫልቩን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እስከ የመጀመሪያው ትልቁ የደም ቧንቧ ማብቂያ መቀየር አለበት። ይሁን እንጂ ይህን ለማድረግ ሂደት ሌላ ትልቅ ስራ ይኖራል። ይኸውም የልብን የደም ቧንቧዎች ከሚነሱበት የተለጠጠው ዋነኛውና ትልቁ የደም ስር (Aorta) በማንሳት አርቲፊሻል የደም ቧንቧ ላይ መትከል ይሆናል። በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የወደቁት ዶ/ር Huge Bental ስራቸውን በድል ተወጥተው አጠናቀቁ። በ1968 ይህንን ስራ ከጓደኛው ዶ/ር De Bono ጋር ስራቸውን ለዓለም አስተዋወቁ። (15)

*****

በዚህና በተወሳሰበና ደም መፍሰስን ማቆም አስቸጋሪ በሆነበት ይህ ቀዶ ጥገና በዓለማችን በብዙ የልብ ቀዶ ጠጋኞች ዘንድ የሚፈራና የማይደፈር ቀዶ ጥገና ሆኗል። በመሆኑም የብዙ ዓመታት ልምድ ያላቸውና በሙያው አንቱ የተባሉ ሠዎች ብቻ የሚሰሩ ቀዶ ጥገና ለመሆን ችሏል።

የልብ ቀዶ ጥገናው ትምህርቱን በእንግሊዝ ሀገር ያጠናቀቀውና ከሃያ ዓመት በላይ በእንግሊዝ እና በአሜሪካ በዚህ ሙያ ያገለገለው Dr. PV. Rao በባንግሎር በሚገኘው ናራያና የልብ ቀዶ ጥገና ሆስፒታል (Narayana Institute of Cardiac Science) ከሰላሳ ዓመት በላይ የልብ ቀዶ ጠጋኝ ሆኖ እያገለገለ ያለ የቀዶ ጥገና ሀኪም ነው። ለትምህርት ሦስት ዓመት Narayan በቆየሁባቸው ጊዜያቶች የልብ ንቅለ ተከላ (transplant) እና Bental ቀዶ ጥገና ከእርሱ ሌላ ሰው ሲሰራ ብዙ አይስተዋልም። እነሆ እኔም የዕድል ጉዳይ ሆኖ በዚሁ ቀዶጠጋኝ ስር ሆኜ እየተማርኩ ነው። በቆየሁባቸው በእነዚህ ጊዜያት አራት የልብ ንቅለ ተከላ ሲሰራ ተሳትፌያለሁ። ከዚህ በሻገር አስራ ሁለት Bental Procedure ሲከወን ረዳት ቀዶ ጠጋኝ (Assistant surgeon) ሆኜ ሰርቼ ነበር ።ሁሌጊዜም ትልቁ ፈተና የሚሆነው ደም መፍሰስን ማቆም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ከቀዶ ጥገናው ክፍል ሳንወጣ እዚያው የሚቀሩትን ታካሚዎች እንደነበሩ አስታውሳለሁ። የኔም የዛሬ ትልቁ



ስጋት የሆነው ይህ የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት ከቀዶ ጥገናው ክፍል ሳይወጣ እንዳይቀር ነበር።

*****

ይህ የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት የቁመቱ ርዝመት እና የእጅ ሰፋት በመመልከት ለዚህ ያጋለጠውን በሽታ Marfans Syndrome በቀላሉ መጠርጠር ይቻል ነበር። ይህ በሽታ ብዙ የሰውነት ክፍሎችን የሚያጠቃ ሲሆን በዋናኛነት የመገጣጠሚያ ክፍሎችን፣ አጥንትን፣ አይንና ትልቁን የደም ስር በመለጠጥና በማስፋት ይታወቃል።

ታካሚውም ሆነ ቤተሰቡ ለዓመታት በሰበሰቡት መረጃ የቀዶ ጥገናውን ክብደትም ሆነ አደጋ ተገንዝበዋል። ልቡ ላይ የደረሰው ችግር በMarfan Syndrome ምክንያት የተለጠጠው ትልቁ የደም ስር አንደኛውን የልብ በር እንዲያፈስ በማድረጉ ነበር። ለአመታት ወደኋላ ባፈሰሰው የዚህ ልብ በር ምክንያት ዋናው የልብ ክፍል (left ventricle) በከፍተኛ ሁኔታ ተለጠጠ።

ይሁን እንጂ በ Aorta ላይ የሚያስከትለው ችግር ዋናውና ለሞት

የሚያበቃው ሲሆን ይህም ሁኔታ Ascending Aortic Aneurysm ይባላል።

በሀገራችን ለበርካታ ጊዜ ከውጭ የሚመጡ የበጎ አድራጊ የልብ ቀዶ ጥገና ቡድኖች ጋር ቢቀርብም ሁሉም እንደማይሰሩት ነግረው አሰናብተውታል። ከዚህ ቀጥሎ የዚህ ታካሚ ዕጣ ፈንታ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ መታከም ነበር።

ለሞት የሚያበቃትም ዋንኛ ምክንያት ሳይሰራ በቆየ ቁጥር ይህ የደም ቧንቧ የመሰንጠቅ (Aortic Dissection) ወይም የመፈንዳት (Aortic rupture) እንዲሁም Aortic Valve የተባለው የልብ በር በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኋላ በማፍሰስ (severe aortic regurgitation) ለልብ ድካም (Heart Failure) በመዳረግ ነው።

*****

ምርመራዎችን አጠናቀን በቀዶ ጥገናውም ሰዓት ሆነ ከዚያ በኋላ ለችግር ሊዳርጉ ይችላሉ ያልናቸውን ነገሮች አጥንተን ጨረስን። የምንፈልጋቸው መሣሪያዎች መኖራቸውና የሌሉት ከውጭ እንዲመጡ አደረግን። እናም በተማርኩትና በገኘሁት ልምድ ይህንን



የቀዶ ጥገና መስራት እንደምንችል ከኢትዮጵያ የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን (Heart Team Ethiopia) ጋር ተስማማን።

"ዕውቀት ተግባር ላይ ካልዋለ ሀገርን ካልጠቀመ ተምሮስ መምጣት ለስምና ለወረቀት ፍጆታ መዋል የለበትም" ብዬ ራሴን ላበረታታ ሞከርኩ። የሠው ልጅ ትልቁ ድል ሁሌም በለውጥ ጎዳና ላይ ሲሆን እንጂ አንድ ቦታ ላይ ቆሞ የተለመዱ ስራዎችና ቀላል ህይወትን (daily routine activities) ምርጫው ማድረግ የለበትም ባይ ነኝ።ሕይወት ማብቃት የለበትም። እንዚህንና እንዚያን እሰራለሁ። ስለዚህ ለእኔም ሆነ ለዚህች ደሀ ሀገር ይህ ይበቃል ብዬ ማሰብም መቀበልም አልፈለኩም። ለውጥ፣ አዲስ ድል፣ አዲስ ታሪክ፣ አዎን በዚህ ትግል ውስጥ መሰበር፣ ከፋኛ መሰበር፤ አለመነሳት ሊከሰት ይችላል።

*****

ሀሙስ ምሽት አለመተኛቴ አርብ ከአቅም በላይ በሆነ ድካም እንድተኛና እንቅልፍ እንዲወስደኝ ረዳኝ። በመሆኑም ቅዳሜ ከእንቅልፌ ስነቃ በመልካም የአካል እና የመንፈስ ብቃት ነበር። እነሆ ቅዳሜም ነጋ። የቀዶ ጥገናውም ቀን ደረሰ። ምንም እንኳን ከሁለት

ወር በፊት ቀዶ ጥገና ለመስራት አጋጣሚ የነበረ ቢሆንም በሀገራችን የታዋቂውን የኪነጥበብ ሰው ግድያ ተከትሎ በተከሰተው ብጥብጥ ታስሞው ከሚመጣበት ከተማ መንገድ ተዘግቶ መምጣት ሳይችል ቀረ። ነገሩ ፈጣሪ አላለውምና ምንም እንከዋን ትልቁ አኦርታ የተባለው የደም ስሩ ተለጥጦ 90ሚ.ሜ የደረሰ ቢሆንም በህይወት ኖሮ ለዛሬዋ ቀን ደረሰ።

*****

ወደ ቀዶ ጥገና ክፍሉ ጓዜን ይዤ ስደርስ ሽር ጉዱ ለጦር እንደሚዘጋጅ በታሊዮን ከክፍል ወደ ክፍል እንቅስቃሴ ከወትሮ ለየት ባለ መልኩ ይስተዋላል። በሁሉም ሰው ፊት ትኩስነት እና ምን ይከሰት ይሆን የሚል ዓይነት ከዚያም አልፎ ሁሉም አይቶ የማያውቀው ቀዶ ጥገና በመሆኑ መጓጓትም ጭምር ነበረው። አንዳንዶቹ ለፊልድ እንደሚወጣ ስንቅ በዛ አድርገው ይዘው የመጡም ነበሩ። "ምነው?" ስላቸው "ምናልባት ከሠዓታት አልፎ ወደ ቀናት ሊረዝምም የሚችል ቀዶ ጥገና ስለሆነ" ብለው አሳቁኝ።

ሰባቢን ቀደሬ ወደ ቀዶ ጥገናው ቴያትር ዘው አልኩኝ። ስልኬን ድርግም አድርጌ አጠፋሁ። ህባቢን ሙሉ በሙሉ ከቀዶ ጥገናው ክፍል ነርስ Scrub Nurse ጋር አደረኩኝ።በእያንዳንዱ Step ስለሚያስፈልጉ



መሳሪያዎች እና ፍላጎቴን እስከመጨረሻ በጥንቃቄና በጥልቀት ተነጋገርን። እንዲሁም የልብንና የሣንባን ስራ ተክቶ የሚሰራን ማሽን የሚዘውሩት Perfussionist ሁለቱ ሲኒየር ነርሶች ጋር እንዲሁም ተወያየን።

ዛሬ ከወትሮው ልዩ ቀን መሆኑን የእነዚህ ሁለት ጉምቱ Perfussionist ነርሶች በአንድ ላይ፤ በአንድ ቀዶ ጥገና ላይ መገኘታቸው ይናገራል። እዎ እንዳቸው ሲደክማቸውና ለሻይ እረፍት ሲፈልጉ፤ እንዲሁም ፈታኝ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል በሀሳብም ለመረዳዳት ጭምር ነበር። የልብ ቀዶ ጥገና በመመን ስፔሺሊስቱም ጋር እንዲሁ ውይይታችንና ፍላጎታችን ተወያይተን ጨረስን።

እናም በመጨረሻ ቀዶ ጥገናው ተጀመረ። የቀዶ ጥገናው ክፍል AC ክፍሉን ለማቀዝቀዝ ይሞክራል። ከፍተኛ የሆነ ፀጥታ በክፍሉ ውስጥ ቢኖርም ለስለስ ያለ የእስቴር ዘፈን በቀስታ ይንቆረቆር ነበር። ብዙ እስቸጋሪ ብለን የለየናቸው የቀዶ ጥገናው ክፍሎች (Steps) ቀስ በቀስ በሰላም ያልፉ ጀመር።

እነሆ በከፍተኛ መመሰጥ ውስጥ ሆነን ስድስት ሰዓታት አለፉ። ሁሉም ነገር በሠላም የሠራን መሰለን። መደሰት ግን አልጀመርንም። ምክንያቱ ደግሞ ሁልጊዜም የዚህ ዓይነቱ ቀዶ ጥገና Bental Proce-

ጨመ ቅምሩ አንገሬሽ ካለቀ በኋላ ደም መፍሰስን ማቆም የሁልጊዜ ፈተና ስለሆነ ነበር። እናም ዓለም በደረሰበት የመቅቱ ደረጃ ሁሉንም ጨርሰን እንደተለመደው በአንድ አስቸጋሪ ቦታ ላይ በብዛት ደም ሲፈስ ማየት ጀመርን። የፈራነው ደረሰ። ላለመረበሽ እየሞከርን የተቻለንን ያህል ተረጋግተን ለመቆጣጠር ጥረት ማድረጋችንን ቀጠልን። ይሁን እንጂ አልተሳካልንም ነበር። ይበስ ብሎ ከቦታው ላይ የሚፈሰው ደም ከመጨመሩም በበለጠ ይህ ቦታ የቀኝ የልብ የደም ስ ከሰንበነው ሰው ሰራሽ የደም ቧንቧ (Artificial Aortic Conduit) የሚነሳበት ስለነበር ነው። በየደቂቃው ልብ ይበልጥ ይገዳ ጀመር። አሁን በሁላችንም ላይ መደናገጥ መታየት ጀመረ። ምንም እንኳን ልብና ሳምባን ከማሽን በሰላም አላቀን ወደ ተፈጥሮው ተመልሰን የነበረ ቢሆንም ሁሌም እንደሚደረገው ደም መፍሰስን ለማቆም የሚሰራው ከዚህ በኋላ ልብ እየመታ በመሆኑ ነው።

ይሔንን አስቸጋሪ ሁኔታ መቆጣጠር ተሳነን። እናም ቀዶ ጥገናውን ከጀመርን ከ 7:00 ሰዓት በኋላ በጠቅላላው ቡድኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያዝን አስተዋልኩኝ። መሯሯጥ በዛ፤ እናም የዚህን ወጣት ነብስ ለማዳን አንድ የመጨረሻ የሞት ሽረት ትግል ማድረግ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ቡድኑን አረጋግቼ እቅዴን አንድ በአንድ አስረዳሁ። እናም እንደገና ተመልሰን ልብና ሳንባን እቆምን። የደም ዝውውርን ለማሽኑ በድጋሚ ሠጠን፤ እናም አደገኛ ድካም ተሠምቶኝ ስለነበር በዚሁ



ወሳኝ ሰዓት ራሴን እንዳልሰት ብዬ እረፍት ለማድረግ ወሰንኩ። ለብሴን አወለቅሁ። ከጭንቅላቴ ላይ ሁሉንም መሣሪያ አወለቅሁ። ፊቴን ታጥቤ አንድ ብርጭቆ ትኩስ ሻይ ጠጣሁ።

ጥቂት ደቂቃ ካረፍኩ በኋላ ተመልሼ ታጠብኩ። እንደገና የቀዶ ጥገና ልብሴን ለብሼና መሳሪያዎችን በሙሉ በዓይኔና በጭንቅላቴ ላይ አድርጌ ገባሁ። እንደገና ልብን ሙሉ በሙሉ በድን በማድረግ (On Cross Clamp) የሚደማውን ቦታ በእርጋታ መለየት ጀመርን። ቀጥሎ ቀስ በቀስ የቀኝ የደም ቧንቧን ሳንጎዳ ችግሩን ለመፍታት ሞከርን። ጥሩ ስሜት ተሰማን።

አሁንም ቢሆን ግን ቦታው አለመድማቱን ማረጋገጥ የሚቻለው ልብ መምታት ሲጀምርና ከማሽን ስናላቅቅ ብቻ ነው። ሁላችንም በፀሎታችን እየፀለይን ለሁለተኛ ጊዜ በፕሮቶኮሉ መሠረት ልብና ሳንባን ከማሽን አላቀቅን ቦታውን በጥንቃቄ መመርመር ተያያዝን ። የድል ብስራት ስሜት ወረረኝ። ልብ ተመችቶት ይመታል፤ ሳንባም በጥሩ ሁኔታ አክስጅን ያቀብላል፤ የምናያቸው መስፈርቶች በሙሉ ፀድተ ያሉና የእኛን ልብ በደስታ የሚሞሉ ነበሩ። እነሆ ቢላችንን ካሳረፍን ከ10:00 ሰዓት በኋላ የወጣቱ ደረት ተዘጋ። ሁሉም ነገር ደስ ይል ነበር።

ለብሴን አውልቄ ከቀዶ ጥገና ክፍል ወደ ፅኑ ታማሚ (ICU)

ክፍል ለማዝ በድኔ ነበር የሚጋዘው። በጣም ደንዝዣለሁ። የሚገርመው መንቃቴ በጣም ብዙ ሰዓት እንደፈጀብኝ ተረዳሁ፤ እናም "ቤተሰቦቼ ምን ያህል ተጨንቀው ይሆን?" ብዬ ራሴን ጠየኩኝ።

ቀጥ ብዬ ከ ICU ወጥቼ በዓይኔ ሳማትር ከየጥጋጥጉ ስር ሆነው በሀዘን ተቆራምተውና ተስፋ ቆርጠው አምላካቸውን በሆነ ተዓምር መልስም እንዲያሰማቸው ሲማፀኑ ተመለከትኳቸው። እነሱም ተመለከቱኝ። ወደ እኔ በፍጥነት መጡ። የገባቸው ይመስላል፤ እኔ እንጃ ብቻ አበቄ መጥቶ አቀፈኝ፤ ወንድሞቹም እንደዚያው። ቀዶ ጥገናው ማለቁ፣ የተሳካ ስራ መሰራታችንና በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን አስረዳኋቸው። በዕንባ ተራጩ እኔም ዓይኔን ዕንባ ሞላው። ሙሉ በሙሉ በበዓቱ እጅግ መርዘም ተስፋ ቆርጠው እንደነበረ ነገሩኝ።

አሁንም ቢሆን ገና ሙሉ በሙሉ ከችግር እንዳልወጣን፤ ይህ ማለት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ነቅቶ አዕምሮው አለመጎዳቱን ስናረጋግጥ የድል ጮቤ የለም አልኳቸው። እንዲሁም በመጀመሪያው 24ሰዓት ደግሞ የመድማት አደጋ ሊኖር እንደሚችል አስረድቼ ተለያየን።

በጉድኑ ውስጥ የነበረው ድካም እጅግ ፈታኝ የነበረ ቢሆንም ደስታው ግን ልዩ ነበር። ያ ሁሉ ፀጥታና ጥርጣሬ በሰቀ፤ በሆታ ተቀየረ። ተቃቀፍን፤ ተሳሳምን፤ የማስታወሻ ፎቶ ተነሳን። ምሽቱን ከጋመስን



በኋላ እና ሁሉም ነገር መልካም እንደሆነ ስናረጋግጥ ሁላችንም ወደ ቤታችን ሄድን። እዎ ቀጥሎ ያለው በጽኑ ታማሚ (ICU) ክፍል የሚሰሩ ዶክተሮችን ተጋድሎ የሚጠይቅ ይሆናል።

በድካምና ለወራት በቆየው ጭንቀት ይመስላል ደስታዬን ጣጣጥም አቅቶኝ በድኔን ወደመኪናዬ ገባሁ። እየነዳሁ ቤቴ ደርሼ በቀዝቃዛ ውሃ ገላዬን ታጠብኩ። ምግብ ፊት ቀርቤ እህሉን ከማጣጣም ይልቅ የመጀመሪያ ምርጫዬ የነበረው ስልክ መደወልና የICU ሐኪሙን "እንዴትን?" ነው ማለት ነበር።ሁሉም ነገር መልካም ነው፤ ማመን እያቃተኝ ወደማይናገረው ከፊቴ ወደተቀመጠው እህል ቃታዬን ያለርሀራሄ መዘዝኩኝ፤ በጣም ርቦኝ ነበር።ተመገብኩ።

ጥሩ እንቅልፍ ተኛሁ መሰል ጠዋት ትኩስነት ተሰማኝ። ቀጣዩ ቀን እሁድ ነበርና በበዶው የቦሌ መንገድ በርሬ ወደ ሆስፒታል ሄድኩኝ። ምንም እንኳን ሌሊቱን አለመደወሉ የሚነግረኝ ጥሩ ምልክት ቢኖርም በአካል ሄጄ ይህን የ27 ዓመት ወጣት እስካየው ጓጓሁ፤ በቦታው በደርስ ከማሽ Ventilator ተላቋል፤ በራሱ ይተነፍሳል፤ ምንም ደም አልፈሰሰውም። ደስ አለኝ። ነገር ግን አዕምሮው ገና ሙሉ በሙሉ ጥርት አላለም ነበር።

በቀጣይ ቀን ሁለት ሦስቴ እየተመላለስኩኝ አየሁት። ሰኞ ጠዋት

እንደዚሁ በሆንት መጥቼ ሳየው ደስ የሚል ፈገግታ እያሳየኝ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ "ሥራኸው አይደል" አለኝ እኔም አዎን ሁሉም መልካም ነው አልኩት "ደግናዬ ነህ" አለኝ።

እናም ሁለት ቀን ሙሉ ያጣሁትን ደስታ አሁን ግልብጥ ብሎ መጣ። የደስታ ጎርፍ አጥለቀለቀኝ ሁሉም ነገር አበቃ። አይደለም እንዴ አሁን ሞት መጥቶ ቢወስደኝ እኔ ጣጣ አለኝ?

ቀዶ ጥገናውን በበራን በዓመቱ ከሚኖርበት የገጠር ከተማ በጓሮው ያበቀለውን ሽንኩርት በማዳበርያ ጭኖ አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ አበረከተልኝ።






ሥ/ምስል 11 የቤንታልን ቀዶጥገና በቀላል ሥዕል እንዲህ ማስቀመጥ የሚቻል ሲሆን በዋነኛነትም አራት ክፍሎች እንዳሉት ከማሳያ ሥዕሉ መረዳት ይቻላል (ሀምሌ 2012 ዓ.ም)




፬/ምስል ፱፤ የቤንታልን ቀዶጥገና በቀላል ሥዕል እንዲህ ማስቀመጥ የሚቻል ሲሆን በዋናኛነትም አራት ክፍሎች እንዳሉት ከማሳያ ሥዕሉ መረዳት ይቻላል
(ሀምሌ 2012 ዓ.ም)





፬/ምስል ፲፤ ቤንታል ቀዶጥገና በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በድል የከወነው የሀገር በቀል የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን
(ሀምሌ 2012 ዓ.ም)



8/ምስል ለ1 ቤንታል ቀዶጥገና በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በድል የከወነው የሀገር በቀል የልብ ቀዶ ጥገና ቡድን (ሀምሌ 2012 ዓ.ም)



# ፱

## የራስን ቤተሰብ ማከም

የጥዋት ንቃቴን ለማግኘት በቀዝቃዛ ውሃ ገላዬን ከታጠብኩ በኋላ የዕማዬን ሁለት ሲኒ ቡና ፉት አልኩኝ። አንድ ሰዓት ተኩል ሲል ከቤቴ ስወጣ በጥሩ መንፈስና መነቃቃት ነበር። ዛሬም እንደወትሮው ዕቃዬን ሸክፌ ወደ መኪናዬ ለመግባት ስነሳ ስልኬ ጮኸችና "አቤት" አልኩኝ። ስልኩ የተደወለው ከባለቤቴ አጎት ሚስት ነበር። መልዕክቱም የባለቤቴ አጎት በጣም መታመምን ለመንገር ነበር። ሁላችንም ተደናበርን። ከአንድ ቀን በፊት በተቻኮለ መንፈስ ቤቴ ድረስ መጥቶ መታመሙን የነገረኝ ሰው ሲሆን በሰዓቱ የጨጓራ ምልክት ስለሰጠኝ መድኃኒት አዝዤለት ጥሩ እንደተሻለው ገልፆልኝ ነበር የተለያየነው። ታዲያ አሁን ምን ገጠመው?

ወደ መኪናዬ ገብቼ የጉዞ አቅጣጫዬ ወደ ስራ ሳይሆን ወደ በለቤቴ አገት ቤት ሆነ። እዚያም ስደርስ ጥሩ እንዳልሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብንም። በፍጥነት ወደ ምኒሊክ እንደኛው የልብ ሆስፒታል ይዘነው መኪድ እንዳለብን አሳውቄ ወደዚያ ከነፍን። እንደፈራሁት፣ እንደጠረጠርኩትም ምርመራውን ስናካሂድ የልቡ የደም ቧንቧዎቹ መዘጋታቸውን የሚያሳይ ውጤት ማየት ጀመርን። እዎ ብዙም ሳንቆይ በአፋጣኝ የልብ የደም ቧንቧዎችን የሚያበየውን (coronary Angiogram) የሚባለውን ምርመራ አደረግን:: የልብ የደም ስሮቹ ተዘግተው ሊሆን ይችላል የሚለው ጥርጣሬያችን ምንም ስህተት አልነበረውም፣ ሦስቱም የደም ቧምቧዎች ተዘግተዋል:: እናም የበለቤቱ አገት አፋጣኝ በሚባል ሁኔታ የልብ ቀዶ ጥገና ማከናወን ይኖርበታል። ይህም ቀዶ ጥገና "የልብ የደም ስሮችን የማስከፈት (CABG)" በመባል ይታወቃል:

*****

እንግሊዛዊው Stephan Paget በ1896 ተስፋ በቆረጠ ስሜት Surjery of the heart has reached to the limit God has set to all surgery ከማለቱ በሻገር በልብ ላይ የሚደረግ ቀዶ ጥገና በተከበረው የቀዶ ጥገና ሙያ ላይ እንደማላገጥ ሊቆጠር ይችላል ተባለ፡ ይሁን እንጂ በተመሳሳይ ዓመት ጀርመናዊው ዶ/ር Ludwig Rehn



በጦር የተወጋን ልብ በተሳካ ሁኔታ መጠገን ቻለ። እነሆ የማይደፈረው ልብም ለመጀመሪያ ጊዜ በሠው ልጆች እጅ ተደፈረ። ለሚሊዮኖች የልብ በሽታ ፈውስ ከዚህ ቀን ወዲያ "ሀ" ብሎ ይጀምራል። በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚዘወተረው የልብ ቀዶ ጥገና የደም ስሮችን የማስከፈት (CABG; Coronary artery bypass Graft) ይባላል። የተዘጉ የልብ የደም ቧንቧዎችን የደም ዝውውር እንዲያገኙ የሚደረግ ቀዶ ጥገና ሲሆን ከተለያዩ የሠውነታችን ክፍሎች የተወሰዱ የደም ስሮችን ተጠቅሞ ከአኦርታ (ትልቁ የደም ቧንቧ) ጋር በማገናኘት የተዘጋውን የልብ የደም ስር አልፎ የማናኘት ትልቅ ቀዶ ጥገና ነው።

ምንም እንኳን ከ1960 ወዲህ ብዙ ፈር ቀዳጅ ሙከራዎች የተሞከሩ ቢሆንም የማንዛቢን ዕውቀት ከማዳበር ባሻገር የተሳኩ የደም ስሮችን የማስከፈት CABG መስራት ሳይቻል ቀርቷል። ይሁን እንጂ በ1960 G.C Goetz et.al (እና ጓደኞቹ) ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳካ የልብ የደም ስሮችን የማስከፈት (CABG) ቀዶ ጥገና ለመከወን ችሎ ነበር። (16)

*****

[illegible] ይህንን ቀዶ ጥገና ከሃያ ጊዜ በላይ በተሳካ ሁኔታ

አከናውናለሁ። ቀዶ ጥገናውም CABG (Coronary Altery by pass Graft) ይባላል። የዚህ ቀዶ ጥገና ሂደት በሁለት መልኩ ሊካሄድ ይችላል። አንደኛው ልብ ሳይቆም እየመታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልብ እና ሳንባ ቆሞ የሚካሄድ ቀዶ ጥገና ነው። የቤተሰቤ የልብ የደም ቧንቧዎች ሁሉም (ዋናዎቹ ሁለት ቢሆኑም ትልልቅ ቅርንጫፎቻቸው ሲታከሉ ብዙ የደም ስሮች ይሆናሉ) በመዘጋታቸው ሁለተኛው ምርጫ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል።

የማላውቀው ከቤተሰቤ ውጭ የሆነ ሰው ቢሆን ለመስራት የማያስፈራ ዓይነት የተመቻቸ የደም ቧንቧ ነበረው። ነገር ግን ቤተሰቤ ነው። በአዘቦትም ሆነ በበዓላት አብረን የምንበላ የምንጠጣ አንድ ቤተሰብ። እናም ለመስራት ከማሰብ ይልቅ በፍጥነት ወደ ውጭ እንዲሔድ መወትወት ጀመርኩ። ከቤተሰብ ጋር ስላነበረበት ሁኔታ በስፋት መከርን። ሁላችንም በሀሳቡ ተስማምተን ለውጭ ጉዞ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ተጀመሩ።

በአንድ በኩል የውጭ ጉዞ ዝግጅት፤ በሌላ በኩል በጥብቅ እየተከታተልነው ነበር። ይሁን እንጂ የጤናው ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን የሚያሳስብ ሆነ። ከሁሉም በሻገር የአውሮፕላን ጉዞ ሊባብሰው እንደሚችል አምነን ነበር። በዚህ በቋፍ ላይ ባለ ልብ እንዲህ አይነት ጉዞ ማድረግ አይቻልም። ይሔንን በንድፈ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ከአንዴም ሁለቴ ገጥሞኝ ያውቃል። ወደ ቀዶ ጥገና ለመግባት



በዝግጅት ላይ ሆነን የብዙዎች ሕይወት ተቀጥፎ ያውቃል። በፍርሀት እና በጭንቀት ተወጠርኩኝ።

እኔ እዚህ መስራት እየቻልኩኝ እንዲሁ እንደዋዛ ለጉዞ ዝግጅት በሚል ሰበብ ህይወቱ ካለፈ የእድሜ ልክ ጠጠት ሊሆንብኝ ነው። መላ ቤተሰብ የሚወደውና የሚሳሳለት ቤተሰባችን፤ በአንድ ጊዜ በህይወትና በሞት መሀል ሆኖ አረፈው። የወንጌ እና ቤተሰብ ደራሽ መሆን ነበረብኝ። ነሁሉም በላይ ደግሞ ሦስት ልጆች ያፈራሁበት ትዳሬ ችግር ውስጥ ከገዳይወድቅ ስጋት ገባኝ። ከሁሉም በላይ ደግሞ በውጪ የሚኖሩ ጓተሰቦች ስለሁኔታው በቂ ግንዛቤ ባለማግኘታቸው ተጠራጠሩ። እነሱ ጉዞ ወደ ውጭ መሔድ እንዳለበት ብቻ ነበር ያምኑት። እርግጥ ነው ኔችንም እንደዚያው ነበር የወሰነነው። ነገር ግን ጤናው ይሻሻላል ብለን አስበን የነበረ ሲሆን ይህ ሳይሆን ቀረ። ሁኔታው የሚያሳስብ እና በድንገት ሕይወቱ ሊያልፍ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ከምናያቸው ምርመራዎች ጠረጠርን። በደረቱ ስር የሚሰማው ህመም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጣ። ለተከታታይ ሦስት ቀናት እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር ተሰቃየ።

ስለዚህ በድጋሚ ከቤተሰብ ጋር ተቀምጠን ያለውን ሁኔታ አስረዳሁ። ...ሉም ሆነ በጉዞ ዝግጅት ላይ የሚያጋጥመው አደጋ እዚሁ ኦፕሬሽን ...ስራ ሊከሰት ከሚችለው አደጋ ሊበልጥ ይችላል ብዬ አስረዳሁኝ። ...ላይ ጫና ላለማሳደር መላው ቤተሰብ ከእኔ ከራሴ ይህ ሀሳብ

እንዲመጡ ይጠባበቁ ነበርና ባልጠበኩት መንገድ መላው ቤተሰብ በደስታ ተቀበለው። እናም በፍጥነት ወደ ቀዶ ጥገና እንድገባ አረንጓዴ በራልኝ ።

እኔም ቀበቶዬን ጠበቅ አድርጌ ዝግጅቴን አጧጧፍኩኝ። ጥሩ ስራ እንደምሰራ ተሰማኝ። በደም ቧንቧዎቹ ላይ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። ነገር ግን ከስራው በላይ ያሳሰበኝ የቤተሰብ ጉዳይ መሆኑ እና "እንዲህ ቢሆን እንዲህ ቢፈጠር" እያልኩ ስለ ቤቱ ቤተሰቡና ትዳሬ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ተጨነኩኝ። ነገር ግን መውጫ አልነበረም:: ሕይወትን የመታደግ ጉዞ ነበርና ጨከንኩኝ።ይህንን ሀይወት ማዳን ካልቻልኩ በዚህ የቤተሰብ ትዝታ ውስጥ መኖር እንዴት ከባድ እንደሚሆን ማሰብ አይከብድም።

*****

አርብ ማታ ቤቴ ሶፋ ላይ ጋለል ብዬ የውጭ ዜና እየተከታተልኩ ነበር። ባለቤቴ ሀገር ውስጥ ባለመኖርዋ ጭንቀቴን በመጠኑ ቀንሶልኛል። እናም የባለቤቴ መንታ ወንድም ወደ ቤት ሲገባ እኔን ሳሎን አገኘኝ። ቀዶ ጥገናው ነገ ቅዳሜ ጠዋት ነበርና እሱም ጭንቀት ውስጥ ነበር። የባሰውን ጭንቀቴን ያባሰው የሚመስል፤ ነገር ግን እኔን ፈገግ ያሰኘኝ ጥያቄ ጠየቀኝ "ዛሬ ግን



እንዴት እንቅልፍ ይወስድሀል?" ብሎ በሀዘኔታም በግርምትም እየተመለከተኝ ጠየቀኝ። እውነቱን ነበር። ሊያስችል አይሰጥምና ምሽቱ አልፎ ነጋ። ባለቤቴ ጠዋት አዲስ አበባ ትገባለች። ነገር ግን ስለተፈጠረውም ስላለንበትም ሁኔታ ያላስረዳሁት ስለሆነ እንዳታገኘኝ ወሰንኩኝ። እናም ማንም የቤተሰብ አባል ላለማግኘት ስል በሌሊት ተነስቼ ወደ ሆስፒታል ገባሁ፥ ስልኬንም አጠፋሁ።

*****

በሀገራችን ይሄንን ቀዶ ጥገና የደም ስሮችን የማስከፈት (CABG) ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ከፍተኛ የደም ቧንቧ ብዛት ያስገባሁት ሦስት ነበረ። ቀዶ ጥገና ከመጀመሬ በፊት መወሰን አቅቶኝ ያስቸገረኝ የተዘጉት የደም ስሮች አራተኛውን የደም ስር ልስራ ወይስ አልስራ የሚለው ጥያቄ ነበር።ከተዘጉት ሦስት ዋና የደም ስሮች በተጨማሪ ቅርንጫፎችን የሚነሱ ብዙ ጠቃሚ የደም ስሮች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ቅርንጫፎች መካከል አንደኛው ክፉኛ በመዘጋቱ ነበር አራት የደም ስሮችን ለመስራት ያሰብኩት። ይህን ቀዶ ጥገና ሲጀመር በቅድሚያ የሚተከሉትን የደም ስሮች ከደረት ስር እና ከሁለት እግሮቹ መውሰድ ጀመርን።

በመቀጠል ልብንና ሳንባን አቁመን ወደገደለው ገባን። አንድ ሁለት ሦስት ብለን አራተኛውን የደም ስር ባለማመን ስሜት ጨረስን። ይህ ሁሉ ሲሆን ያለምንም የጎላ ችግር ነበር። ቀጥሎ ልብን ማስነሳት ነበር። ይሄ ሁሉ የደም ስር በልብ ላይ ተብትበንበት ይሰራ ይሆን? ጥርጣሬያችንና ስጋታችን ሳይሆን ልብ በጥሩ ሁናቴ ይሰራ ጀመረ። ብዙ መድሀኒቶች ሳያስፈልግ በሰላም ጥኑ ታማሚ ክፍል ደረስን።

ዛሬ በዚህ በቤተሰቡ ላይ በፈፀምኩት ይሁን በሰራሁት ጀብድ ባልታሰበ መንገድ ለቤተሰቡ ጋሻ መሆን ከማሳየቱ በሻገር አራት የተዘጉ የደም ስሮችን በማስገባት በሀገራችን ሪከርድ የሆነ በልብ የደም ስሮች ላይ ንቅለ ተከላ አካሄድን።

ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሆኖ ነበር። ከቀዶ ጥገና ክፍል ወጥተን ወደ ICU (ፅኑ ታማሚ ክፍል) ስንወርድ ሙሉ ቤተሰቡ ጠዋት የገባቸው በለቤቱን ጨምሮ ኮሪደሩ ላይ እየጠበቁን ነበር። ካሰብነው በላይ ማሳካታችንና በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናችንን አበሰርኩ። ሁላችንም በመገላገል ስሜት ተቃቀፍን። በላብ የወረዛውን ሰውነቴን አልተፀየፉትም። ሁላችንም ደስ አለን። ምንም እንኳን ልሰራ ያሰብኩት ሦስት የደም ቧንቧ የነበረ ቢሆንም ሌሎች የተዘጉ ጠቃሚ ቅርንጫፍ የደም ቧንቧዎች ነበሩና አራት የደም ስር መስራታችንን ነገርኳቸው። ይህን ስነግራቸው በቀልድ "መልክ ለቤተሰብ አንድ አስተያየት አድርገሀ/ መርቀህ ነው አይደል?" አሉኝ። ተሳስቀን ቀጣይ ቀኖች ሰላም እንዲሆን ተመኘን። በቀጣይ



ሰአቶችና ቀናት ያገገመበት መንገድ እጅግ በጣም ፈጣንና ፍጹም ሰላም ሆነ።

በሀገሬ ከሰራኋቸው ትልልቅ ስራዎች እና ከምኮራባቸው ስራዎች ተርታ ውስጥ እነሆ ይህ ስራ አንዱ ሊሆን ቻለ። አንድ ጓደኛዬ እንዲህ ሲል ቀለደብኝ። "ሦስት ልጅ ከወለደክ በኋላ ለባለቤቱ ትልቅ ጥሎሽ ያበረከተ" እንተን አየሁ አለኝ። እነሆ ከቀዶጥገና በኋላ አንደኛ ዓመት ተከብሮ አልፏል። ከ 10 ዓመት በኋላ ያገናኘን።




ፀ/ምስል ሀ፤ በሀገራችን ሪከርድ የሆነው የተዘጉ አራት የደም ቧዎችን አልፎ የመክፈት (a four graft coronary artery graft, CABG) ከላይ በተመለከተው ምስል መሰረት የተሰራ ነው (ሕዳር 2012 ዓ.ም)



# 10

# ደም መሸናትን ያስቆመው የልብ ቀዶ ጥገና

ዛሬ ልጆቼን በቤት ትቼ ስወጣ የወንድ ልጁ የሆድ ህመም እያሰሰበኝ ነው። በለቤቱ በስራ ጉዳይ ከሀገር ውጭ ነች፤ እኔ ደግሞ የዕድል ጉዳይ ሆኖ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በላይ ለወራት የተጨነቅኩበት አንድ ከባድ ቀዶ ጥገና የማከናውንበት ቀን ሆኗል።

ልጆቹ ወደ ት/ቤት እንዳይሔዱ አድርጌ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ከተፈጠረ እንዲደውሉልኝ አሳስቤ ከቤቱ ወጣሁ።

በጀርባ በኩል በሚገኘው የልብ ማዕከል በር ለመግባት የመኪናዬን በላከስ ሳሰማ የተለመደው የግቢያችን አትክልተኛ በሩን አልከፈተልኝም

ነበር። ይልቁን በሩን የከፈተልኝ ግለሰብ መኪናዬን ወደ ውስጥ አስገብቼ ከቆምኩ በኋላ ከመኪናዬ ሳልወርድ መርዶ አረዳኝ። የአትክልተኛዬን አባት ማረፋቸውንና ቀብርም በምሳ ሰዓት እንደሆነ ነገረኝ።

በልብ ማዕከሉ ዋልታና መከታዬ የምለው ታማኝ ጓደኛዬ እና ባልደረባዬ በደረሰበት ሀዘን አዝኜ፤ የአባቱን ቀብር ለመድረስ የማልችልበት ቀን በመሆኑ ይልቁን አሳዘነኝ። ገና በጠዋቱ 2:00 ሰዓት ሳይሆን የተደራረቡትን ሀሳቦች አዕምሮዬን ሰላም ነሱት።

ስልክ ደውዬ ለማፅናናት ሞከርኩና በዕለቱ እጅግ ከባድ የሚባል ቀዶ ጥገና ስላለኝ ቀብር መገኘት እንደማልችል ነገርኩት። እውነቱን ለመናገር ወደ ልብ ማዕከል ስገባም ሆነ ስወጣ ልባዊ በሆነ ፈገግታ የሚቀበለኝና የሚሸኘኝ ለመኪናዬ ውበት ከእኔ በላይ የሚጨነቅ ምርጥ የስራ ባልደረባዬ ነው።ትምህርቴን ከሕንድ ሀገር ጨርሼ በመጣሁበት ጊዜ አንስቶ እነሆ እስከ አሁን ድረስ መኪናዬን ማንም ከእርሱ ውጪ ነክቷት አያውቅም። በሆስፒታሉ ውስጥ ከሚኖረኝ የስራ ሰዓት ውጪም ከእርሱ ጋር ቁጭ ብዬ በቀድሞ የውትድርና ዘመኑና በቤተመንግስት ውስጥ ስላሳለፈው ሕይወት በትዝታ ሲያወራኝ ያዝናናኝ ነበር። ዛሬ በሀዘኑ አልተገኘሁም፤ ነገር ግን ስራዬን ጠንቅቆ ይረዳልኛልና ቂም እንደማይቋጥር ይገባኛል።

*****



የቀዶ ጥገና ልብሴን ቢሮዬ ውስጥ ቀይሬ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍሉ አመራሁ። የቀዶ ጥገና ክፍሉ ነርሶች እቃዎቻቸውን በመልክ በመልኩ እየፈረጁ የጎደለውን ለመሙላት ውር ውር ይላሉ። የልብ ቀዶ ጥገና ሰመመን ሰጪዎች ማሽኖቻቸውን መፈተሽ ላይ ተጠምደዋል፤ መድኃኒቶቻቸውን በየመልኩ መኖራቸውንና መጠናቸውንንና ከዚህ የ10 ዓመት ህፃን ልጅ ጋር እንደሚመጣጠን ያጣራሉ። የልብ እና የሳንባና ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን የሚዘውሩት ነርሶቻችን (Perfusionist) በማሽኑ ላይ የሚገጠሙትን ውስብስብ ቱቦዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ ይገጥማሉ፤ በአጠቃላይ ሽር ጉዱ ጦፏል።

ሠላምታዬን ካቀረብኩ በኋላ ሁሉም በቦታው መገኘቱና ለከፍተኛው ድግስ መዘጋጀታቸውን ገለፁልኝ። ቀጥሎም ከሁለተኛ ፎቅ ወደ ታች አንደኛ ደረጃ ወርጄ ይህንን የ10 ዓመት ሕፃን ልጅ ከነቤተሰቡ እንዴት አደራችሁ ለማለት እና ዝግጅት መጠናቀቁን ለማጣራት ወረድኩ።

ከተኛበት ክፍል ብቅ ስል ይህ ታዳጊ ሕፃን ሁለት የእጆቹን ጣቶች [illegible] ጆሮዎች ውስጥ አድርጎ ጮክ ብሎ ይለፈልፋል። ነገር ተበላሸ አልኩኝ፤ ስንፈራ ስንቸር ከብዙ መሰናክል በኋላ ለዚህ ቀን ደርሰን ነበር። አዕምሮው ዘብረቅ ያለ መሰለኝ። በእንዲህ ሁኔታ ወደ ኦፕሬሲዮን መግባት እንደማልችል አውቀዋለሁ። ከሁለት ሣምንት በፊት እንዲሁ አደገኛ ባህሪ (Aggressive behavior) አሳይቶ በመድኃኒት መቆጣጠር ችለን ነበር። ጥንቃቄ በተሞላው መንገድ

ሁሉን አልፈን ለዚህ ቀን ደረስን ስንል ብዬ ድንጋጤ እየተሰማኝ ቀረብኩት። ይሁን እንጂ ይህ ሕፃን እኔ ማየት ከማልችልበት መሣሪያ ስር የዛሬን ክሊፕ እየተመለከተ በጆሮው ውስጥ ያለው Ear Phone እንዳይወድቅ በመያዝ እየተዝናና ነበር። ይህን ስረዳ የደስታ ስሜት እኔንም ፈንቅሎኝ ሣቅኩኝ።

ሳየውም ስዳስሰውም የሚነዝረኝ ይህ ሕፃን ዛሬ በሰውነቱ ውስጥ ያለውን ደም በሽንቱ እየሸና እና ደሙ በተደጋጋሚ ዝቅ እያለ ከ 22 ጊዜ በላይ ደም እንዲወስድ ያስገደደውን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ ሊያገኝ የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና ያካሔዳል። ምክንያቱም ደግሞ ከአራት ወር በፊት በእኔው አማካኝነት የተካሔደው የልብ ቀዶ ጥገና ነበር።

በወቅቱ ሁለት የልብ በሮቹ ላይ ጥገና አካሔደን የነበረ ሲሆን ይህን ቀዶ ጥገና ካካሔደ የሦስት ሳምንት ጊዜ ጀምሮ እነሆ እስከአሁን ሰዓት ድረስ የሚሸናው ደም ሆኗል። ይህን ሕፃን ዛሬ በአራት ወር ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ለማካሔድ ወስነናል። እጅግ እጅግ ከበድ ውሳኔ ነበር።

ሕፃኑን አናግሬና ደባብሼ ቀና ስል ለዚህ ትልቅ ውሳኔ ከደቡብ ሱዳን ተጠርተው የመጡት የገጠር ገበሬ የሆኑት አባቱ ለሽ ብለው ተኝተዋል። ነብሳቸውን አያውቁም። እንግዲህ ሌሊቱን ሙሉ ሲፀልዩና



ሲጨነቁ እንዳደሩ የዛሬው ድግስም የሞት ሽረት መሆኑን ሁኔታዎች እንደነገሩቸው ግልፅ ነበር። ምናልባትም ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ እንደጣላቸው ያሳብቅ ነበር።

*****

ከአንድ ዓመት ገደማ በፊት ነበር በልብ ማዕከል የተመላላሽ ሕክምና ክፍል ኮሪደር ላይ በ20ዎቹ መጨረሻ ላይ የሚገኝ አንድ ወጣት ጠጋ አለኝና የታናሽ ወንድሙ ሕይወት በቋፍ ላይ መሆኑን የነገረኝ። በማዕከላችንም ለሁለት ዓመት መከታተሉን ካስረዳኝ በኋላ በተመሳሳይ በሽታ የሚወደው ታናሽ ወንድሙ ያለ ሕክምና እርዳታ በልብ ሕመም መሞቱን አስረዳኝ። እና ይህ የ9 ዓመት ጨቅላም በተመሳሳይ ሁኔታ ሕክምናውን ሳያገኝ ክትትል ላይ ሆኖ እንዳይሞትበት ተማፀነኝ።

የዚህ ወጣት ድርጊት እና አነጋገር ለህፃን ወንድሙ ያለውን የሚያሳሳ ፍቅር ፍንትው አድርጎ ያሳይ ነበር። ድህነት ሆኖ እንጂ ገንዘብ ቢኖረው ለዚህ አይተው ለማይጠግቡት ትንሽ ወንድሙን የትም ሀገር ወስዶ በቶሎ ችግሩን ቢፈታው ደስ እንደሚለው እሙን ነው።

እነን ሲያናግረኝ መፍትሔ ሊሰጠው እንደምችል የተማመነብኝ ይመስላል። በእርግጥ እንዲህ ያሉ ጨቅላ ሕፃናትን የልብ በሮቻቸውን መጠገን ሁሌም አስተምህሮታችን ይመክራል። በተቻለ አቅም የልብ በር ቅየራን በእንዲህ ያሉ ጨቅላ ሕፃናት ላይ ከቀዶ ጥገና በኋላ ያለውን ክትትል አስቸጋሪ ከማድረግ ጋር ይያያዛል። በተለይም በሀገራችን ያለውን የመድኃኒት አቅርቦት ችግርና በገጠር የሚኖሩ ታካሚዎች በተፈለገው መጠን ለክትትል አለመገኘታቸው ዋንኞቹ ምክንያቶች ናቸው።

ሆኖም ግን በእንዲህ ያሉ ሕፃናት ላይ ቁጥሩ በቂ ባይሆንም በጥቂት ሕፃናት ላይ የሠራኋቸው የቀዶ ጥገና ስራዎች አመርቂ የሚባል ውጤት ነበራቸው። ስለዚህም ነበር ይህን የ9 ዓመት ሕፃን ልጅ እንዳየሁት እጅግ ከመጎዳቱ የተነሳ በተጨማሪም ተጠግኖ የተሻለ ኑሮ እንደሚኖረው በማመን ነበር መስራት እንዳለብኝ የወሰንኩት። እንዲህ በወረፋ እና በተለያዩ የአላቂ ዕቃዎች ችግር የተወሰኑ ወራቶች ካለፉ በኋላ እነሆ በ10 ዓመቱ የዚህን ሕፃን የልብ በሮች ቀዶ ጥገና በልብ ማዕከሉ ለመስራት ቻልን።

በዚሁ ቀዶ ጥገና ደስተኛ ሆንን። አንድ ዋነኛው የግራ ልብ በሩን (Mitral Valve) እና አንድ የቀኝ ልብ በሩን (Tricuspid Valve) መጠገን ቻልን።



በእርግጥ በሁለቱም በሮች በከፊል ማፍሰስ የነበረ ቢሆንም ኦፕሬሽናችን በሙያው ይህ እጅግ አመርቂ የሚባል ውጤት ሲሆን ህፃኑም ከአሁን በኋላ የተሻለ ሕይወት እንደሚኖረው እርግጠኛ ነበርን። ሁለት ሣምንት በሆስፒታላችን ካገገመ በኋላ በጥሩ ሁኔታ ከሆስፒታል እንዲወጣ ተደረገ።

በመጀመሪያ ሳምንት የተመላለሽ ቀጠሮው ደሙ እጅግ ዝቅ ብሎ የሚሸናው ሽንትም ኮካ ቀለም እንደሆነ፣ ምግብም ብዙ እየማይደፍርና እየደከመው መሆኑን አየን።

በድጋሚ በሆስፒታል አስተኝተን ደም መተካት ጀመርን። ሆኖም እንደሚስተካከል ተስፋ አድርገን ብንጠብቅም ይህ ሕፃን ደም መሸናቱንና ደሙም ዝቅ (Level of Hemoglobin) ማለቱን ቀጠለ። በተደጋጋሚ ደም ቢሰጠውም የደሙ መጠን ከፍ ሳይል ቀረ።

በዚህ ጊዜ በጥቁር አንበሳና በቅዱስ ጳውሎስ የሚሰሩ ከፍተኛ የደም ስፔሻሊስት ሐኪሞች ጋር ውይይት ተደረገ። መጠነ ሰፊ የደም ምርመራ ተካሔደ። ለወራት የዘለቀው ምርመራ እዚህ ግባ የሚባል ውጤት ሳይገኝ ቀረ።

ስለዚህም ጥናታችንን በልብ በሩ ላይ በተሰራው የልብ በር ቀዶ ጥገና ላይ አደረግን። እጅግ ባልተለመደ ሁኔታ ጥገና ሲካሔድ የቀይ የደም ሴሎች

ሊሰበርየሚችልበትሁኔታሊኖርእንደሚችልየጥናትፅሁፎችንአገኘን። እነዚህም ፅሑፎች የሚያትቱት በታካሚያችን ላይ የሆነውን ዓይነት መንገድ መከተላቸውና በመጨረሻም ይህንን የልብ በሮች በድጋሚ በመስራት መፍትሔ ማግኘታቸውን በ Case Report መልክ ተፅፈው አገኘን።

የትኩረት አቅጣጫችንን በዚሁ አድርገን ለድጋሚ ቀዶ ጥገና ራሳችንን ማዘጋጀት ቀጠልን። ይሁን እንጂ ይህ ሕፃን እንደተለመደው ደም በመውሰድ ላይ ሳለ አለርጂ በመከሰቱ በጠና ታመመ። ከብዙ ደም መውሰድ በኋላ ዛሬ ይህ በመሆኑ ተገርመን እንደገና ወደ ICU (ፅኑ ታማሚ ክፍል) አዘዋወርነው። ይህንን ችግር ፈትተን በተመሳሳይ በደም ውስጥ በቀላሉ ለማግኘት በማይቻል ኢንፌክሽንም ይህ ችግር ሊከሰት የሚችል በመሆኑ የዚህም የ 6 ሣምንት ሕክምና አስጀመርን። ሕፃኑም ተመልሶ ከፅኑ ታማሚ ወደ ዋርድ መመለስ ቻለ።

አሁን ወስነናል። የደሙ መጠን (Level of Hemoglobin) ከተስተካከለ እና በቂ የኢንፌክሽን ሕክምና ካገኘ በድጋሚ ቀዶ ጥገናውን ለመስራት መወሰኑን ለቤተሰብ ነገርኳቸው። ገምዛዛ፤ ለመቀበሉ የሚከብድ፤ እንዲህ የተጎዳ ጨቅላ እንዴት አድርጎ ነው በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ እጅግ ከፍተኛ አደጋ ያለውን ቀዶ ጥገና የሚያካሂደው?

*****



ከራውን ለዚህ ታናሽ ወንድሙ የሠዋው የታካሚያችን ታላቅ ወንድም ዛሬ ደግሞ ይኼ ሁሉ የደከመለት ወንድሙ እንደማይተርፍ ከተሰማው ውሳኔውን መወሰን ቸገረውና ገጠር ያሉት አባት እንዲጠሩ አደረገ። እኔም ውስጤ የሚታገለኝን አንድ ሺህ ጥርጣሬዎችን ዋጥ አድርጌ ከምጨምጭ በለ አነጋገር ሌላ አማራጭ እንደሌለ አስረዳኋቸው።

ሲውል ሲያድርም ይህ ደም እንዲሸና የሚያደርገው ጉዳይ ኩላሊቱን እንዲወድቅ እንደሚያደርገው፤ በሂደት ሕይወቱን ልናጣ እንደምንችልም ተናገርኩ።

ልጅም አባትም ሀሳቡን በመጨረሻ ተቀብለው የቀዶ ጥገናውን ቀን መጠባበቅ ጀመሩ። እኛም ለማይቀረው ለድጋሚ ቀዶ ጥገና ተስማሚ ሁኔታ መፍጠር ተያያዝን። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የተቆረጠለት ቀን ደረሰ። በዚህ ታሪካዊ ቀንም ይህን የሀይወት አድን ቀዶ ጥገና ለመስራት በሙሉ የሀገር በቀል እውቀት የተዋቀረው ቡድን ህጻኑን ከበን ተሰየምን።

ከደረቴ ስር በፍጥነት እየደቃ የነበረው ልቤም "ተው!" እያልኩ ገላበት ሙረር እያለ የሚወርደውን ቀዝቃዛ ላብ እየታዘብኩ እነሆ የካገናና የደረት መክፈት የመጀመሪያውን ደረጃ ክፍል ጀመርኩ።

*****

Omar Tmran, እና ጓደኞቹ በ2014 በRoyal Victolie Beelfast, UK ባካተሙት ጽሑፍ "በ544 በድጋሚ በሚከፈት ደረት ከፍተኛ የደም መፍሰስ ያጋጠማቸው በ33 ሰዎች ላይ ነበር። ከነዚህም ከአንድ አራተኛው በበላይ (26%) የሞት አደጋ አጋጥሟቸዋል" ይላል። (17)

ምንም እንኳን በሀገሬ ምድር የዚህ ዓይነት ቀዶ ጥገና ሰበት ጊዜ አከናፏጄ ሁሉም የተሳካ ቢሆንም የዚህ ታካሚ ጉዳይ ተለይቶብኛል። የታካሚያችን ሕፃን መሆንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል መመለሳችን ሲሆን ከሁሉም በሻገር ግን ብዙ ጉዳት የደረሰበትና የተገለሉታ ጨቅላ መሆኑን ነገሩን እጅግ አወሳስቦታል።

ከጥቂት ተመስሎ በኋላ ራሴን ያገኘሁት አስፈሪውን ክፍል በሰላም አስናቀቄ ወደ ሁለተኛው ተሻግሬ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ በዝግታ የሚንቆረቆረውን የአስቴር አወቀ የድሮ ዘፈን በጆሮዬ የተሰማኝ። "መስሚያዬ ጥጥ ነው" የሚለው የአራዳ ልጆች ቋንቋ ትዝ ብሎኝ ከራሴ ጋር ሳቅ አልኩኝ።

እንዲህ እንዲያ እያልኩኝ ልብና ሳንባን አቀመን ወደ ገደለው ገባን። ወደኋላ የሚያፈሰውን የማራ ልብ በር በትልቅ የልብ ሰው ሰራሽ ሽፋኝ ቀየርን፣ የቀኝ ልብ ላይ አስገብተን የነበረውን ቀለበት አስወግደን ምንም ዓይነት ባዕድ ሣንጠቀም ጠገንን። በዚህ ሁኔታ 7 ሰዓት



የፈጀው ቀዶ ጥገና በሰላም ተጠናቀቀ። ጨቅላውንም በጣም ትንሽ በሚባል የመድኃኒት እርዳታ ፅኑ ታማሚ ማድረስ ቻልን።

ጥቂት ቆይቼ የሕፃኑን አባትና ታላቅ ውንድም ለማናገር ወደ መጀመሪያ ደረጃ Floor ወደሚገኘው ክፍል ወረድኩ። ሁለቱም ከወንበራቸው ብድግ ብለው በድካም የዛለውን ፊቱን እያዩ፣ የተለያዩ ሰምበሮች ያረፉበትን ግንባሬንና ፀጉሬን እየተመለከቱ፣ 'ምን ገጥሞት ይሆን? ምን ሊለን ይሆን?' የሚለው እንባ ያቀረረውን ፊታቸውን ይዘው ቀረቡኝ። ልጃችን በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለ እና ኦፕሬሽኑም ስኬት እንደነበር አበሰርኳቸው:: ታላቅ ወንድምየው ሲቃውን መቆጣጠር ተስኖት በደስታ እጄዬውን አቀለጠው። በለለፍኩበት ጫናም በፈጣሪ በኩል መካሻ ይስጥህ ብለው አቅፈው ሳሙኝ።

የመጀመሪያው 24 ሰዓት አደገኛ በመሆኑ ለመደሰት ገና ሩቅ ነበርኩኝ:: ከሁሉም በላይ የሚያሳስበኝ 'ደም መፍሰስ እንደገና ይከሰት ይሆን ወይ? ሲሆን፣ ሲቀጥል ደግሞ' ደም የሚሸናው ነገር እውን ከዚህ ቀዶ ጥገና በኋላ ይቆማል ወይ? የሚለው ጥርጣሬዎቼ ነበሩ።

የመጀመሪያውን የደም መፍሰስ በመጀመሪያ ከ4-6 ሰዓት ውስጥ ይለይለታል። ስለዚህም ትንሽ እረፍት ማድረጉ ተገቢ ነው ብዬ ከራሴ ጋር ተማከርኩ። ሲቀጥል የልጁ የጤንነት ጉዳይ ከምን እንደደረሰ

ለማወቅ በቶሎ ወደቤት መሄድ ነበረብኝ። ቤቱ ስደርስ ለዓይን ያዝ የሚያደርግ ደንገዝገዝ ያለ ምሽት ነበር። ልጄም በጥሩ ጤንነ ሲጫወት በማየቴ እፎይታ ተሰማኝ ። ይሁን እንጂ መብራት ጠፍቶ ቤቱ በጨለማ ተውጦ ነበር። የወትሮው ጨዋታችንና ደስታችንን ሳናጣጥም፣ የኔም የጭንቀት ሀሳብ ታክሎበት ፍራሽ ላይ ተቃቅፈን ቁጭ እንዳልን ሁላችንንም እንቅልፍ ይዞን ጭልጥ አለ።

ከእንቅልፋችን ስንነቃ ነግቷል። አይኔን ማመን ተሳነኝ፤ በሳሎን ውስጥ ከሦስቱ ልጆቼ ጋር በተነጠፈልን ፍራሽ ተዘርረናል። ማመን አቃተኝ፤ በፍጥነት ስልኬን ፈልጌ ካኖርኩበት አገኘሁና ማየት ጀመርኩ። እፎይ፣ ምንም ዓይነት የሆስፒታል ጥሪ አልነበረም። ይህ በብዙ መከራ ያለፈው ታዳጊ አስቸጋሪውን ጊዜ በሰላም አልፎታል ማለት ነው።

*****

ከሆስፒታል ደርሼ ICU ስገባ አባት ከልጁ ጎን ወንበር ላይ ቁጭ ብለው ፈገግታ በሞላው ፊት ይስቃሉ። የሆንኩትን ሁሉ ከነገርኩኝ በኋላ በለመደዉሌ ይቅርታ ጠይቄ እንዴት እንዳደረ እንዲያስረዱኝ ጠየቅኩኝ። ለፈፀሙት ትልቅ ስራ ምስጋናዬን አቀረብኩኝ። ከእንዲህ



ዓይነት በራሳቸው የሚተማመኑ የ ICU ባለሙያዎች ጋር መስራት ያስደስታል። በሀገራችን በ ICU አደረጃጀትም ሆነ የሙያ ልህቀት የልብ ማዕከልን የሚስተካከል ማግኘት በእውነት ያስቸግራል።

በደስታ ተሞልቼ በኮሪደር ላይ ስራመድ የሆስፒታሉ ሠራተኞች "እንኳን ደስ አለህ፡ ልጅህ ደህና ሆነልህ" ይሉኝ ነበር። ለካስ ሳይወልዱም ልጅ ይኖራል እንደዚህ ነው።



10/ምስል ሀ፤እነሆ ከአራት ወር የሆስፒታል ቆይታ በኋላ በአስገራሚ ሁኔታ የዳነው ህጻን ከሆስፒታል ሲወጣ ከነኛው ህጻን በጠቅላላው የሆስፒታሉ ሰራተኞች ሊሸኝ የማስታወሻ ፎቶ ነው (ግንቦት 2013 ዓ.ም)



# 11

# የሰማያዊ ሕፃናት ህክምና በኢትዮጵያ

ከስልጤ ክልል ልዩ ስሙ ወራቤ ከሚባል አካባቢ የመጣ የ12 ዓመቱ ሕፃን ቆዳው ጠቁሮ ከንፈሩ ጠቁሮና ጣቶቹ በሙሉ እንደ ከበሮ መምቻ አብጠውና ጠቁረው ካልገደልኩህ ከሚለው የአራትዮሽ የተፈጥሮ የልብ ችግር በአንድ ላይ (Tetralogy of fallot) መፍትሔ ሊያገኝ በኦፕሬሽን ጠረጴዛ ላይ ተኝቷል። በሀገራችን ምድር በሙሉ በሀገራችን እውቀት ይህን ቀዶ ጥገና ለመጀመሪያ ጊዜ ልንሰራ እነሆ ደረት ከፍተን ልብና ሳንባን አቁመን የደም ዝውውር ለማሽን ሰጠን። እንግዲህ ዓለም ከ 60 ዓመት በፊት እንዲህ አይነቱን የጀመረውን ኦፕሬሽን ዛሬ ላይ እኛ እነሆን አንድ ልንል ተሠብስበናል ይባስ ይሆን።

ምንም እንኳን በሀገራችን ከውጭ በሚመጡ ሀኪሞች ይህ ቀዶ ጥገና ይደረግ የነበረ ቢሆንም ዛሬ ግን በሙሉ የሀገር እውቀት መሆኑ ታሪካዊ አደረገው።

*****

አንዲት የሐኪም ልጅ የሆነች ሕፃንን ግን ከሁሉም ከሠራኋቸው የአራትሽ የተፈጥሮ የልብ ችግር በአንድ ላይ (Tetralogy of fallot) ውስጥ እንደ አንዷ አድርጌ ለመቁጠር እቸገራለሁ።

ታሪኩ እንዲህ ነው። ይህች የ3 ዓመት ሕፃን መሠረታዊ ችግሯ TOF የተባለው በሽታ ቢሆንም ከእነዚህ በተጨማሪ በላይኛው የልብ ክፍል ቀዳዳ ነበር። ይህም የዚህን በሽታ ስም ወደ Pentalogy of fallow ወይም አምስት ችግሮች በአንድነት (አምስትዮሽ) እንደማለት ይሆናል። በዚህ ብቻ አላበቃም። በዚህ በሽታ (Pentalogy of Fallot) ላይ ያልተለመደው የደም ስሮች ግንኙነት PDA (Patent ductus arteriosus) አብሮ ነበር። ስለዚህም ስድስት ነገሮች አንድ ታካሚ ላይ በአንድ ጊዜ (ስድስትዮሽ) እንደመከሰት እንደማለት ነው።

*****



የ88ኛ ዓመት ልደቷን ለማክበር አራት ቀናቶች ብቻ ሲቀሯት በአገረ አሜሪካ ይከሄድ በነበረው ምርጫ ድምፅ ለመስጠት ወደ ምርጫ ጣቢያ በመሄድ ላይ ሳለች በፔንስለቬኒያ አደባባይ ላይ ባጋጠማት የመኪና አደጋ ሕይወቷ የተቀጠፈው።

ይህች አሜሪካዊ የልብ ሐኪም (Cardiologist) በህፃናት የልብ ሕክምና መስራች ትባላለች። ለዚህም ከፍተኛ ሙገሳ በተፈጥሮ የሠውነትን ቀለም የሚያጠቁሩ የልብ በሽታዎች መካከል አንዱ የሆነውን ቶፍ (TOF is the most common cause of blue baby syndrome) ጊዜያዊ የመፍትሔ ሀሳብ ነበር። ምንም እንኳን በልጅነቷ በተደጋጋሚ ባጋጠማት ኢንፌክሽን ሙሉ በሙሉ የመስማት ችሎታዋን ብታጣም የመስከረላትና የሚያስታውሱት እንኳር ሀኪም ከመሆን አላገዳትም። ስቴቴስኮፕ ተጠቅማ ልብን ማዳመጥ ባትችልም የራሷን ተክኒክ ተጠቅማ ዓለምን አስደመመች። በመሆኑም በከንፈር እንቅስቃሴና በጣቶቿ ዳበሳ በመጠቀም የሕፃናትን ችግር ከመረዳት የሚሊዮኖች ህይወት አድን ቀዶ ጥገና እንዲፈጠር ፈር ቀዳጅ መሆን ችላለች።

እጅግ የበዙ ሽልማቶች ባለቤት የሆነችው Dr.Helen Taussig ከምትታወቅባቸው ሌሎች ጉዳዮች መካከል Thalidomide የተባለውን መድኃኒት እንዲታገድ በበረከተችው አስተዋፅኦ እና

በአሜሪካ የመጀመሪያዋ ሴት የአሜሪካ ልብ ማህበር ፕሬዝዳንት ሆና በመመረጧ ነበር።

በአራት የተለያዩ ችግሮች የሚፈጠረው ይህ የልብ ችግር (Tetralogy of fallot, TOF) ሕፃናትን ቀለማቸውን፣ ከንፈራቸውንና የእጅ ጣቶቻቸውን ከማጥቆር አልፎ እድገታቸው የጫጨ እና ሕይወታቸውን በአጭር የሚቀጭ ከባድ የልብ ሕመም ነው።

በዚህች ብሩህ የልብ ሐኪም ሀሳብ አመንጪነትና በቀዶ ጠጋኙ Dr Blalock እና ጥቁር ረዳቱ Vivian Thomas በመታገዝ የነዚህን በወቅቱ ተስፋ ያጡ ሕፃናትን ሕይወት የሚያራዝም የልብ ቀዶ ጥገና መስራት ተቻለ። ይህ ቀዶ ጥገና

ታሊዶማይድ (thalidomide) በ 1950ዎቹ መጨረሻዎቹ እና በ1960 መጀመርያ በሰፋት ይወሰድ የነበረ መድሀኒት ነበር። ልክ እንደአስፕሪን ያለፕሪስክሪብሽን እንደጉድ የተቸበቸበ መድሀኒት ነበር። መድሀኒቱ ለህመም እና ለእንቅልፍ እጦት በሰፋት የታዘዘ ሲሆን እርጉዝ እናቶችም የmorning sickness መፍትሄ ለማግኘት በሰፋት ተጠቅመውታል። ነገር ግን የሚወለዱት ህፃናቶች ያለእጅ አሊያም እጅግ ያጠረ እጅ ይዘው እንዲወለዱ ማድረጉ ተደርሶበታል።



አፕሬሲዮንም እነዚህን ሰዎች ለማስታወስ ሲባል BT-Shunt / Blalock Tausig Shunt ወይንም BTT (Blalock,Tausig,Thomas) በመባል ይታወቅ ነበር።

በ ህዳር 1944 የመጀመሪያው አፕሬሽን Dr. Blalock እና ጥቁር ረዳት Vivian Thomas በሰው ልጅ ላይ ከመደረጉ አስቀድሞ ከ 200 በላይ ውሾች ላይ በላብራቶሪ በሙከራ ተፈትሾ ጥሩ ውጤት አሳየ።

ምንም እንኳን BTT Shunt የተሰኘው አፕሬሽን ዘላቂ መፍትሔ ባይሆንም በ 1954 Dr. John Gibbon የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን (Heart Lung Machine) ለአለም ካስተዋወቀ በኋላ እነዚህን ሕፃናት ወደ ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት የሚያስችለው ICR (Intra Cardiac Repair) መስራት ተቻለ። እናም ይህ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለገለው ቀዶ ጥገና የሚሊዮኖች ሕይወት የታደገና እየታደገ ያለ ቀዶ ጥገና ለመሆን ችሏል።

በ1945 በ Journalist of American Medical Association ላይ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በሦስት ሕፃናት ላይ ስለተገኘው ድል የሕፃናቱም በአንድ ጊዜ ቀይ (Pink) መሆናቸውን የሚያትት ጸሁፍ አወጡ። ይህን ተከትሎ በመላው ዓለም ይህንን ተዓምር የሠሙ ወላጆች ወደ ባለቲሞር John hopkins University ተመሙ። እናም

በ1951 ብቻ የ1000 ሕፃናትን ሕይወት የቀየሩ ስራ (ቀዶ ጥገና) መስራት ተቻለ። (18,19)

*****

የምንሰራው ዘላቂ መፍትሔ የሚሆነውን ICR (Intra Cardiac Repair) የመጨረሻውን ቀዶ ጥገና ነበር። ምንም እንኳን ይህ አራት አይነት የልብ ችግር ያለባቸው (Tetralogy of Fallot) ታካሚዎች የመጀመሪያ ዓመት የልደት በዓላቸውን ከማክበራቸው በፊት ቢሰራ ቢመከርም፤ በሀገራችን ካለው የአገልግሎቱ በስፋት ካለመኖር አንጻር ከነ ችግሮቹ ከፍ ላለ እድሜ ይዘልቃሉ። ይህም በቀዶ ጥገና ውጤት ላይ ከፍተኛ ጫና እንደሚያሳድር ይታወቃል።ወደ ውጭ መሄድ የቻሉ በጊዜ ታክመው ጥሩ ውጤት ለማግኘት ቢታደሉ፤ እንደዛሬው አይነት ታካሚዎችን ግን ለረዥም ጊዜ በመቆየት ለታካሚውም የመከራ ወቅት ለእኛም ከባድ ፈተና ይሆናሉ።

ይህ ቀዶ ጥገና ዋናው ክፍል ሦስት ሲሆን አንደኛው ትልቁን የታችኛው የልብ ግድግዳ ስር ቀዳዳን መዝጋት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከቀኝ ልብ መውጫ ላይ በብዛት የወፈረውን ጡንቻ በመቀነስ ደም በተሻለ ወደ ሣንባ የደም ቧንቧዎች እንዲሔድ ማድረግ የሚያስችል



ስራ ነው። ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ወደ ሣንባ የሚወስዱትን የደም ቧምቧዎች የማስፋት የጥገና ስራ ነው።

በአስገራሚ ሁኔታ የዚህ የመጀመሪያው የ TOF ቀዶ ጥገና ከቀዶ ጥገና ክፍል እስከ ICU ያለምንም እንከን በሠላም ተከውኖ አለቀ። ይህም ታማሚውን በፍጥነት አገግሞ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አስቻለው። ለዘመናት በጥቁርነቱ የሚያውቁት አባቱን ጨምሮ ልጃቸው እንዲህ ቀይ ሆኖ ጣቶቹ እና ከንፈሮቹ ተፈጥሯዊ ቀይ መልክ ይዘው በዩ ጊዜ ለጅትን ተገረሙ፤ ተደነቁም፤ አመሰገኑም።

ስድስት ችግሮች አንድ ታካሚ በአንድ ቀዶ ጥገና ለመስራት ወስነናል። ህፃን ታካሚና ሐኪም እናቱ ከብዙ መመላለስና እንግልት በኋላ በሆስፒታላችን ገብተው የመጨረሻ ፍርድ ሊያገኙ ነው።

ይህ ሁሉ ችግሮች በአንድ ታካሚ ላይ መከሰታቸው እንድፈራ አላረገኝም፤ ጭራሽ የመስራት ፍላጎቱን ከፍ እንዲል አደረገው እንጂ። እንግዲህ እንዳልኳችሁ የሐኪም ልጅም ነች። ጫናው ምን ያህል ለበረታብኝ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። የሆነው ሆኖ ዛሬም ይህችን ሕፃን ለመታደግ ቀዶ ጥገናውን ጀመርን።

ደረት ከፍተን የደም ዝውውርን ለማሽን የመስጠት ሂደቱን (Set-

CamScanner

ting & Going on bypass) በሰላም አጠናቀቅን። ልብና ሳንባን አቁመን ልብን ከፈትን።

ታዲያ ዋነኛውን የቀዶ ጥገና ክፍል ለመስራት በቀኝ የልብ በር በኩል ማለፍ ግድ ይል ነበርና ባገኘሁት ነገር ተደናገጥኩ።

ለደቂቃዎች ብዙ ትግል አደረኩ። ይህ በር ፈፅሞ ከጠበቅነው ውጭ ጠባብ ነበር። በበቂ ሁኔታ በሽታውንም ሆነ ታካሚዋን አልተረዳንም ብዬ ጠረጠርኩ። በሽታውንም ያላወቅን እስኪመስለኝ ተጠራጠርኩ።

በመጨረሻም ቀዶ ጥገናውን ማቋረጥ እንዳለብኝ እና ምናልባት በሰላም ካለፈችው ወደፊት በበቂ ጥናት እንመለስ ይሆናል ብዬ ከራሴ ጋር ተማከርኩ።

ውሳኔው እጅግ መራር እና ለመዋጥ የሚከብድ እንደሚሆን ግልፅ ነበር። ለቤተሰብ ደግሞ ከሁሉ የከፋ ነበር። አንድ የመጨረሻ እድል በተረጋጋ በሰከነ መንፈስ ልሞክር ብዬ ራሴን ሰብስቤ በዚያች እጅግ በጠበበ በር እየተሽሎከለኩ በከፍተኛ ጭንቀት እና ስቃይ የታችኛውን የልብ ግድግዳ ክፍተት መዝጋት ቻልኩኝ። ሌላው የቀዶ ጥገናው ቀጣይ ክፍሎች እዳው ገብስ ነበር።ሁሉንም የቀዶ ጥገና ክፍሎች አጠናቀን ልብና ሳንባን ወደ ተፈጥሮው ስንመልሰው የልብ ምት መቆረጥ (atrio ventricular conduction block) አለመከሰትን ስንመለከት ደስታዬ ልዩ ሆነ።



ስድስቱንም ችግሮች የፈታንበት ይህ ቀዶ ጥገና በሰላም ተጠናቀቀ። በፅኑ ታማሚ ክፍል ውስጥ ቆይታዋም ችግሮች የበዙበት ሆነ። ከቀኝ ሳንባዋ ክፍል እንደ ወተት የሚፈሰው (Chylothorax) ሌላ ቱቦ በቀኝ ሳንባዋ በኩል እንዲገባ አስገደደን። ኢንፌክሽንን ለመቋቋም አቅም የሚያሳጣ እና አመጋገብን የሚያዛባ ዋንኛ የዚህ አይነት ቀዶ ጥገና የነገ ችግር ነበር። ከባድ ጉዳት የሚያስከትለው ይህ ችግር በረዥም ጊዜ ሂደት ተፈታ።

በመጨረሻም ይህች ሕፃን ከሐኪም እናቷ ጋር ከሆስፒታል በሰላም ስትወጣ የተነሳሁት ፎቶ ከአዕምሮዬ የማይጠፋ ልዩ ስጦታዬ ሆኖ ይኖራል።

*****

እንዲህ ያለ ችግር ያለባቸው ብዙ ታካሚዎች ከሀገራችን እንዳሉ እሙን ነው። በአራት ዓመት በሀገሬ የሠራኋቸው የልብ ቀዶ ጥገናዎች ከ300 በላይ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ይህንን (Tetralogy of Fallot) ለመስራት የቻልኩት ግን ለስድስት ሠዎች ብቻ ነበር።ተጋድሎ የበዛባቸው ቢሆንም ስድስቱም በጥሩ ሁኔታ ወደቤታቸው መግባት ችለው ነበር።ረዥሙም የቀዶ ጥገና ሰዓት፤ ረዥሙም የጽኑ ሕሙማን

ቆይታ፤ የበዙ መድሀኒቶችና መሳሪያዎች መፈለጉና ጥሩ ውጤት ላይገኝ ይችላል የሚሉት ምክንያቶች እንደተፈላጊነቱ በሀገራችን እንዳይዘወተር አስገድዶታል።

በልብ ቀዶ ጥገና ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ቀዶ ጥገና ካለቀ በፅኑ ታማሚ (ICU) ክፍል ውስጥ የሚኖረው ቆይታ በአብዛኛው አስቸጋሪ አይሆንም። ነገር ግን ይህንን ዓይነት (TOF) ቀዶ ጥገና በሕፃናት ላይ ሲከወን የICU ቆይታቸው የተለመደ ላይሆን ይችላል። በበታውም መጠጥ ያለ ዕውቀት ያለው ሀኪምና ነርስ ከማስፈለጉም ባሻገር እጅግ የበዛ መድኃኒት እና መሳሪያ ሊፈልግ ይችላል። በመሆኑም በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ የሚደረገው ከፍተኛ ትግል ሣያንስ እንደገና በ ICU ሙያተኞች ዘንድም እልህ አስጨራሽ ስራ ይፈልጋል።

ታዲያ በሀገሬ በ4 ዓመት ቆይታዬ 6 ብቻ TOF ሠራሁ ስል የብዙ ምክንያቶች ጥርቅም መሆኑ እሙን ነው።






11/ምስል ሀ፤ ከላይ በምስሉ ላይ የተመለከተው በTOF(tetralogy of fallot) የተጠቁ ህፃናት የሚያካሂዱት ዘላቂ መፍትሄ የሚባለው ቀዶ ጥገና (intracardiac repair,ICR) ሦስቱን መሰረታዊ ክፍሎችን የሚያሳይ ነው።

........................................

# 12



## ላያስችል አይሰጥ

በፍጥነት ራሴን በእንዲህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አገኘዋለሁ ብዬ አልጠበኩትም ነበር። ዛሬ በቀዶጥገና ክፍላችን ጠረጴዛ ላይ ያለው በ40ዎቹ መጀመሪያ ላይ ያለ ወጣት ነው። ቀልዱ፣ ጨዋታ አዋቂነቱ፣ ፈገግታው፣ ቀልደኛ ከሚመስለው አፍንጫውና አይኑ ጋር ተደምሮ ውስጥ ያበርራል። እንዴት የበው ልጅ በእንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ተገኝቶም የሰውን ቀልብ እንዲህ በመልካም ይስባል? ሁለቱም ኩላሊቶቹ ከወደቁ ድፍን ሁለት ዓመት ያለፉት ሲሆን በዚህም ጊዜያት ሳያቋርጥ በሳምንት ሦስት ጊዜ የኩላሊት እጥበት ያካሂዳል።

በለጋእድሜውገጠርእንጠርሮጦያፈራውንጥሪትዛሬላይከቤተሰቡ



ጋር ሊያጣጥም ሲል የመጣበት ዱብ እዳ ነበር። እናም ከቤተሰቡና ከሚበላው ቆጥቦ ለዚሁ እያዋለ ለኩላሊት ንቅለ ተከላ ራሱን እያዘጋጀ ነው። ለዚህ ፕሮግራም (ለኩላሊት ንቅለ ተከላ) ተራ ደርሶት አጠቃላይ ምርመራ ሲያካሂድ ታዲያ ሌላ ከሁሉም የገዘፈ ዱብ እዳ ተነገረው።

ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለቅጥ የሚደክመውና ተኝቶ የሚያፍነው ነገር ሠላም ነስቶት ሰንብቷል። በዚያ ላይ አልፎ አልፎ ትኩሳት ሄድ መለስ ይልበታል እህልም እያስጠላው መጥቶ ነበር።

ይኸውም ሁለቱም የግራ ልብ በሮች (Aortic & Mitral Valves) በከፍተኛ ሁኔታ መጎዳታቸውና ወደ ኋላ እንደሚያፈሱ ተነገረው። ከዚያም አልፎ የልብ በሮቹ ላይ ከበድ የሚባል ኢንፌክሽን የሚታይ መሆኑ ተነግሮታል። ይህ ሁኔታ (Infective Endocarditis) በመባል ይታወቃል።

ሰው ብርቱ ነውና ያንን ክፉ ጊዜ ከቤተሰብ ጋር ሆኖ አለፈው። ለስድስት ሳምንታት የሚሰጠውን የልብ በሮች ኢንፌክሽን ሕክምናም ተከታትሎ ጨረሰ።ከመፅናናት አልፎ ይህ ወጣት እኔም ጋር መጥቶ የልብ ቀዶ ጥገና (ለዚያም ሁለት የልብ በሮች መቀየር) እንዲደረግለት ሲያናግረኝ እጅግ በሚያስገርም የመንፈስ ጥንካሬ ነበር። ደስ የሚል ስሜት ያጫውትሃል፤ በየነገሩ እንዴት እንደሚቀልድ የሚያውቅ! ቀኑን ሙሉ ብታወራው የማይሰለች አይነት ሰው ነበር። ሁላችንም

ስለራሳችን እንድንመለከት እና እንድናስብ የሚያደርግ አይነት ስብእና የተላበሰ ግለሰብ፡፡ በዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያለምንም ተስፋ መቁረጥ ነገ ጥሩ ይሆናል በሚል ስሜት ማንንም ሳይረብሹ እና ጭራሽ ለሌሎች ድሎት ደባብ መፍጠር የሚችል ስብእና እንዳለው በአይኔ በብረቱ ዓይቼ መሰከርኩ አስቀናኝ፡፡

ታዲያ ዛሬ በሀገሬ ምድር እንዲህ አይነት ከባድ ሁኔታ ላይ ያለውን ወጣት ደረት ከፍተን ልብና ሳምባን አቁመን ሁለት በር ልንቀይር በቀዶ ጥገና ዙሪያ ተገኘን፡፡

*****

በ1968 በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ኩላሊታቸው የማይሰራ ታካሚዎች የአንድ ቫልቭ ቅየራ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን ያወሳል፡፡ በዓለማችን በኩላሊት እጥበት ላይ ሆነው የቫልቭ ቅየራ የተካሄደላቸው ብዙ አይደሉም፡፡ ሲቀጥል የሁለት ቫልቭ ቅየራ የልብ ቀዶ ጥገና ሲሆን ቁጥሩ ከዚያ እጅግ ያነሰ ይሆናል፡፡ በ1998 በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር የአሜሪካው የልብ ማህበር (AHA/ACC) በእነዚህ ታካሚዎች ላይ የብረት ቫልቩ ከስጋው (tissue valve) ቫልቭ እንደሚመረጥ ቢያወሳም በዚህ ዘመን ይህ ምርጫ ብዙም ልዩነት ላያመጣ እንደሚችል ብዙዎች ይከራከራሉ፡፡



ሁሉንም የሚያስማማው ግን "በቀዶ ጥገናው ህይወታቸው አይተርፍም፤ ታካሚዎችም ከዚህ ከባድ ሁኔታ አይድኑም" በሚል አስተሳሰብ ቀዶ ጥገናውን የሚያጣጥለው አስተሳሰብ ውድቅ ሆነ፡፡ በዚያም አልፎ ይህ ቀዶ ጥገና ከተሰራ በኋላ የተሻለ የኑሮ ጥራት ከመኖሩም ባሻገር ለኩላሊት ንቅለ ተከላ ሊደርሱ እንደሚችሉ ስምምነት አለ፡፡

የልብ ቀዶ ጥገናው በጥሩ ሁኔታ መከወን ከተቻለ እንዲሁም ከቀዶ ጥገናው በኋላ በፅኑ ታማሚ ክፍል ተገቢው እንክብካቤ ከተደረገ ወደ ኩላሊት እጥበታቸው መመለስ ይቻላል፡፡

አንዳንዶች እንዲህ አይነቱን የቀዶ ጥገና የሞት መጣያ ወይም ምክንያት ከመሆን የዘለለ ፋይዳ የለውም ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አይሆንም ብሎ ከመግፋት እና የፈጣሪን ሚና ከመጫወት "ይህ ሰው በዚህ ቀዶ ጥገና ይሞታል" ከማለት ይልቅ የሙከራ እድል ሊሰጣቸው ይገባል ይላሉ፡፡ በመቀጠልም ከኃላፊነት ራስን ማሸሽ ተገቢ እንዳልሆነ እና ከፍተኛ ውጤት በእነዚህም ታካሚዎች ላይ ማግኘት እንደሚቻል በጥናት ታውቋል፡፡ (20)

*****

ለሳምንታት የተዘጋጀንበት ይኸው አፕሬሽን በከፍተኛ ጥንቃቄ ተጀምሮ አለቀ። ይህ ነው የሚባል አንድ ችግር ሳይገጥመን ታካሚያችን ፅኑ ታማሚ ክፍል በሰላም ደረሰ። ብዙም ሳይቆይ ከማሽን ተላቆ በራሱ መተንፈስ ቻለ። ሁላችንም ተንፈስ አልን።

ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን ኩላሊቱ ምንም ዓይነት ሽንት ስለማያወጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻው ጉዳይ ነበር። ከኩላሊት ስፔሻሊስት ሐኪሞቹ ጋር እየተመካከርን ያንን ቀን በሰላም ካለፍን በኋላ በሁለተኛው ቀን ብዙ የሚንቀሳቀሱ ቱቦዎችን አውጥተን ወደ ኩላሊት እጥበት መሄድ ተቻለ። እናም የመጀመሪያ የኩላሊት እጥበት ከትልቅ የልብ ቀዶ ጥገና በኋላ በሀገራችን በራሳችንሙሉ እውቀት በሰላም ተካሄደ።

በቀጣይ ቀናትም በምክክር በሰላም ታለፈ ታካሚያችንም ወደ ወትሮው የሳምንት ሦስቀናት የኩላሊት እጥበት በሰላም ተሸጋገረ።

በሀገራችን እንዲህ ዓይነት የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲህ የተሳካ ስራ በሙሉ የሀገራችን ባለሙያ ሲሰራ ማየት ያስደስታል። ለታካሚውም ከሚወዷቸው ቤተሰብ በምቾት እና በፍቅር ተከበው እንዲህ ዓይነት ግልጋሎት ማግኘት መቻል ትልቅ ነገር ነው። ለሀገርም ከከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚታደግ ከፍተኛ አገልግሎት ነበር።



ይህን ቀዶ ጥገና ባደረግን በሁለት ወር ውስጥ ዓለማችን በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በመመታቷ ታካሚያችን የኩላሊት ንቅለ ተከላ ተስፋ ለተወሰነ ጊዜ በስጋት ውስጥ ወደቀ። ምክንያቱም አንደኛ በሀገሪቱ የሚሰጥ የነበረው የኩላሊት ንቅለ ተከላ አገልግሎት ተቋረጠ። ሲቀጥል ደግሞ ተዳዳኝ በሽታ ያላቸው ሰዎች የዚህ በሽታ ሰለባ መሆናቸው ነበር።

*****

አንድ ቀን ታዲያ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል "ተረኛ ሐኪም ነኝ" ያለ አንድ ዶክተር ደወለልኝ። "እከሌ የሚባል ታካሚ በ ኮቪድ-19 ተይዞ ፖዘቲቭ ሆኖ እኛ ጋር ተኝቷል። በመሆኑም ስለነበረው የልብ ችግርና ስለተሰራው አፕሬሽን እንድትነግረኝ ነበር" አለኝ። እጅግ በጣም ደነገጥኩ። ይህ ታካሚ ከላይ ታሪኩን የማጋራችሁ ሰው ነበር። በፍፁም እንደማይተርፍ ተሠማኝ። የተጠየቀውን ከማስረዳት ይልቅ ያለበትን መጠየቅ ሆነ ስራዬ፤ ሐኪሙም ካረጋጋኝ በኋላ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለና የኩላሊት እጥበት ለሚያካሂዱ ሰዎች በሚደረግ ምርመራ ፖዘቲቭ ሆኖ ስለተገኘ እንጂ ምንም ምልክት እንደሌለበት አስረዳኝ።

ቀጥሎም ሊደረግለት ስለሚገባው ልዩ እንክብካቤና ስለመድኃኒቶቹ ከተነጋገርን በኋላ በየጊዜው ሁኔታውን እንዲነግረኝ ጠይቄው ተለያየን።

በአስገራሚ ሁኔታ ለሦስት ሳምንታት በማቆያ ያለምንም የኮቪድ በሽታ ምልክት ቆየ። በምርመራም "ኔጌቲቭ" ተብሎ ከሆስፒታል በሰላም ወጣ።

*****

በአንድ የተመለለሽ ቀን ቀጠሮ ቀን እንደ ሐኪምና ታካሚ ሣይሆን እንደ ቤተሰብ እያወራን ሳለ፤ በድንገት ስለ ልጆች ተነስቶ ማውራት ጀመርን። ለልጆቹ ያለውን ስሜትና ፍቅር ሲነግረኝ ያ የማይሰበረው በለ ጠንካራው መንፈስ ባለቤት፤ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት ዕንባዎቹ ዝርግፍ ዝርግፍ፣ ከማለታቸው ባሻገር የለቅሶው ሲቃ ሁላችንም መቆጣጠር ወደማንችለው ለቅሶ ውስጥ ከተተን።"ይሔን ሁሉ የማደርገው እነኚህ ጨቅላ ልጆቼ ሲያድጉ ለማየት ነው። "እነርሱን እንደማየት የሚያደስተኝ ነገር የለም" እያለ እርግፍ እርግፍ ብሎ ተንሰቀሰቀ። ማፅናናት ሳይሆን ሁላችንም አብረን አለቀስን። ያፅናናን ከሆነ ብለን ተቃቅፈን ሁላችንም አለቀስን።

ዛሬ እነሆ ከቀዶጥገና በኋላ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሆኖት በሀገራችን የሚሰጠው የኩላሊት ንቅለ ተከላ ተስፋ በ ኮቪድ-19 ምክንያት ስለጠፋ ይኸው ነፊማሳ ውጭ ሀገር ሄዶ የኩላሊት ንቅለ



ተከላ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ይገኛል።"መልካሙን ሁሉ ይግጠምህ። ሁሉን የሰጠህ አምላክ የሚበጅህን ያርግልህ" ከማለት በሻገር ምን ይባላል?

የሁለተኛው ታካሚያችን የሚለየው ልቡ ላይ ያጋጠመው በቀኝ በኩል በድንገት ዕጢ በቅሎ መገኘቱ ነበር። ከመጀመሪያ ልምዳችን በተገቢው መንገድ ተጠቀመ። እናም ይህንን የልብ ቀዶ ጥገና በሰላም ሠርተን ወደ ኩላሊት እጥበቱ መመለስ ቻልን። እኔም በሀገሪቱ በሙሉ የኢትዮጵያ ቡድን የልብ ቀዶ ጥገና በጀመርኩ በ4 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ልምድ እና አጋጣሚዎች ይኖራሉ ብሎ በጭራሽ አላበውም አልሜውም አላውቅም ነበር።



12/ምስል ሀ፤ የዚህን ታካሚ ቀዶ ጥገና በጎበኘን ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ሰመመን ቡድን ሳይቀር እንዲህ ለሦስት ከበው በከፍተኛ ጥንቃቄና ውጥረት ነበር ለቀዶጥገና ሲያዘጋጁት የነበረው።



# 13

## አትረፍ ያለው,,,,

አንድ በጣም የማውቀው የሴት ድምፅ፤ ነገር ግን መተንፈስ የቸገራት ድምፅ፤ የደረሰልኝ ጥሪ አስማቸኝ። ምንድን ነው የተፈጠረው? ከ2 ወር በፊት ሁላችንም ከኮራንበት የድጋሚ (Redo) ቀዶ ጥገና በስኬት ያጠናቀቅነው ስራ ነበር፡ እናም በሰላም ከሆስፒታል ወጥታ ነበርና፤ የሆነውን በለማመን በፍጥነት ወደ ልብ ማዕከል እንድትሔድ (እንዲወስዷት)፤እኔም ወደዚያው እየመጣሁ መሆኑን አሳውቄ ስልኩን ዘጋሁት።

### ከ10 አመት በፊት፤

ከ10 ዓመት በፊት ሁለት የልብ በሮቹ ከቶንሲል ጋር ተያይዞ በሚከሰት የልብ በሮችን በሚጎዳው (Rheumatic Heart Disease)

በሽታ ምክንያት በቀዶ ጥገና አስቀይራለች ። ሁለት የልብ በሮችን የመቀየር የልብ ኦፕሬሲዮን ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ቀዶ ጥገናዎች ይመደባል። ይሁን እንጂ ይህች ሁልጊዜም ፈገግታ ከፊቷ የማይለያት ፍልቅልቅ በሃያዎቹ መጨረሻ ላይ የምትገኝ ሴት ልጅ በስኬታማ ቀዶ ጥገና አድርጋ፣ እነሆ ይኸው ከ10 ዓመት በኋላ እየተከታተልናት ነው።

በዚሁ በልብ ማዕከል በኢትዮጵያ በርካታ እንደዚህ ዓይነት፤ ቤሳቤስቲን የሌላቸው ምስኪን ኢትዮጵያውያን በነፃ የሕይወት አድን የልብ ቀዶ ጥገና አከናውነዋል። በወቅቱም ከውጭ ሀገር በበጎ ፈቃደኝነት ከመላው ዓለም በየጊዜው የሚመጡ የልብ ሐኪም ቡድኖች ለበርካታ እድለኛ ታካሚዎች መድህን ሆነዋል። አሁንም ቢሆን እየሆኑ ይገኛሉ።

ታዲያ ይህች ምስኪን ፍልቅልቅ ከዚህ ከፍተኛ የልብ ቀዶ ጥገና ተርፋ ለእድሜ ልክ የማይቋረጠው የልብ ሕክምና ክትትል ውስጥ ለመቀጠል የኢኮኖሚ አቅም አልነበራትም። ራሴ ከሰራኋቸው ቀዶ ጥገናዎች ባሻገር በሌሎች ቡድኖች ከተሰሩ የቀዶ ጥገና ታካሚዎች መካከል ይህች ወጣት አንዷ ነበረች። ከሁሉም ባሻገር ከአስቸጋሪ የጤንነት ሁኔታ ጋር የማይጣጣም የጥበቃ ስራ መስራቷ ይበልጥ የሚያሳዝን ጉዳይ ነበር።

ታድያ በአንድ ከስራ ውጭ በለ ቀን የደወለችልኝ ከልብ ጥን



በአደገኛ ሁኔታ ላይ መሆንዋን የሚያሳብቅ ነበር። መናገር እያቃታት፤ ቁርጥ ቁርጥ በለ ድምፀ፤አየር እያጠራት ያለችበትን ሁኔታ አስረዳቺኝ። በአስቸኳይ የፅኑ ሕክምና ክፍል ክትትል የሚያፈልገው ሁኔታ ላይ መሆኗን ተረድተን ወደ ልብ ሕሙማን በፍጥነት እንድትመጣ አድርገን አስተኛናት።

ነገሩ እንዲህ ነበር። በአንደኛው የተቀየረላት የልብ በር (Mitral Valve) ደም መፍሰስ ጀምሮ ነበር። ይኸውም ምክንያቱ በሁለት ጉዳዮች ሊሆን ይችላል። አንደኛውና ዋነኛው የደም መወፈርና መርጋት ሊያስከትል የሚችለው ሲሆን ምክንያቱም ደሟ መቅጠን የሚገባውን ያህል ሳይቀጥን ሲቀር ነው። ሁለተኛው ምክንያት በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ወደ ልብ በሮች ውስጥ የሚያደርግ ስጋ ሊሆን የሚችልበት ሁናቴ ነበር።

እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉት ሁለት ጉዳዮች ናቸው። ይኸውም እጅግ በጣም ውድ በሆኑ የደም ማቅጠኛ መድሀኒቶች በመጠቀም የረጋውን ደም ከተጋገረበት የልብ በር ላይ የመበተን ሙከራ ሲሆን ይህ ካልተሳካ ደግሞ የድጋሚ ቀዶ ጥገና በማድረግ የበፊቱን ቅያሪ ቫልቭ በማውጣት (Explanting) እንደገና ሌላ አዲስ ቫልቭ ማስገባት አማራጮች ናቸው።

ምንም እንኳ ውድ ቢሆንም የመጀመሪያውን አማራጭ መሞከር

ሁሉም ቢሆን ተገቢ ነው። ሁለተኛው አማራጭ ሕይወትን በከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል እና ከፍተኛ የደም መፍሰስ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ እጅግ የተፈራ ቀዶ ጥገና ነው።

የተከሰተው ግን እንደዚህ ነበር። ሁኔታዋ በህይወትና በሞት መካከል ሆና የመተንፈሻ መሣሪያ (Ventilator) አስፈለጋት ።ከ24 ሰዓት ትግል በኋላ ሁኔታዋ በከፊል በመሻሻሉ ከመተንፈሻ መሳሪያ ተላቀቀች። ይሁን እንጂ ዋነኛውን የልቧን በር የዘጋውን እና በሩን አላስከፍት ያለውን የደም መርጋት "ሊሆን ይችላል" የሚል መላምት ነው፤ ለማቡተን እጅግ በጣም ውድ የተባለውን መድኃኒት መሞከር ነበረባት።

እንዳሁ በማደግ ላይ ባለን ሀገሮች አንድ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና በነፃ ማግኘት በራሱ ትልቅ ዕድል ሲሆን፤ እንደዚህ ዓይነት እልህ አስጨራሽ፤ የአንድን ሰው ሕይወት ለማትረፍ ትግል ማድረግ እጅግ ያልተለመደ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ካለው ከፍተኛ የመሳሪያዎች አቅርቦት (Re-source limitation) እጥረት በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ ዕውቀት የሚፈልግ እና የሚጠይቅ ስለሆነ ነው። በተለይም ሁሉንም በነፃ በሚያገለግል አንድ ሆስፒታል እና እጅግ የበዙ ታካሚዎች የመጀመሪያ እድል ሳያገኙ በሚመላለሱበት ሀገር በአንድ የሕክምና ተቋም ላይ እንዲህ ዓይነት ርብርብ ለብዙዎች ምሳሌ የሚሆን አስደናቂ ተሞክሮ ነው።



ስለዚህ በከፍተኛ ጫና ውስጥ ያለው የልብ ሕሙማን በኢትዮጵያ፤ ለዚህች ፍንድቅድቅ 'ዛሬ ግን ትንፋሽዋ የራቃት ወጣት ሴት' እድሉን አልነፈጋትም። ይልቁንስ በከፍተኛ ተነሳሽነት የሚቻለው ሁሉ እንዲደረግና መድኃኒቱም ተገዝቶ እስከመጨረሻው የሕይወት አድን ፍልሚያ እንዲካሔድ ወሰነ። መድኃኒቱም በብዙ ፍለጋ ተገኝቶ ተገዛ። በከፍተኛ ክትትል ውስጥ ሆና ይኸው መድኃኒት ለ24 ሰዓት ሳይቋረጥ ተሰጠ።

ይሁን እንጂ ውጤቱ አመርቂ አልነበረም፤ ሁኔታዋ መለስተኛ በሚባል መልኩ ለውጥ ቢያመጣም የልጅቷ ሕይወት በቋፍ ላይ እንደተንጠለጠለ ቆየ።

እናም የሚቀጥለው ውሳኔ እጅጉን ከባዱ ነበር እዎን ያለው አማራጭ የተዘጋውን ነገር እንደገና ደረትን ከፍቶ፤ ልብን እና ሳንባን አቁሞ፤ ልብን ከፍቶ በማየት የተዘጋውን የቀድሞ ቫልቭ ማውጣትና በአዲስ መቀየር ብቻ ነበር።

*****

በ United Kingdom Heart Valve Registration ለ10 ዓመታ (ከ1986-1995) በተከታተሏቸው፤ የልብ ቫልቭ የተቀየረላቸው ታካሚዎች 2.43% የእንደገና የልብ በር ቀዶ ጥገና (Redo Surgery) ሊያፈልጋቸው እንደሚችል ከማተቱም በላይ በአንደኛው የግራ የልብ በር በታ ላይ (Mitral Valve) እና በወንዶች በከፍተኛ ሁኔታ የመከሰቱ ዕድል ከፍ ያለ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። (21)

በሦስት ዓመት የህንድ ሀገር የልብ ቀዶ ጥገና ትምህርት ቆይታዬ የ Redo (ድጋሚ) ደረት ከፍቶ ቀዶ ጥገና ብዙ ትዝታዎች ነበሩኝ። ተመድቤ በምማርበት የ 4 እና 5 ቁጥር የዶ/ር Pv. Rao ቀዶ ጥገናን ክፍሎች ውስጥ የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና (Redo) ቀዶ ጥገናዎች ያልተለመደ አይደለም ። የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና (Redo) ቀዶ ጥገናዎች በሉ ጊዜ ያለው ሽርጉድ ይበዛል። ጭንቀት እና ጥንቃቄ ከዝግጅት አንስቶ ደረት ተከፍቶ እስኪያበቃ ከባድ ነው። በከፍተኛ የደም መፍሰስ መረበሽ እና ሲብስም ሕይወት ሲያልፍ ገጥሞን ያውቃል። ከዚያም በሻገር ከሌሎች ወንድም እህት የቀዶ ጥገና ክፍሎች በተደጋጋሚ እንዲሁ አይነቶች አስፈሪ የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና (Redo) ቀዶ ጥገና ክስተቶች መስማት ያልተለመደ ጉዳይ አይደለም።

በሁሉም የሚገርመኝ አንድ ጉዳይ ግን በዚሁ የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና (Redo) አፐሬሽኖች ነበር። ይህንን ቀዶ ጥገና ስንከውን



የሚደረጉ ቅድመም ሆነ ደረት በመክፈት ሂደት ውስጥ ስፌ ነው ይገበዋልም። በህንድ በዚሁ በ Narayan Institute of Cardiac Science የተለመደው አንድ ጉዳይ አለ።

ዋናው እና ጉምቱው መምህር Professor የሚመጣው ደረት ከተከፈተ በኋላና የደም ዝውውር ለልብና ሳንባን ስራ ተክቶ ለሚሰራው (Heart Lung Machine) ከተሰጠ በኋላነው። በመሆኑም የዋናው ቀዶ ጠጋኝ ስራ፤ የሠርጀረውን ዋናውን ክፍል (ለምሳሌ ቫልቭ ከሆነ ቫልቩን መቀየር የደም ስር ባይፓስ ማድረግ ከሆነ የልብ ላይ የደም ቧንቧን ማገናኘት፤ የተፈጥሮ ክፍተት ከሆነ ክፍተቱን መዝጋት) ሰርቶ መሔድ ብቻ ነው። ነገር ግን በዚሁ የድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና (Redo heart surgery) ቀዶ ጥገና ላይ ግን፤ ዋናው ቀዶ ጠጋኝ ገና ከዚሁ ከደረት መከፈት ጀምሮ መገኘት ግዴታው መሆኑ ነው። እንደዚያም ሆኖ ግን የሚነሱት አደገኛ ነገሮች ከመከሰት ወደ ኋላ ያሉበት ጊዜ አልነበረም።

በድጋሚ በሚከፈት ደረት ላይ የሚደረገው የልብ ቀዶ ጥገና ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ አከናውኜ ነበር። በተለይም የመጀመሪያው የድጋሚ (Redo) ቀዶ ጥገና የተለየ ነበር ። ይኸውም አንድ ከ10 ዓመት በፊት ከውጭ አገር በሚመጡ የበጎ አድራጊ ሀኪሞች አንዱን የልብ በር ቫልቭ የተቀየረላት ጎልማሳ ነበር። በወቅቱ ሙሉ በሙሉ የልብ ምቱ ከቀዶ ጥገናው በኋላ በመቋረጡ (Complete Heart Block) የአርቴፊሻል

ባትሪ (Pace Maker implementation) አስፈልጎት ነበር ። በዚህም ምክንያት ወደ ሕንድ ሀገር በመሔድ በውቀቱ ቀዶ ጥገናውን አከናውኖ ተመለሰ።

ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ የ Pace Maker ባትሪ ኢንፌክሽን ስለፈጠረ፤ በድጋሚ ወደ ሕንድ ሄዶ የነበረ ቢሆንም ይህንኑ የተበከለ ባትሪ (infected Lead) በታ ላይ ገመተው ሌላ Pace Maker በቀኝ በኩል አስገብተውለት ይመለሳል። በዚህም የተነሳ በተደጋጋሚ ሆስፒታል መተኛትና ኢንፌክሽኑ መታከም ግድ ይሆንበታል። የመጨረሻ መፍትሄውም ይህ እንደገና ቀዶ ጥገና በማድረግ የተበከለውን የባትሪ ገመድ (batrey lead) ማስወገድ ነበር።

እነሆ እኔም የመጀመሪያው የ Redo (ድጋሚ) ደረት ከፍቶ የመስራት ቀዶ ጥገና ይኸው ታካሚ ሊሆን ቻለ። በዚህ ቀዶ ጥገና በድጋሚ ደረት ከመከፈት በሻገር ኢንፌክሽን የፈጠረውን የተበከለውን የባትሪ ገመድ (batrey lead) ከቀኝ የታችኛው የልብ ክፍል (right ventricle) ጀምሮ ወደላይ እስከመጨረሻ ባትሪው እስካለበት ድረስ ተከትሎ ማውጣት ነበር። ቀዶ ጥገናው ቀላል አልነበረም፤ ሆኖም ተሳካ። ጎልማሳም ከዚህ ከማይቋረጥ ኢንፌክሽን ተገላገለ።

በዚህ ሁኔታ የ Redo ኦፕሬሽን የጀመርኩ ቢሆን በቀጣይ ግን የሠራሁት አንዷት በዕድሜ የገፉ እናት ላይ ሲሆን ይኸውም ከ12



ዓመት በፊት በግራ የልብ በር (mitral valve) የገባው የ Tissue Valve (ከሠውነት ጋር ተመሳሳሎ የሚሰራ የቫልቭ ዓይነት ነው) በማርጀቱ እና ደም በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኋላ በመፍሰሱ ነበር። ይኸም ቀዶ ጥገና ያለምንም እንከን የተጠናቀቀ ነበር።

*****

ምንም እንኳን ከፍተኛ ትግል የሚጠይቅ ቀዶ ጥገና ቢሆንም አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋችንን ከማረጋገጥ ባሻገር ለውሳኔ አልተቸገርኩም ነበር። በዚህም መሠረት ሁሉም ዓይነት የደም አይነቶችና ውጤቶችን አዘጋጅተን በድጋሚ የዚህችን ወጣት የተዘጋውን እንደኛውን የግራ የልብ በር (mitral Valve) ለመቀየር ወስነን ወደ ቀዶ ጥገና ገባን፡

ምናልባት ከፍተኛ ጥንቃቄ ስላደረግን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን 35 የደም ዓይነት አዘጋጅተን የገባንበት ይህ ቀዶ ጥገና በሰላም ተጠናቀቀ። በ ICU እና በዋርድ ቆይታዋን ጨርሳ ስትወጣ አንድም ደም አልተጠቀምንም ነበር። በድል ስሜት ተዋጥን። ችግሯ የነበረው ቫልቩ ላይ የደም መርጋት ብቻ ሣይሆን ወደ ቫልቩ ውስጥ ያደገው ስጋ ቫልቩን እላስከፍት ብሎት ነበር። እናም በአዲስ ቫልቭ ቀየርነው።

ለዚህች ወጣትም አዲስ ሕይወት ለሁለተኛ ጊዜ ተሰጣት። የመቻልና የመብቃት ስሜት ደስ ይላል ።በተቀረው የአለም ክፍል እኩል መስራትና መብቃት በተግባር አሳየን። ይህም አለን። ይህ በምንም ዋጋ አይተመንም።

እንግዲህ ብዙ አንቀው በሚይዙ ሁኔታዎች በምሉባት ሀገር ውስጥም ሆነን ትልቅ ትግል አካሂደን ውጤት በማሳየታችን የመላው የልብ ሕሙማን ትልቁ የኩራት ምንጭ የሆነ ውጤት ተመዘገበ።

*****

እናም ይህችው ልጅ ነበረች ከ2 ወር በኋላ በድጋሚ የቀየርነው ቫልቭ ተዘግቶ መተንፈስ ተስኗት በሲቃ ውስጥ ሆና የደወለችው። አቤት ጣጣ ምን የሚሉት ፈተና ውስጥ ገባች /ገባሁ። ከፍተኛ ግርምት ፈጠረብኝ ። በእርግጥ በዚህ ጊዜ ውስጥ ደሟ ወፍሮ (ረግቶ) ቫልቩን ከመዝጋቱ ውጪ ሌላ ጉዳይ ሊሆን እንደማይችል ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማሰብ ይቻል ነበር።

አንደኛ ይህንን እጅግ ውድ መድኃኒት በድጋሚ እንዴት ማግኘት ይቻላል? ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የበለፈውን መድኃኒት በድጋሚ



መውሰድ ስለማይችሉ የዚሁ ዘር ሆኖ ሌላ ዓይነት መሆን ግዴታ ነበረበት። ይህም ተጨማሪ ዋጋ የሚጨምር ጉዳይ ያደርገዋል።

እናም ሁኔታው ለልብ ሕክምና ማዕከል ኃላፊዎች አስረዳሁ ። ያላት ምርጫ ይህንን መድኃኒት መሞከር ብቻ መሆኑን አስረግጠው ተናገሩ። ይህ በበጎ አድራጊዎች ስጦታ የቆመ ቤት ለመላው ኢትዮጵያዊያን የሚገኘውን ዕርዳታ በተቻለ መጠን አብቃቅቶ መስራት እንደሚገባው እሙን ነው። ታዲያ ይህ ሁሉ ሀብት አንድን ሕይወት ለማዳን ማዋል ለዚያውም ላይሳካ ይችላል የሚለው ምልከታ እንዳለ ሆኖ ተገቢ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀየር ጉዳይ ነበር።

ነገር ግን ሁላችንም በአንድ ቆምን። አዎን፤ የልብ ማዕከሉ አስተዳደርና ኃላፊዎች የዚህችን ምስኪን ሕይወት ለማዳን እስከመጨረሻው ትንፋሽ እንሞክር የሚል ውሳኔ በድጋሚ ሆነ። ቀጥሎም ይህንን መድኃኒት ማፈላለግ ተያያዝን። በመጨረሻም ማግኘት ተቻለና በከፍተኛ ወጪ ተገዛ።

የሚያስገርመው ይህንን መድኃኒት ለመስጠት እንኳ ከፍተኛ ጥንቃቄና ዕውቀት ይፈልግ ነበርና ልክ እንደ ቀዶ ጥገና ታካሚው መድኃኒቱን ለመውሰድ መፈረምም ግዴታው ነበር። እናም ፈርማዋን [illegible] የተለመደው ፍልቅልቅ ፈገግታ ፊቷ ላይ በግ ብሎ ይታይ

ነበር። ቅናት ቢጤ ተሰማኝ። አንድ መምህሬ "በማንኛውም ችግር ውስጥም ሆነህ ፈገግታ አይለይህ" የሚለው ታወሰኝ።

ለሁለተኛ ጊዜ የተሰጣት ይኸው የረጋን ደም የሚያላላው መድኃኒት አስገራሚ ውጤት አሳየን። እናም ትንፋሿ ተመልሶ ተረጋጋ።

ወጣቷ ፍልቅልቅ የድህነት ኑሮ በአንድ በኩል ሲያንሳቁላት በሌላ በኩል "ሕይወትሽን ካልነጠቅንሽ" የሚለው ተደጋጋሚ በሽታዋ ምቾቷን እድሜዋን በሙሉ ነስቷታል።

ጤንነቷ ተመልሶ በድጋሚ ወደ ቤቷ ስናሰናብታት ስንዘጋጅ የልብ ማዕከሉ እንደዚህ ዓይነት ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሕይወት አድን ተጋሎን በሙሉ የሀገራችን ልጆች ማድረጉ ትልቅ ክብር ያሰጠዋል። እኛም የዚህ ድል ተቋዳሽ መሆናችን ልዩ ደስታ ይሰጠናል።





13/ምስል ሀ፤በሥዕሉ የተመለከተው ለብዙ አመታት ከገለገለ በኋላ በሀገራችን መሬት እና እውቀት በድጋሚ የልብ ቀዶ ጥገና ያወጣነው እና ተዘግቶ የነበረ ሰው ሰራሽ የልብ በር ነው።

# 14

## ውብት ሲፈነዳ

እድሜዋ በ20ዎቹ መጀመሪያ ነው። በደቡብ ክልል ከሚገኝ አንድ ዩኒቨርሲቲ የ3ኛ ዓመት ተማሪ ብትሆንም በጤና ምክንያት ትምህርቷን መከታተል ተስኗታል። በቀጠሮዋ ቀን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለመገኘት ነበር ትምህርቷን ጥላ አዲስ አበባ የመጣችው። ባለፉት 5 አመታት በየሦስት ወር የልብ ህክምና ክትትል ስታደርግ ያለማቋረጥ መድሀኒት ትወስድ ነበር። በብዙ አጋጣሚ የበሽታዋ መፍትሄ በልብ ቀዶ ጥገና ብቻ መፍትሄ እንደሚያገኝ ቢነገራትም የውጭ ቪዛ ካልመጣ ደግሞ እንደማይሰራ ተነግሯታል። በኋላም በሰዎች ጥቆማ አዲያቸው ጥቁር አንበሳ ቅጥር ግቢ የሚገኘውን የልብ ማዕከል እንድትጎበኝ ተነገራት። እኛም በስተመጨረሻ ከዚህች ወጣት ጋር የመገናኘት ዕድል ገጠመን።



"ለምን እንደሆነ አላውቅም" አለችኝ። እስካሁን የበሽታዬን ምንነት ማንም ሊያስረዳኝ አልቻለም። አሁን ግን ልቤን ለዚህ ለከፋ ደረጃ ያደረሰውና የልብ በሮቼ እንዲጠቡና እንዲያፈሱ የሆኑት ከልጅነቴ ጀምሮ ያጠቃኝ በነበረው የቶንሲል በሽታ ምክንያት መሆኑን ተረድቻለሁ። በደፈናው 'የልብ በሽተኛ' እየተባልኩ የልብ ክፍል እየመጣሁ በየወሩ እነዚህን መድኃኒቶች ከመውሰድ ውጪ ምን እየሆንኩ እንደሆነ አልገባኝም። "ስትል እንባ እየተናነቃት አንጀት በሚበላ ሁኔታ አስረዳችን።" ውስጧ እጅጉን ጨልሟል፤ ሳይደክመኝ የማደርገው አንድም ነገር የለም፤ሀሳቤን ጥዬ እንቅልፍ እንዳልተኛ ደርሶ እንቅ፤ አፍን ያደርገኛል፤ በፊቼ እንዳልጠግብ እሁሉን እንደቀመስኩት ይጨንቀኛል፤ ከሁሉም በላይ ከጓደኞቼ ሁሉ የተለየሁ ሰው ሆኜ መታየቴ እና መገኘቴ ነው" አለችኝ። በሚያስደነግጥ ሁኔታ የበሽታዋን አመጣጥ እና በልብ ላይ ያደረሰውን እና እያደረሰ ያለውን ጉዳት በመረዳቷ እርካታ ብቻ ሳይሆን የሆነ በታ ጎዳ ልትገቀለው ያበቸ እስኪመስል ድረስ ተደሰተች።

በተደጋጋሚ እያገረሸ እና እየተመላለሰ ያስቸግራት የነበረውን የቶንሲል ሕመም በተለያዩ ባህላዊ ሕክምና በብቸኝነት በሰደኃት እናቷ ቀጣሚነት ትታገል እንደነበር የምትናገረው ይህች ወጣት አንድም ጊዜ ለቶንሲል ዘመናዊ ሕክምና ወስዳ አታውቅም ነበር።እናም ዛሬ የልቧን የግራ በር (mitral valve) እንዳይከፈት እና እንዳይዘጋ አድርጎ ያበላሸው ከዚሁ ከቶንሲል ጋር ተያይዞ የሚከሰት የ Rheumatic

Heart Disease (RHD) ነበር። በሽታዋ በዚህ ብቻ ሳያቆም ተባብሶ ወደ ቀኝ የልቧ ክፍል ዞሮ የቀኝ የልቧ በር (tricuspid valve) ከፊቶ ወደኋላ እንዲያፈስ አድርጎታል።

ጊዜ ወስጄ ስላለቸበት ሁኔታ ባስረዳትም፤ የኔ ዓላማ የበሽታውን ምንነት መንገር ማስረዳት አልነበረም። ፍላጎቴና ዓላማዬ ይህንን አላንቀሳቅስ ያላትን በሽታ ምክንያት የሆነውን የግራ ልቧን በር (mitral valve) በአስቸኳይ መቀየርና እንዲሁም ሌላኛውን የቀኝ ልቧ ላይ የሚገኘውን ሌላ ቫልቭ (tricuspid valve) በአስቸኳይ መጠገን ነበር። ነገር ግን ይህቺ ወጣት በሽታዋን በመገንዘብ ብቻ የተሰማት ደስታ እና ያሳየችው እፎይታ ያስተማረኝ ትልቅ ትምህርት ነበር። መናኛነትም የሰጠናትም ተስፋ ተጨምሮ ስንቅ ሆኖትም ይሆናል ብዬም አሰብኩ። የሆኖ ሆኖ ከታካሚዎቼ ጋር አቅም በፈቀደ መጠን ስለ በሽታቸውና ስለህክምናቸው ሂደት እንዲገባቸው ማድረግ ያለውን ልዩ ጥቅም በዚቺ ታካሚ ላይ በየሁት የመንፈስ እርካታ በአእምሮዬ ጓዳ ታትሞ ቀርቷል።

ታዲያ ይህን የልብ ቀዶ ጥገና ማድረግ የምንችለው በልብ ማዕከል ነበር። ነገር ግን ይህችን ታካሚ ከገንዘብ ሰሞን ለዚህ ሰርጀሪ የሚሆን ቁሶች ማሰቃቸው ችግር ሆነ። ሌላው አማራጭ በከተማው የሚገኘው የግል ሆስፒታል መክፈት አለያም ወደውጭ ሀገር መሄድ ነበር።



ነገር ግን ይህች ወጣትና ቤተሰቦቿ ከኪሳቸው ገንዘብ አውጥተው ይህን ቀዶ ጥገናን የሚያህል ውድ ህክምና ለማድረግ ዛይሆን የዕለት ጉርሳቸውን ለመደጎም የሚታገሉ ነበሩ። ከዚህም በሻገር ይህች ለጋ ወጣት ያለአባት ከአንድ እናቷ ጋር ብቻ የሚኖሩ ረዳት አልባ አሳዛኝ ቤተሰብ ነበሩ።

ይህንን ቀዶ ጥገና በልብ ማዕከል እንዳናከናውን መሰናከል የሆነብን ትልቁ የልብን ስራ ተክቶ የሚሰራው ማሽን ላይ የምንገጥመው የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራው (oxygenator) እላቂ እቃ ነበር። በጊዜው በእጃችን የነበረው ይህ እላቂ እቃ በበቂ ሁኔታ ኦክስጅን ማቀበል የሚችለው ከታካሚያችን ክብደት በታች ነበር። የዚህችን ልጅ ቀዶ ጥገና ለመስራት እዚህ መፅሀፍ ላይ መጥቀስ የማልፈልገው ብዙ አማራጮችን ብሞክርም አልተሳካልኝም ነበር። በውስጤ ታካሚዋ የፈጠረችብኝ ስሜት ባይገባኝም የዚህችን ልጅ ቀዶ ጥገና ከመስራት ወደ ኋላ እንደማልል ለራሴ አስረግጬ ነገርኩት።

በመጨረሻም አሰቤ፣ አውጥቼ፣ አውርጄ አንድ ውሳኔ ላይ ደረስኩ። ይኸውም ለታካሚዋም፣ ለእኔም አደጋ (Risk) ያለው አማራጭ ነበር። በልብ ማዕከል ከሚገኙት የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን (Heart Lung Machine) የሚዘውሩት የሚያንቀሳቅሱት በለሙያ ነርሶች ጋር ቁጭ ብለን ተወያየን። ችግሩ በእርሷ ክብደት እና ቁመት የተስተካከለ የሳንባን ስራ የሚሰራ (Oxygenator)

አለመኖር ነበር። እናም አማራጭ ቴክኒክ ለምን አንጠቀምም አሉ። የሠውነትዋን የደም ቅዝቃዜ መጠን ከተለመደው የምንሰራበት ደረጃ በጣም በማውረድ የሠውነታችን የኦክስጅን ፍጆታ በመቀነስ ከዚህ ውድ እሳቤ የሳንባን ስራ ተክቶ ከሚሰራ እቃ የሚጠበቅበትን የሚያቀብለውን የኦክስጅን መጠን መቀነስ ዋናው ዓላማው ነበር።

*****

ካናዳዊው ዶ/ር Wilfred G. Bigelow በ 1950 ሰውነትን የሙቀት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ የልብ ቀዶ ጥገናን የመስራት ፅንሰ ሃሳብ (the conept of hypothermia) ይዞ ብቅ ሲል ለዛሬው የልብ ቀዶ ጥገና ስኬት ከፍተኛ ቦታ ነበረው።

ዶ/ር Bigelow በላብራቶሪ ውስጥ በውሾችና በጦጣዎች ላይ የሰውነታቸውን የደም ቅዝቃዜ ወደ 20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እና ከዚያ በታች ዝቅ በማድረግ ከ 15 እስከ 24 ደቂቃ ድረስ ልብን አያቆመ መመለስ ችሎ ነበር። በቀረበውም ሀሳብ የሰውነታችን የደም ሙቀት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ የኦክስጅን ፍላጎት በሁሉም የሰውነታችን ክፍሎች ማውረድ እንደሚቻል አስረዳ። ይህም ማለት የደም አቅርቦታቸው በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ለተወሰኑ ደቂቃዎች



በጥቂት እሊያም ያለምንም ደም መቆየት የሚቻልበትን ሀሳብ አቀረበ። በዚህ ወቅት ከልብ የሚጠበቅ ስራ ስለማይኖር ልብን ከፍቶ ለመስራት የሚያስችል እድል ይፈጥራል ማለት ነው።

ምንም እንኳን ከክርስቶስ ልደት በፊት በአርስቶትል አስተምህሮ ከሰማይ በሚወርድ በረዶ ቁስልን ማከምና ማዳን በታሪክ የተቀመጠ ሲሆን፤ በመቀጠልም የታላቁ ጦረኛ የፈረንሳዩ ንጉስ ታላቁ ናፖሊዮን ሀኪምም የወታደሮቹን ቁስል በበረዶ ያክም እንደነበረም በሰፊው ይነገራል። ነገር ግን የዚህ "Cold Heart" በሚለው ፅሁፍ የሚታወቀው ካናዳዊ ዶ/ር Bigelow እና ጓደኞቹ የጥናት ፅሁፍ በላብራቶሪ የተደገፈና ዝርዝር በመሆኑ በመላው አለም ያሉ ሀኪሞችም ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና መነቃቃትን ፈጠረ።

በ1952 በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር ዶ/ር John Lewise በሰው ልጅ ላይ ይህንን ሀሳብ እና ደም ወደ ልብ እንዳይገባ (in-flow excusion technique) በመጠቀም በወቅቱ የልብና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራው ማሽን ባይፈበረክም ለመጀመርያ ጊዜ በልብ የላይኛው ክፍል ላይ የሚከሰተውን የተፈጥሮ ቀዳዳ (Atrial Septal Defect) መዝጋት ቻለ።

እንዲሁም እያለ በ29 ሰዎች ላይ የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራው ማሽን (Heart Lung Machine) ባይኖርም ሰውነትን በማቀዝቀዝ

(Hypothermia) ዕንስ ሀሳብ ብቻ በመጠቀም የተወሰኑ የልብ ቀዶ ጥገናዎችን ለመስራት ቻለ። በውጤቱም የ3 ሰዎች ህይወት ቢያልፍም የ26 ሰዎች ህይወት ማትረፍ የቻሉበትን ቀዶ ጥገና ለመስራት በቁ። (22,23)

*****

ምንም እንኳን ዛሬ እኛ የምንሰራው የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን (heart lung machine) በመጠቀም ቢሆንም፤ የሳንባን ስራ የሚሰራው አላቂ እቃ (oxygenator) ለዚህች ወጣት በሚስማማ እና በሚመጥን መልክ ግን አልነበረንም። በመሆኑም የሰውነትን ሙቀት የማቀዝቀዝን ዕንስ ሀሳብ በመጠቀም ለዚህች ወጣት የሚስማማ መፍትሄ አበጀን።

ይህንና ሌሎች ጥቃቅን የመፍትሄ ሀሳቦችን በልብ ማዕከል ከሚገኙት የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን (HLM) የሚዘውሩትና የሚያንቀሳቅሱት በለሙያ ነርሶች ጋር በዝርዝር ተወያየን፤ በችግር ጊዜ ማድረግ ያለብንን ነገር ተነጋግረን ተስማማን። የሚገርመው እነዚህ ሁለት የሙያ አጋሮቼ ከእኔ ብሰው ስሜታዊ ሆነው ይህች ልጅ በተሰካ ሁኔታ ቀዶ ጥገናው እንዲሰራ ቆርጠው ተነሱ።



እናም ዝግጅታችንን ሁሉ አጠናቀን እንሆ በዕለተ ሰኞ ይህችን ወጣት ለመስራት ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ገባን።

በወጠንነውና በቀደነው መሰረት የዚህን የልብ ቀዶ ጥገና አከናወንን። ቀዶ ጥገናው 6 ሰዓት ፈጅቶ ተጠናቀቀ። በፈጣሪ ኃይል የወጠንነው እና ያሰብነው ስራ ተሳካ።

ቀዶ ጥገናው ያለምንም ችግር ተሠርቶ አለቀ። ይኸውም አንዱ የግራ ልብ በር ሲቀየር (Mitral Valve Replacement) ሌላኛው የቀኝ ልብ በር ደግሞ ተጠግኖ (Tricupid Valve Repair) ታካሚዋ ያለምንም እንከን ከቀዶ ጥገና ክፍል ወጣች።

የሚገርመው ለበዙ ዘመን የራቃት አበት አስታማሚ ሆኖ በሆስፒታሉ አዘውትሮ ሲገኝ በብቸኝነት ያሳደጋቻት እናት ደግሞ በህመም ምክንያት በቤት የአልጋ ቁራኛ ሆነው መጥተው ሊያዩዋት አለመቻላቸው ነበር።

ከሁሉም የሚያስገርመኝና በዚህች ወጣት ሁሌም ሲረሳው የማችለው ግን ሦስት ወር በለሞላ ጊዜ ውስጥ በሠውነትዋ ያየው ለውጥ ነበር። በተረያዋ ያሉ ሁሉ በፀት ተገረሙ። ውስጥዋ አንድ ሳይቀር ፍልቅልቅ ብሉ ወጣ። ሠውነትዋ እጅግ በሚያምር ሁኔታ ፋፋ፤ የቆዳዋ ቀለም የሚያምር ቀይ ልጅ ሆነች። ምንም እንኳን ሁሉም

በRHD ተጠቅተው የተበከ ቀዶ ጥገና የሚያካሂዱ ሠውነታቸው በአጭር ጊዜ ቢቀየርም በዚህች ውጣት ላይ ያየነውን ለውጥ ለመርሳት ግን ይቸግር ነበር።

*****

ለመሆኑ 'ይህ ቀዶ ጥገና ባይሰካ ምን ሊከሰት ይችል ነበር' ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። ነገር ግን ይህን የማስበው ቀዶ ጥገናውን ከሰራን እና ሁሉም ከተፈፀመ በኋላ ነው ማለት ግን አይደለም። ከልኝ መጠነኛ ፈሳሽና ውስጤ ከሚነግረኝ (intusion) መልካም ስሜት ከመነጨ እንጂ የሰው ልጆችን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት መሆኑ ግልፅ ነበር። በልተሟላ ሁኔታ ውስጥ ለምን የሠው ልጅን ሕይወት አደጋ ውስጥ ይጥላል ተብሎ እንደምጠየቅ አልጠራጠርም። ነገር ግን በየትኛውም ሙያ ውስጥ ያለ ባለሙያ በተለይ ደግሞ ከፍተኛ የብዙ እቃዎች እጥረት ውስንነት ባለበት ሁኔታዎች ውስጥ የዚህ ዓይነት ችግር ፈቺ መፍትሔ ሀሳቦች እንደየ ሁኔታው እያመነጨ ካልሠራ አንድ እርምጃ ወደፊት መራመድ ከባድ ነው ባይ ነኝ።





ነ4/ምስል ሀ፤ የዚህን ቀዶ ጥገና መሳካት ከፍተኛውን ሚና የጫወቱት ሁለቱ እንቋቁ የህፃናትን የልብንና የሳንባን ስራ ተክቶ የሚሰራውን ማሽን የሚዘውሩት እንስት ባለሙያዎች ናቸው፡- ከግራ ወደ ቀኝ ህያት እና ቤዛ።

# 15

# ቡናና ጊዮርጊስ በልብ ህክምና

ኩርምት ፊፍስፎስ ብሉኒ ለመቀመጥ ከማይመቸው ወንበር ላይ ተቀምጦ የደከመው ሰው ወጣት አየሁ። እንደማውቀው እርግጠኛ ነበርኩ። እሱም እንዳየኝ ብድግ ብሎ ወደ እኔ መጣ። ለወራት ያክል ከስትሬት በመራቁ መከለኛ አሲያም መድኃኒቱን አቋርጦት ኖሮ ጉዳቱ ቀደም ሲል ቁመት ቢኖረውም ቀና ብሎ ለመሄድ የሚያስችል አቅም የለውም። ልቡ ተጎድቷል እና በዚህ ቡሃላ እድሜው ገና መሮጥ ሲጀምር ተያዘ። ከከፍተኛ ድካም ነገር በጥጥ የሚደቃ ልቡ ከውድ አያረን እና አያዘረ ቀጭ በል አልያም ተቀ ይለዋል። በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኋላ የሚያፈስው አንደኛው የልብ ግድብ (Aorta Valve Regulation) ነበር ለዚህ ሁሉ የዳረገው።



ወደ ምርመራ ክፍሉ ውስጥ ገባንና ያለበትን ሁኔታ መርመርን መድኃኒቶቹን እንደገና እንዲጀምር አደረግን፤ ከዚያም "ምነው?" ስለው ክትትሉ ሰለቸኝ'። ለዓመታት መድኃኒት ዋጥኩ፤ ለውጥ ከማየት ይልቅ እየደከመኝ መጣ። በመጨረሻም ሁሉንም ነገር ትቼ ወደ ገዳም ገብቼ ፀበል ይሻለኛል ብዬ ለ3 ወር በዚያው ከርሜ መምጣቴ ነው" አለኝ።

በልብ ማዕከል ውስጥ ይህንን ቀዶ ጥገና ለማድረግ የአላቂ ዕቃዎች ችግር ነበረብንና በፍጥነት መስራት አይቻልም ነበር። በዚህ አጋጣሚ በሚበላ ልጅ ሁኔታ ስሜታዊ ሆኜ ነበር። ስለዚህም መፍትሔው የልብ ቀዶ ጥገና እንዲሆንና መድኃኒቶቹን ጊዜ ለመግዛትና ጉዳት ለመቀነስ መሆኑን አስረዳሁት። አቅም እንዳለው እና ከኪሱ ገንዘብ ከፍሎ ማሰራት እንደሚችል ጠየኩት። አይደለም በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ ከፍሎ ማሰራት ይቅርና ከታላቅ ወንድሙ ጋር ተከራይተው የሚኖሩበትን አንዲት ደሳሳ ቤት ከፍያ እንኳን ለማካከት ከፍተኛ ትጋድሎ እንደሚያደርጉ ነገረኝ።

"አሁን ላይ ሰላም የነሳኝ ወንድሜን ማገዝ ቀርቶ ሸክም የሆንኩበት ጉዳይ ነው" አለኝ። ጤናዬ መልካም በነበረ ጊዜ ሁላታችንም እንሰራ ነበረ። ከራሳችን አልፈን ገጠር ለሚገኙት ቤተሰቦቻችን እንተርፍ ነበር። አሁን ላይ ሁሉም ጫና ታላቅ ወንድሜ ላይ ነው። ገጠር የሚገኙት ቤተሰቦቻችንም "ከእኛ ብዙ ይጠብቃሉ" አለኝ።

ዕድል ደርሶት ይህን ቀዶ ጥገና እስኪሰራ (መቼ እንደሆነ ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው) በመጠባበቅ ላይ ለሚከሰተው ሞትም ይሁን ማገኛውም የጤና እክል ከመቀበል ውጪ ሌላ አቅም አልነበረውም።

ሞክሬ የማላውቀውን አንድ ነገር ለማድረግ ከራሴ ጋር ሞገትኩ። "ማን ለምን አልሞከረውም" እያልኩ ከራሴ ጋር ብዙ ከወጣሁ ካወረድኩ በኋላ ሊረዱት ይችላሉ ብዬ ወደ አሰብኳቸው ሰዎች ስለዚህ ልጅ ለማሳወቅ ወሰንኩ። እኔ ቀዶ ጥገናውን በነፃ በመስራት እነሱ ደግሞ በሆስፒታሉ የሚከፈለውን ብር እንዲሸፍኑለ ለመጠየቅ ነበር ከፈራ ከቸር ወደ አንደኛው ግለሰብ ይሄድኩት።

ከእኔ ጋር በመልከም የመግባባትና በመረዳት ብዙ የማውቃት አንዲት ልበ ብርሀን በለሀብት ዘገድ ቢሮ ሔጄ አንኳኳሁ፤ ስለዚህ ወጣትም ጊዜ ወስጄ አስረዳኋት። ቀጥሎ ወደ ራሴ የቤተሰብ አባላት ሄጄ ራት ቢጤ አዘጋጀሁ፤ የዚህን ወጣት ልጅ ታሪክ ነገርኳቸው። በውጤቱም በእነዚህ በሁለት ውይይቶች የዚህ ልጅ ቀዶ ጥገና በፍጥነት እንዲሰራ የሚያስችል ገንዘብ አገኘሁ።

የአጠቃላይ ቀዶ ጠጋኝ ሐኪም እስከሆን ድረስ በሀገሬ ምድር በነፃ ዕውቀትን አግኝቻለሁ። የልብ ቀዶ ጥገና ሕክምና በሕንድ ሀገር ለሦስት ዓመታት የትምህርት ዕድል (Scholarship) ላገኝ የቻልኩት ለደሀ ሕዝቦች በሚደረግ የዕርዳታ ክታ ነው። እናም በእነዚህ በደሀ



ሕዝቦች ስም ያገኘሁትን ዕውቀት፣ ጉልበቴ እና ጊዜዬ እስከፈቀደ ድረስ ማገልገል እንዳለብኝ ይሰማኛል። ይህን ሳደርግ ደግሞ ከፍተኛ የእርካታ ስሜት ይሰማኝ ነበር።ይሁን እንጂ ከዚህ በተሻለ መንገድ እንዲሆን የውስጥ ፍላጎቴ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ እኔ ያለኝ መሰርያ ውሱን ብቻ ሲሆን በዚህ ልጅ ህይወት ላይ እንደታየው ብዙ ቅን ሰዎች ካልታከሉበት ለብቻዬ እንደማልነድ አሙን ነውና።

አንደኛውን የግራ የልብ በር (aortic valve) መቀየር ይፈልግ የነበረው ይህ ወጣት ያለምንም እንከን ቀዶ ጥገናውን አከናወነ። በቀዶ ጥገናው የልብ ምት መቋረጥ ወይም የደም መፍሰስ ሳይከሰት ሰለማዊ የግራ አንድ የልብ በር ቅየራ በብረት ሽልሽ (aortiv valve replacement with mechanical valve) ተካሄደ። በፍጥነትም ማገገም ጀመረ።ድካማችንና ውጥረታችን ፍሬያማ ሆነ። ከሙያዊ ጥረት ባሻገር ሰዋዊ ምኞትና ፍላጎታችን ሰመረ።

ከእጆቼ፤ ከአንገቴና ከአልበሳቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ አርማ የማይለየው ይህ ለጋ ወጣት በስተመጨረሻ ለዘመናት የሚጓጓለትን ቀዶ ጥገና ሊያገኝ ወደ ሆስፒታል በጠራነው ጊዜ ምኞቱን ገልፆልን ነበር። ከቀዶ ጥገናው በኋላ ጤናው ተመልሶለት የናፈቀውን የቅዱስ ጊዮርጊስ ማሊያ ለብሶ፤ የጊዮርጊስን ጨዋታ በአዲስ አበባ ስታዲየም መታደም መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ያጫውተኝ ነበር።

CamScanner

ምንም እንኳን እኔ ተወልጄ ባደኩበት መሳለሚያ ተብሎ በሚጠራው ሰፈሬ የቡና ገበያ እግር ኳስ ክለብ ተጫዋቾች እና ደጋፊ በእጅጉ የሚበዙበት ቢሆንም፤ በእኔ ልብ ስር የቡና ገበያ ደጋፍ የተሰቀረው ነገሩን ይማረውና በታላቅ ወንድሜ የተለየ የቡና ገበያ ስፖርት ክለብ ፍቅር ነበር።ከልጅነቴ እንስቼ በታላቅ ወንድማችን አጋፋሪነት በስታዲየም ተገኝተን የቡና ገበያን ጨዋታን እየከመከምን ነበር ያደግነው። ከስታድየም መልስም የታላቅ ወንድማችን የሰፈሩን ሰው ሠብስቦ ስለጨዋታው Commentator (ሲዘግብ) መስማት በጣም ያዝናናኝ ነበር።

በትምህርት እና በስራ ለብዙ ዓመታት በገጠረቱ ኢትዮጵያ ቆይቼ የልብ ቀዶ ጥገና ለመማር አዲስ አበባ ከመጣሁበት ጊዜ እንስቶ ላለፉት 8 ዓመታት የፀጉር አስተካካይ ደንበኛዬ አንድ ግለሰብ ነው። እናም ላለፉት ስምንት ዓመታት በልዩ ፍቅር እና መስተንግዶ አብረን ቆይተናል። ይህ ፀጉር አስተካካይ ታዲያ ቅልጥ ያለ የቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊ ነበር። ዛሬ ፀጉሬን ከስተካከለኝ በኋላ የወትሮውን የቡናና ጊዮርጊስ ቀልድና ብሽሽቆችንን ከጨረስን በኋላ አንድ ሰው ላስተዋውቅህ ብዬ ወደምሰራበት ሆስፒታል ወሰድኩት። በሆስፒታሉም በጥሩ ሁኔታ ያገገመውን ቅልጥ ያለው የቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊው ታካሚዬን አስተዋወቅኳቸው። ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍን።

*****





15/ምስል ሀ፤የምወደው ክለቤ ቡና ገበያ በ2003 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ዋንጫ ሲበላ በደስታ ፕሮግራም ላይ የተነሳነው ፎቶ።

# 16

## ሞቴን የደገስኩለት

በዓይኖቼ ሠርግ ላይ ለመገኘት በጎንደር ከተማ ተገኝቻለሁ። ከተሰናበትኳት 7 ዓመት ከሞላኝ በኋላ ጎንደርን ለማየት ጓጉቼ ነበርና የ"ማዚ ሁነኝ" ጥያቄውን በቀላሉ ነበር የተቀበልኩት። አየር ማረፊያው ድረስ መጥቶ የተቀበለን ግለሰብ በያዛት ቶንጆ የፒክ አፕ መኪና ላይ ሆነን ጉዞ ወደ ጥንታዊቷ ጎንደር መሀል ከተማ አደረግን። ማራኪ ከምታበና የተማርኩባትን የጎንደር ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ እያለፍን ወደ መሃል ፒያሳ ስንዘልቅ ያሳለፍኩት የ6 ዓመት የህክምና ትምህርት ቤት ኑሮዬ በትዝታ ወደ ኋላ ጭልጦ ብሎ ይዞኝ ሄዶ ነበር። በጨዋታም ምንም ሳይሰተፍ ወደ አረፍንበት ሆቴል ደረስን።

ምሽትላይማዚእናአጃቢዎቹበአንድሆነንካረፍንበትሆቴልተገናኘን።



በጋራ ተሰባስበን ራት እየበላን አንድ ሁለት መበል ተጀመረ። ጨዋታው ደራ፤ በአዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለሰውን አንድ ጉዳይ ላንሳ ወይስ ላንሳው እያልኩ ከራሴ ጋር እደራደራለሁ። ምናልባትም ይሔ በጉዞ የተለውን አዕምሮ ዛሬ በሌላ ቁምነገር መጥመድ ተገቢ ላይሆን ይችላል ብዬ ከራሴ ጋር ወሰንኩ፤ ይሁን እንጂ ነገ ደግሞ የሠርጉ እለት ነው። ስለዚህ በዚያ ሁሉ ግርግር በሰርጉ እለት ሀሳቤን ማጋራት አልፈለኩም፣ ከሠርጉ በኋላ ባለው ቀን ደግሞ ማምሻው ላይ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ይሆናል።

በዚህ መሀል መቁነጥነጤን ያየው ሙሽራው ገብቶት ነበርና ነጠል ብለን ወጣን። ትንሽ ከተመካከርን በኋላ ጊዜ እንስጠው በሚለው ሀሳብ ተስማማን።

ጉዳዩ እንዲህ ነበር። ከሣምንት በፊት አንድ መልዕክት በቴሌግራም ይደርሰኛል። መልዕክቱ የመጣው አርባ ምንጭ ሆስፒታል ውስጥ ከምትሰራ አንዲት ዶክተር ነበር። መልዕክቱ አንድ በሆስፒታላችን ውስጥ የሚኖር አሳዳጊ የሌለውና በሆስፒታሉ ሠራተኞች ቀና ትብብር የሚኖር የ16 ዓመት ልጅ እንዳለና ልቡ በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቶ በሞትና ሕይወት መሀል መሆኑን ይገልፃል። በተደጋጋሚ ልቡ እየደከመ (Heart Failure) ሆስፒታል እንደሚተኛና አሁን ግን በቋፍ ላይ መሆኑን ገለፀችልኝ። እንግዲህ ይህ ልጅ ከቶንሲል ጋር ተያይዞ በሚመጣ የልብ በር በሽታ (Rheumatic Heart Disease) ሁለቱ የልብ በሮች ክፉኛ ተጎድተዋል።

በመጀመሪያ ለመወሰን ልጁ አዲስ አበባ መጥቶ ማየት እንዳለብኝ ነግሬያት ታካሚው በአርባ ምንጭ ሆስፒታል በአምቡላንስ የምሰራበት ሆስፒታል ድረስ መጣ። የልጅነት ወዙን ያጣ መናገር እስኪቸግረው ድረስ እጅግ የተጎዳ ነበር። ነገር ግን በዓይኖቹ ስር የድረሱልኝ እና ነገን በተስፋ የሚጠብቅ አይነት አሳዛኝ ልጅ አየሁ። በፍጥነት የልብ አልትራሳውንድ ሠርተን የተበላውን አረጋገጥን። ነገር ግን አብሮኝ ከሚሰራ የሙያ አጋሬ በሁለተኛው በር (Valve) ላይ ባለው ጉዳትና ስለአስፈላጊው መፍትሔ በጥልቀት ተወያይተን ሁለቱንም በሮች መቀየር እንደሚሻል ተስማማን።

ልብ ማዕከል መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ ይገላገላል (First come first served) የሚል መርህ ይዞ የሚሰራ ሲሆን ይህ ታዳጊ ለመጀመሪያ ጊዜ በልብ ማዕከሉ ተመዝጋቢ በመሆኑ ረጅም ወረፋ መጠበቅ ግዴታው ይሆን ነበር። ጊዜ ከዚህ ህይወት በተቃራኒ አቅጣጫ ቆመች። እንደሚታወቀው የልብ ማዕከል በኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ፣ ይህንን ታካሚ የሚያስንቁ፣ ብዙ ሰዎች የቀዶ ጥገና ወረፋ የሚጠብቁበት ቤት መሆኑም ይታወቃል።

ሲቀጥል ለዚህ ታማሚ የምናደርገውን ዓይነት ቀዶ ጥገና ሁሉም ከዓመት እስከ ዓመት የሚሰራ አለመሆኑ ዋናው ምክንያት ነበር። ይህ ቀዶ ጥገናም እጅግ ብዙ አላቂ እቃዎች ከሚወስዱ ቀዶ ጥገናዎች አንዱ ሲሆን በተገኝነትም የሽልብና እና የኦክስጅኔተር ችግር ነበር።



እነዚህ ተደምረው ይህንን ልጅ ቶሎ ለማከም ከተማ ውስጥ ወደ ምንሰራባቸው የግል የልብ ቀዶ ጥገና ሆስፒታሎች ወስዶ መስራት አንድ አማራጭ ነበር። ይሁን እንጂ አይደለም ለዚህ አሳዳጊ ለሌለው ታዳጊ ቀርቶ ጥሩ ደመወዝ ተከፋይ ዘንድ እንኳ የልብ ቀዶ ጥገና ክፍያው ከባድ መሆኑ ነው። ስለዚህም "መፍትሔው ምንድን ነው?" ስንል ከዚህች የአርባ ምንጭ ሐኪም ጋር መከርን። በወቅቱ የእኔ የነበረው "እኔም ሆንኩ ሌሎች የሙያ ባልደረቦቼ ያለምንም ክፍያ ብንሰራ" የዋጋ ቅነሳ ስለሚኖረው፤ ሆስፒታሎቹም የራሳቸውን አስተያየት አድርገው ከዚያ በኋላ የሚመጣን ሂሳብ ሕብረተሰቡን በማነቃቃት መሰብሰብ ይቻላል አልኩ። ይህች የቀና ልብ ባለቤት የሆነችው ሐኪም ይህንን ሀሳብ በአስገራሚ ሁኔታ ወደ መሬት አወረደችው።

እኔም ዛሬ በጓደኛዬ ሠርግ ላይ ሠላም የነሳኝን ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመን ስለዚህ ታካሚ በመናገር ሁሉም የድርሻውን እንዲያደርጉለት ሀሳብ ለማቅረብ ነበር። በነገራችን ላይ ሙሽራው ሀሳቡን በጣም ከመውደዱም በሻገር በሠርጉ ላይ እንዲህ ዓይነት ነገር ተደርጎ ቢያልፍ ለእርሱም ትልቅ ኩራት እንደሆነ አጫወተኝ።

በሰርጉ ማማሻት በነበረው ምሳ ፕሮግራም ላይ ያሳሰበኝን ጉዳይ በዝርዝር አጫወትኳቸው ሁሉም ከመውደዳቸውም በሻገር ሌሎች ሰዎችንም ወደዚህ እንቅስቃሴ ለማስገባት ቃል ገቡ።

ወደ አዲስ አበባ ከተመለስን በኋላ ለዚህችው የአርባ ምንጭ ሆስፒታል ዶክተር ሀሳቤን ካጋራኋት በኋላ በማህበራዊ ሚዲያ እንቅስቃሴውን መርታ አስጀመረችው። ሦስት ሳምንታት በሞላ ጊዜ ውስጥ ይህንን ታማሚ ለማከም የሚበቃ ገቢ ተሠበሰበ። በመጨረሻም ታማሚው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደረገ።

የዚህን ታካሚ ቀዶ ጥገና ከመጀመራችን በፊት ለሙያ ባልደረባዬ እንደ የቀዶ ጥገና በለሙያ በዚህ ልጅ ላይ የሚታየው ምልክት ከልብ በሮች (Valves) በሻገር ልቡን የሚያቅፈው ጃኬትም ከፋኛ በዚህ Rheumatic process በምንለው ችግር የተጠቃ ይመስለኛል አልኩት። እርሱም "እንዴት ጠረጠርክ?" ሲል ጠየቀኝ። አዎን እንደዚህ ዓይነት ቀዶ ጥገና በመቶዎች ሠርቻለሁ። ነገር ግን አመጣጣቸው እንደዚህ ልጅ በከፍተኛ ጉዳት ላይ ሆነው አይደለም። "ሲቀጥል ደግሞ በዚህ በ አስራ ስድስት ዓመቱ እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰውን ምናልባት ይህ ታክሶበት ሊሆን ይችላል" አልኩት። የሚገርመው ቀዶ ጥገናውን ጀምረን ደረት ስንከፍት የጠረጠርነው እውነት ሆነ። ስለዚህም ይህንን እንደ ሲሚንቶ የተጋገረውን ልቡን የቀፈውን ጃኬት ማላቀቅ የመጀመሪያ ሦስት ሰዓት የፈጀ ትልቅ የቀዶ ጥገና ስራ ሆነ።

ቀጥሎም ሁለቱን የታመሙት የልብ በሮቹን ለመቀየር ልብና ሳንባን ተክቶ የደም ዝውውርን ለማሽን በውሰት ሰጥተን ወደ ገደለው ገባን። እናም ቀዶ ጥገናውን በስኬት አጠናቀቅን በእንዲህ ዓይነቱ ቀዶ ጥገና



ለሰረው የደም መፍሰስንም በጥሩ ሁኔታ ተቆጣጠርነው። ይሁን እንጂ ቀዶ ጥገና እጅግ ረጅም ስለነበረና ልቡም ቆሞ ብዙ ሠዓት በለቆየ የልቡ አሰራር ደካማ ሆነ።

ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚጠበቅ ጉዳይ በመሆኑ ብዙ አይነት የልብ መድኃኒቶችን መጀመር ግድ ሆነ። በብዙ መድኃኒቶች እየታገዝን ከ 11 ሰዓት የቀዶ ጥገና ክፍል ጊዜ በኋላ ወደ ፅኑ ታማሚ ክፍል ገባን። የልቡ አሰራር አስደሳች ባለመሆኑ የደም ግፊቱም በአብዛኛው ጊዜ ዝቅተኛ ነበር። በብዙ መድኃኒቶች እየተረዳ ማሽን እየተነፈሰለት ወደሚቀጥለው ቀን ተሸጋገረ። ይሁን እንጂ በሚቀጥለውም ቀን ሆነ ከቀዶ ጥገናው በኋላ በነበሩት ሰዓታት ምንም ዓይነት ሽንት መሽናት ሳይችል ቀረ። ይህም ኩላሊቱ እየወደቀ መምጣቱን የሚያሳይ ምልክት ነበር። በዚህም ምክንያት የሚከሰተውን ጉዳት ለመቀነስ ሲባል በሆድ ውስጥ በሚገባ የጊዜያዊ የደም እጥበት (Peritoneal Dialysis) ለመጀመሪያ ከኩላሊት ስፔሻሊስት ጋር ምክክር ተካሄደ። እናም በሚቀጥለው ቀን ይህንኑ ኩላሊትን የሚያግዝ የደም እጥበት ጀመርን።

በማምሻ 12:00 ሰዓት ገደማ ይህንን እጥበት በጀመርን ጊዜ ውስጥ በድንገት ልቡ ቀጥ አለች። የሕይወት አድን ስራዎች ለሰዓታት ተካሔዱ። ደረት ከፍተን ልብን ማሳጅ አደረግን። አልተመለሰም፤ ለወራት የደከምንበት የሕይወት አድን ጥረት እና ድካም በዚህ ተደመደመ።

እኔም ሀዘን ተሸልሜ በዕለተ እሁድ ከቤተሰብ ከጓደኛ ራሴን አርቄ በልኬን አጥፍቼ ከራሴጋ ዋልኩ።

ገና ለማሰባሰብ እርዳታ ለማግኘት ያመቻቸነው ማህበራዊ ሚዲያ እኔን ለማጥቃት እንደሚውል ማሰብ ቀላል ነበር። በዚህ ሀገር የልብ ቀዶ ጥገና ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ሰዎችን እንዳስከፋሁት ሁሉ እንደዚሁ ያሉ ልብ ሰባሪ፣ ቅስም ሰባሪ አጋጣሚዎችም ነበሩኝ። ተሠባሪነቴ ግልፅ ነው። አጋዥ የምለው ሰው የለኝም። የተማርኩት በከፍተኛ ድህነት ነው። ለደረስኩበት ስኬት ከአንድ ከፈጣሪ ውጪ የታከለበት ውጫዊ አካል የለም። እኔም ለጥቃት ተጋለጥኩ። አንገቴን ደፋሁ፤ ለመሰዋት ዝግጁ ሆንኩ።

ወደሚቀጥለው ስራ መሸጋገር ተሣነኝ። እስከ ፍፃሜው ልረዳውና ላድነው የታገልኩለት ታዳጊ ወጣት ሞተ። ዛሬ ደግሞ ቀብሩ ተፈፀመ ተብሎ በማህበራዊ ሚዲያ አየሁ። የዚህ ልጅ ፎቶ ለቀናት በአዕምሮዬ እየተመላለሰ እንቅልፍ ነሣኝ። "የፈጣሪ ፈቃድ ይሁን" ብዬ ለማንም መልስ ሳልሰጥ ዝም አልኩኝ። "ለመሆኑ ከዚህ መማር የነበረብኝ ምን ነበር?" ብዬ እናንተን ጠየቅኳችሁ።



# 17

# ሳማ ሰንበት

በየዓመቱ ወደ ሣማ ሰንበት የሚያደርጉት ጉዞ ለ አስራ ሰባት ዓመት አስቆጥረዋል። ሰንጋ ተራ አካባቢ የሚገኙ የአንድ ዕድሜ አካባቢ ልጆች በሁዳዴ የፆም ወቅት አጋማሽ ላይ የሚከበረውን ይህን በዓል ሳያቋርጡ ይጓዛሉ ። በቤተክርስቲያን የሀይማኖታዊ ስርዓት ፈፅመው ሲያበቁ በዚያው ከሚገኙ የአካባቢው ቤቶች ወደ አንዱ ጎራ ማለት የተለመደ ነው። አዲስ አበባ የሰለቻቸውን ድራፍትም ሆነ ቢራ በዚህ ቦታ መጠቀም አይፈልጉም።

ከሁሉም የገጠሩ፣ የጥንቱን የእናቶቻችንን ጠላ እና አረቄ የሁሉም ምርጫ ነው።

በተደጋጋሚ የሚያርፉበት አንድ ቤት ሲውል ሲያድር በጣም መለመድ ይመጣና ቤተሰብ ይሆናሉ። እና በየዓመቱ በፆም ግማሽ እኚህ ከአዲስ አበባ ሰንጋ ተራ አካባቢ የሚመጡ ወጣቶች በዚሁ ቤት ያርፋሉ። በዚህ ቤት በዚህ ቀን የተጋገረው ዳቦም ሆነ እህል እነኚህ እንግዶች ሳይመጡ አይቀመስም ነበር። እንግዶቹ በመጡ ሰዓት ዳቦው ይቆረሳል፤ ቤተሰብ እህል ይቀምሳል፤ በአጠቃላይ ደስታ ይሆናል። በእንዲህ ሁኔታ ለ13 ዐመታት ተቆየ።

ከአራት አመት በፊት በአንዱ በዚሁ ቀን እንግዶቹ እዚህ ቤት ሲደርሱ የወትሮው ደስታ አልነበረም። ምንም እንኳ የወትሮው ዝግጅት ሁሉም ቢኖርም ከፍትፍቱ ፊቱ ነውና እናት በሀዘንና እና ጭንቀት ላይ ነበሩ። ወደ ገጠር አያቱ ጋር ኗሮ ሲያድግ የነበረው ልጇ በጠና ቢታመም አያት እንዳይቸገሩበት ወደ እናቱ አምጥተውታል። ይህ ገና የ12 ዓመት ታዳጊ በጠና ታሞ ከእናቱ ቤት ተኝቷል። ቤቱም የወትሮው ደስታ ርቆት ሀዘን ሸብቦታል። እንግዶቹ በደት ነገር ልባቸው ተነካ። እናትም አዲስ አበባ አምጥታ ማሳከም የሚያስችል የገንዘብ አቅም አልነበራትም።

እነኚህ ወጣቶች አዲስ አበባ መጥተው ያዩትን ጉዳይ መርሳት አልቻሉም ነበር። ተወያይተው ጥቂት ገንዘብ አዋጥተው አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መጥቶ እንዲታከም አደረጉ። ወጪውንም መሸፈን ቻሉ።



በእንዲህ ሁኔታ የዚህ ሕፃን ችግር ከቶንሲል ጋር ተያይዞ የሚመጣ የልብ በር (Valve) ችግር መሆኑ ታወቀ። በአብዛኛው የልጅነት ጊዜው ከአያቱ ዘንድ የነበረው ይህ ታዳጊ በተደጋጋሚ በቶንሲል ይጠቃ እንደነበር ይገልፃል። ለዚህም አያቱ በባህል መድኃኒት የተቀመመ ሻይ ይሰጡት እንደነበረና በዚያም እንደሚፈወስ ይናገራል።

በእነዚህ ወጣቶች ቸርነት እናት ለአራት ዓመታት አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ እያመላለሰች ለልጇ ክትትል ሊደረግላት ችሏል። ይሁን እንጂ "መፍትሔው የልብ ቀዶ ጥገና መሆኑና አንድ ቀን ከውጭ በሚመጡ ሐኪሞች እድሉ ካገኘ ይሰራለታል። ይህም እድል ሲመጣ እንጠራችኋለን" የሚል ተስፋ ለክትትል በመጡ ቁጥር ይሰጣቸው ነበር። ይህ ታዳጊ መድኃኒቶቹን ቢወስድም እንቅስቃሴው ሊሻሻል አልቻለም። ትምህርቱንም ከ4ኛ ክፍል ለማቋረጥ ተገደደ። እህል በጉሮሮው አይወርድም፤ ድምፁ የሚያስፈራ ጎርናና ሆነ፤ ሰውነቱም ክብደቱ ቀነሰ።

የዘንድሮው የሁዳዴ ፆም እኩሌታ ተጓዦች በዚሁ ቤት ሲገኙ የወትሮው ድግስ አልጠበቃቸውም። ይልቁንስ እና ባዶ ቤት ነበር። [illegible] ደግሞ እናት በጠና የታመመውን ልጅ ይዘው በአካባቢው [illegible] ሆስፒታል በመግባታቸው ነበር። እነኚህ ተጓዦች ቤት እንቀደር [illegible] ልጁ ወደተኛበት ሆስፒታል ተጉዘው ዛሬ 16 ዓመት የሞላውን [illegible] በፅኑም እጅግ አዝነው ተመለሱ፤ እዚህ ሀገር ካልተቻለ ወደ [illegible] ሌላኛው አማራጭ እንደነበረም ተነግሯቸዋል።

ይሁን እንጂ ይህ ለእነርሱ እጅግ ከባድ ወጪ ነበርና ምን ማድረግ እንደሚችሉ ባያውቁም የሕክምና ሪከርድ ወረቀቱን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

*****

በሚያዝያ 2013 ዓ.ም ለወራት የ Healing Valves Ethiopia (HVE) project ለወራት በሀገራችን የጤና ጥበቃ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ሲገመገም ቆይቶ እጅግ በጣም ከፍኛ በሆነ ሁኔታ ተቀባይነት ያገኘበት ቀን ነበር። እኔም በቦታው የአብሮ መስራት ስምምነት (Memorandum of Understanding –MOU) ለመፈራረም በቦታው ተገኝቻለሁ። ይህ ድርጅት በእቅዱ መሠረት በዓመት የ50 በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዱ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ታካሚዎችን በነፃ የሕይወት አድን የልብ ቀዶ ጥገና ለመስራት የተነሳ ድርጅት ነበር።

አንድ የጤና ጥበቃ ሠራተኛ ወደ እኔ ጠጋ ብሎ "እስኪ ዶክተር እባክህን ይህቺን የሕክምና ወረቀት እያት" አለኝ። የ16 ዓመቱ ታዳጊ አንድ የልቡ በር በከፍተኛ ሁኔታ የሚያፈስ እና ከፉኛ የታመመ መሆኑን ያወሳል። ካማማሰገበት አካበቢ ነው የመጣው። እኔም ባየሁት ነገር ተገርሜ "እነዚህን ልጆች ለማዳን ነው ዛሬ ይኸንን የተፈራረምነው" አልኩት።



በእነዚህ ቀና ወጣቶች የገንዘብ ድጋፍ ታክሎበት ድርጅታችን ወደ ስራ በገባ በሁለት ሣምንት ውስጥ የሚያስፈልገውን ገንዘብ አገኘን። ሙሉ የሀገራችን ልጆች በፈቃደኝነት በነፃ በጎ ፈቃደኛ በመሆን የዚህን ታዳጊ ቀዶ ጥገና በተሳካ ሁኔታ አከናወንን። በፍጥነት አገግሞም ወደ ሀገር ቤት መመለስ ቻለ።" ሹፌር ሆኜ እናቴን መርዳት እፈልጋለሁ" ሲል የነበረው ይህ ታዳጊ ዛሬ ከቀዶ ጥገና በኋላ ግን በትምህርቱ ገፍቶ ሐኪም ሆኖ ወገኑን ማገልገል እንደሚሻ ይናገራል።

እነሆ በእነዚህ እና በመሰል መሠረታዊ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈው ፍላጎት ወደ ድርጅት መልክ አደገ። እነሆ አዲስ ምእራፍ ተከፈተ። በመጨረሻም የ Healing Valve Ethiopian (HVE) የተባለውን አገር በቀል የማብረሰናይ ድርጅትን ወለደ። ይህ አገር በቀል ድርጅት በሀገር በቀል እውቀት የተመሰረተና በሀገር በቀል እውቀት ስራውን የሚከውን ይሆናል። የመጀመሪያ አመት እቅዱም የ50 ህጻናትን ህይወት መታደግ ነው። በዚህም መሰረት በከፍተኛ ድህነትና ከኪሳቸው ገንዘብ ከፍለው መታከም የማይችሉ! ሲቀጥልም የልብ ድካም ውስጥ ያሉ የልብ በራቸው በቁንጊል ምክንያት የታመሙ ህጻናት የህይወት አድን ቀዶ ጥገና ያለምንም ክፍያ ለመስራት ተነስተናል። መልካም ጉዞ



17/ምስል 11፡ የHVE የቀዶ ጥገና የበጎ አድራጎት ቡድን ከላይ ታሪኩ የቀረበውን [illegible] አካባቢ የመጣውን የ16 አመት ታዳጊን የልብ በር በመቀየር ላይ።





17/ምስል አ፤ HVE የተባለው አገር በቀል ድርጅት የመጀመሪያውን የነፃ የልብ ቀዶ ጥገና በካሄደ ወቅት በበጎ ፈቃደኝነት የተሳተፈው ሙሉ የቀዶ ጥገና ቡድን ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለማስታወሻ የተነሳነው ፎቶ።

Healing Valves ETHIOPIA

[illegible] በምስሉ የሚታየው አርማ በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ቁጥር 5821 መሰረት ህጋዊ ሰውነት ያገኘው ድርጅታችን ሂሊንግ ቫልቭስ ኢትዮጵያ ሲሆን በሀገር በቀል በጎ ፈቃደኛ በለሙያ ልጆች በአመት የ50 ድሀ የልብ በር ታማሚ ህፃናትን የልብ ቀዶ ጥገና ለመስራት የተነሳ ድርጅት ነው።



# መውጫ

ከዚህ በታች ያለው የታሪኩ ባለቤቶች የራሳቸውን ታሪክ አንብበው ሲያገኙ የተሰማቸውን የጻፉት ነው። ለማስረጃነት ዋናው ኮፒ የተያያዘ ሲሆን ለማንበብ እንዳያስቸግር በማሰብ ደግሞ በቅድሚያ በታይፕ የተከተበው ቀርቧል።



አባቴ አንተ ዶክተር ብቻ አይደለህም።
አባትም ጭምር ነህ። አመሰግንሀለሁ። እወድሀለሁ።
ዶክተር ህመሙ ብቻ አልነበረም። ህመሜ እንዴት
እታከማለሁ የሚለው ጭምር እንጂ።
ስለአንተ ብዙ ሰዓት በወሬ ብናገር አይደክመኝም።
አመሰግንሀለሁ አባቴ።

ከባለታሪኮቹ አንዱ።



ሁሌም እንደምሆኑ መጠን በርጀሪው ሳይሰራ ቢቆይ ልጄ ምን ያህል አመት ልትቆይ እንደምትችል እና የነገሮች ጉዳቶቹ እያየኋት እሰበሰሁ እጨነቃለሁ።

በእርስዎ ምክንያት ከብዙ ነገር ተስተጓጉያለሁ። የእርስዎን ጉዳይ ከዳር ሳላደርስ በማለ።

ለባማራት ባልችልም ሁሌ ሳያት ተደብቄ አለቅሳለሁ። አበቷም እንደዛው። እንደውም TV የcardiac center "ልቤን ዳንኩ" የሚለው ማስታወቂያ ራሱ መታየት አይችልም ነበር እኛ ቤት።

ዶ/ር ፈቀደ እኔ እስከዛሬ ሲለኝ ማመን ነበር የከበደኝ። ከእግዚአብሄር ቀጥሎ ልጄን አምኜ ሰጠሁት። እርሱም አላሳፈረኝም፤ መለሰልኝ።

ብዙ ውስጥ ውረድ ባልፍም ልብ እንደዳደሮ እየተመካከርን የነበሩ ነገሮችን ተወጥተናል።

በስዉሩ ከበርጀሪው /ቀዶ ጥገናው/ በኋላ ሲያያት የማይደበት የሚደመርጥው ዓይኖና ሀመድ የለም።
ሁሉም በቤታችን ልዩ ቦታ አለው!!!

የቆመው ነርሶ እንዲቀጥል ምክንያት ሆነሃልና እድሜ ቀጥሉልህ(ልሽምርልህ) ብዙ ህይወቶችን እንድትታደግ ያድርግህ እላለሁ።

ከባለታሪኮቹ አንዱ።





ህክምናው በሀገር ውስጥ አለመኖርና በቀዶ ህክምና ብቻ መዳን እንደምችል በሰማሁበት ወቅት የተሰማኝን ስሜት መቼም ማሰብ አልፈልግም። ነገር ግን በቃ ተስፋ ስለቆረጥኩ ከመሞቴ በፊት ማድረግ ያለብኝን ነገር ማድረግ ጀመርኩ።

ዶ/ር ፈቀደ ስለ ቀዶ ህክምናው አረዳዱን በሚሰጠኝ ወቅት ማመን አልፈለኩም፤ አልተቀበልኩትም። "መሞቴ ስለማይቀር ታዲያ ለምን፤ ገዝም ብዬስ ልሞት አይደል?" አልኩና ለቀዶ ህክምናው ተስማማሁ። ምናልባትም ከተረፍኩ ብዬም ብዙ የቃል ጥያቄዎችን ጠየኩት። እሱ ግን ባትሆኝና ካስረዳኝ በኋላ የጥያቄዎችን መልስ በተግባር አሳየኝ፤ አመንኩት።

በሚገርም ሁኔታ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለመላው ቤተሰቦቼ ጭንቀትን የሚያቀልና ተስፋን የፈነጠቀ ታሪክ። በእግዚአብሔር ፈቃድ የመኖር እድል ተሰጠኝ። ዛሬ ላይ ሆኜ የድሮውን ማሰብ እስከማልችልበት ድረስ ሙሉ በሙሉ ዳንኩኝ።

ፈቀደ

ተስፋ፤ የውስጥ ሰላም እና ደስታ የሚሰጥ ቢሆን በቀጥር አስቀምጠው ነበር። ግን ለእኔ ብቻ በሚገባኝ መልኩ የውስጥ ስጦታ ያበረከተልኝ የጤናዬ ጋሻ ነው።

ፈቀደ

ቃሉ የማይገለፀውን ያህል ስሜት፤ ሰው የማይረዳልኝን በቃይ በተሰጠው እውቀት በተባረኩ የእጆቹ ጥበብ የተበቀለልኝ የልብ ጀግና ነው።

የእነዚህ የተባረኩ እጆችህ ፍሬ ነኝ።





[illegible]

[illegible]

ከባለታሪኮቹ አንዱ።





በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዱ የእኔ ታሪክ ነው።
አንዳንድ ጊዜ ተስፋ በቆረጥንበት እና በቃ
በልንበት ሰአት ፈጣሪ ብዙ ደጋጎችን ወደ
ህይወታችን ይልክልናል። አዲስ ቀንን
በእነሱ ምክንያት ይሰጠናል። ለእኔም
የሆነው ይሄ ነው።

የተሻለ ነገ፤የተሻለ ህይወት ተሰጠኝ።
ምንም ምስጋና የማይገልፀው።
አመሰግናለሁ።

ከባለታሪኮቹ አንዱ።



ድንቅ እጅግ በጣም ድንቅ የሀኪምና እውቀት
እጅግ በጣም ድንቅ ሰው የምውደድ ጥበብ
እጅግ በጣም ድንቅ ትህትና
እጅግ በጣም ድንቅ የሰው አክብሮት
እጅግ በጣም ድንቅ የአጻጻፍ ስልት ወዘተ
ከአምላክ የተቸረው ድንቅ ሰው ዶ/ር ፈቀደ።
ይህም የእጆቹ ስራ የሆነው የእውቀት ጠፈጠፍ
መጽሐፍ ይታተም ዘንድ እምላክ ፈቀደ።

ከባለታሪኮቹ አንዱ።





እኔ የምሰጣቸውን ትኩረት ወንድም ብቻ ስላልሆነ የቤተሰቦችንም የመጀመሪያ ልጅ ነኝ። ወንድሜ ገና በትንሽነቱ የልብ ህመም አጋጥሞውና ይሰቃይ ጀመር። ይህንና ገና በ5 አመቱ ከቆየ አንድ ብሎ በጀመረው ሰአት አንደኛደረጃ መጨረሱና ያንንውን መመገብ ሲያቅተው እንኳን ለወንድም ለባለሙ ይሞላ። ይሀን ጊዜ ወንድሜን መታደግ እንዳለብኝ ተረዳሁ። የምታደገው ደግሞ ጥናቴ ህክምና ብዳለበት በመውሰድና ህመሙ እንዳይብሰበት ክትትል በማድረግ ነው።

ታዲያ ይሄ ውሳኔ የእኔ በሰባተር ወደ አዲስ አበባ መጣቶ የተሻለ ህክምና እንዲያገኝ ወሰንኩና ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና የልብ ማዕከል መጥቶ ክትትል እንዲጀምር አደረኩኝ። ክትትሉን ቢጀምርም በሽታው ግን አልተሻለውም። መረጋጋም አልቻለም። እንደዚህ እያለ ለ5 አመት ሙሉ ከትትሉን ሳያቋርጥ ዘለቀ።

ታዲያ አንድ ቀን ወደ ልብ ማዕከሉ እንደተለመደው ከትትል ለማድረግ ከመጣ ልብ ግቢ ውስጥ እንደገባሁ ስሙን የማላውቀው ዶ/ር መሆኑን ብቻ የማውቀው ሰው አገኘሁ። "ዶክተር!" ስለው እየሳቀ ወደእኔ መጣ። እኔም ነገሩንት ፊቱ እንደሚያሳው ሳቁን ሳየው ደስ አለኝ። እኔም የታመመ ወንድም እንዳለኝና ደሰራ እንደሆነ ጠይቱኝ። እሱም ህፃኑን አየና በጣም የተጎዳ ስለሆነ አለ። በቃ እስራዋለሁ ብሎኝ ተሰናብቶኝ ወደ ቤት ላከኝ። እኛም ወደ ቤታችን ተመለስን። ከዚያ ቀን ጀምሮ አስከሚጠራው ድረስ እንደ ሀኪም ብቻ ሳይሆን እንደ ቤተሰብ ይንከባከበው ጀመር።

ከወራት ቆይታ በኋላ ስልክ ተደውሎ ለሰራ ነው ሊበል ፍርሀትም ደስታም ፈጠረብኝ። ምክንያቱ ደግሞ ወንድሜን በጣም ስለምወደው ሁሉንም ነገር በቅርበት የምከታተለው እኔ ነኝ። ታዲያ የመጀመሪያውን ቀዶ ጥገና ለማድረግ 2 ማክሰኞ ቢደረግ ቀኑ ዉሎ ሆኑብኝ። ብቻዬን



መጨነቅ ጀመርኩኝ። የምሆነው ሁሉ ጠፋብኝ። ለእናቴ እንኳን እንደሚሰራ እንጂ መቼ እንደሆነ አልነገርኳትም። ብቻዬን በጨንቅ ለ 10:00 ሰአት ሲሆን ዶክተር ፈቄን አገኘሁትና "ቀዶ ጥገና በሰላም ተጠናቋል። ሲነቃም ተጠርተህ ትገባለህ ታየዋለህ" ብሎኝ ሄደ። ታድያ ይሄን ጊዜ ውስጡ በድንጋጤ ተሞልቶ ነበር። ምክንያቱም ደግሞ ከዚህ በፊት ሰው አገሬኝን ተደርጎ ለመንቃት ስንት ሰአት እንደሚፈጅበት አላውቅም ነበር።

ከትንሽ ሰአታት በኋላ ነቅቷል ተብሎ ተነገረኝና ወደ ማገገሚያ ICU ገባሁ። ገና እንዳየሁት እምባ ተናነቀኝ። መናገርም አቃተኝ። ምክንያቱም ደግሞ ወንድሜን በጣም ስለምወደውና ብዙውን ጊዜ አብሬው ስለማሳልፍ ነው። ገና ICU እያለ ወንድሜ "እመሰግናለሁ" አለኝ። ለምን ስለው" የሚሰማኝ ስሜት የለም ድካምም የለም" በቃ ዳንኩኝ አለኝ። እኔም በደስታ ለእናቴም ለአባቴም ለጓደኞቼም ነገርኳቸው። እነሱም ተደሰቱ። ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሄር በታች የማመሰግነው ዶ/ር ፈቄ መጣና" እንኳን ደስ አለህ" በደንብ ሲሻለው ወደ ward ይወርዳል አለኝ። ከዚያም እንዳልሰማሁ ኮሪደሩ ነው ስለው እየሳቀ "ቻው" ብሎኝ ሄደ።

ከትንሽ ቀን ቆይታ በኋላ ወደ ward ወረደ። ሲጨወት ሲንቀሳቀስ በጣም ተደሰትኩ። እግዚአብሄርር ልቱን ቆጠረልኝ ብዬ ፈጠረኝን አመሰገንኩ። ከትንሽ ሳምንታት በኋላ ወደቤት ተመልሰን ሁላችንም በሰላም ደስ አለው። ከትንሽ ቀኖችቶ ቆይታ በኋላ ለቁጠሮ ወደ ልብ ማዕከሉ ተመለስን። በንመለስ ዶክተሮቹ ያዩት ነገር ደስ እንዳላላቸው ፊታቸው ላይ ተረዳሁ። እነሱም ወዲያውኑ ደሙ ስለቀነሰ ደም መውሰድ አለበት ብለውን ነገሩኝ። እናም ደም መውሰድ ጀመረ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የመከራ ጊዜ ጀመረ። በጣም ተሰቃየ። የደሙን መስጫዎች ላይ ውስጡ መቆቀም አቃተው። እኔ ብቻ ሳልሆን በልብ ማእከሉ ውስጥ ያሉት ነርሶችና

ጆስተሮች ሁሉም ማዘን ጀመሩ፡፡ በሙያቸው የሚፈቅደውን ሁሉ አደረጉ፡፡

ከዚህ ሁኋላ ውጣ ውረድ በኋላ ብዙ መድሀኒቶችና ደም ከወሰደ በኋላ ምንም ለውጥ ባለማምጣቱ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የደም ክፍል ተላከ። ከዚያ በኋላ ያየው ውጣ ውረድ እሱ ፈጣሪ ይቁጠረው እንጂ ብዙ መከራዎችን አሳልፈናል። ብዙ ከለፋን በኋላ ውጤቱ ምንም የሚያገኘው ነገር ስለሌለ ወደልብ ማዕከሉ እንድንመለስ ነገሩን። ወደ ልብ ማዕከሉ ተመልሰን በውስጡ መሳሪያ "በድጋሚ መሰራት አለበት" ተባልን። በውስጤ ተደናገጥኩና እምባዬ መጣ፤ ከእሱ ፊት ላለማልቀስ እንደምንም ደንበሬን ተቆጣጥሬ እሱን ማበበል ጀመርኩ። እሱም በር ላይ ቆሞ የምንነጋገረውን ይሰማ ነበርና ከወጣን በኋላ መንገድ ላይ ማልቀስ ጀመረ። በጣም ተማረረ፤ ለቀዶውን ሲጨርስ ከአንድ ዘጠኝ ዓመት ልጅ የማይጠበቅ ብዙ ከባባድ ነገሮች በጣምቁ መልስ ሰጠኝ። ይሄኔ እኔም በጣም ሆድ ባሰኝና ተማርሬ አለቀስኩኝ።

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ተቆጣጣሪ መቀበን ነበረብን። ውሳኔው በጣም ከባድ ነበር። የሚከብደው ደግሞ በጣም የምወደው ወንድሜ በቀጣይ ወር ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ሊያደርግ ስለሆነ ነው። ውሳኔውን ይበልጥ የሚያከብደው እናቱና አባቱ እያሉ እኔ በመወሰኔ ነበር። ለመወሰን እናቱ ከዚያም ለአባቱ ነገርኳቸው። እናቱ በጣም ደነገጠች፤ አባቱም ደነገጠ። ሁሉም ነገር ከባድ ቢሆንም ግን ውሳኔው የግድ መወሰን ስለነበረበት ወሰንን። ከዚያ በኋላ ቅጠሩን ሞላልን ገባን። በጣም ተጨንቀን ወደ ልብ ማዕከሉ ሄድን። እንደተለመደው ዶ/ር ፈቀደን አገኘነው። እሱም እኛን ሲያይ እየሳቀ ወደ እኛ መጥቶ ያለውን ነገር ሁሉ አስረዳን። ከዛሬ ጀምሮ እዚያ እንድንቆይ አመቻቸልን። እኛም እሱ በሰጠን መመሪያ ተመልሰን ገባን። ከዚያ በኋላ



እንደተለመደው እንክብካቤ ተደመረለት። ከብዙ ቀናት ቆይታ በኋላ ለሁለተኛው ቀዶ ጥገና ቀናት እንደሚቀሩት ዶ/ር ፈቁ ነገሩኝና እቤቴን ተክቼ እንድወጣ አመቻቹልኝ።

ከወጣሁ በኋላ ስራ ጀመርኩ። ስራዬን ብጀምርም የእሱ ናፍቆትና ህመሙ ያስጨንቀኝ ጀመር። ቢሆንም ሁለተኛው ቀዶ ጥገና ጊዜው ደረሰ። ያን ጊዜ ከሌላው በተለየ እኔ ብዙ አላስፈራኝም። ምክንያቱ ደግሞ ሆስፒታል በቆየሁባቸው ጊዜያቶች በዶ/ር ፈቁ በጣም እተማመን ነበር። የምተማመንበት ምክንያት ደግሞ ሁሉም እሱ የሰራቸው ሰዎች ያለምንም ችግር በሰላም ሲወጡ አያለሁ። ግን ከነገሩ ውስብስብነት አንፃር ጭንቀት ፈጥሮብኛል።

ሰኔ 15 ከባድ ቀን ነበር። ህይወት የማስቀጥል ወይስ ያለማስቀጠል? ታዲያ የዚያን ቀን እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር አደረ። በጠዋት ተነስቼ ጸሎት አድርጌ ወደ ስራ ገባሁ። በጣም ጨነቀኝ። እስከ 6:00 ሰአት ሰርቼ ከሰአት ወደ ልብ ማእከሉ አመራሁ። እዚያ እንደደረስኩ እቤቴን በርቀት አየሁት። ፊቱ በእንባ እንደታጠበና በጣም ተጨንቆ ነበር። ነገር ግን በዚያን ሰአት የምንጨነቀው እኛ ብቻ አልነበርንም። ሁሉም የማዕከሉ ሰራተኞች፤ ነርሶች፤ የምግብ ባለሙያዎች፤ የጽዳት ሰራተኞች ሁሉም እንደኛ የተጨነቁ ነበሩ። ምክንያቱ ደግሞ የሲፍን ሁሉም የማእከሉ ሰው ስለሚወዱት ነው።

ልክ ከቀኑ 1:00 ሰአት ሲሆን በመስኮት አየሁት። እሱም ጠራኝና ወደ እሱ እንድመጣ ነገረኝ። ከዚያም ከአባቱ ጋር አገኘኝ። በውስጡ በድንጋጤ እንደዘለለ ያስታውቃል። ቢሆንም እሱ ግን ከመጀመሪያው ክፍል በሰላም ወጥቷል። አሁን ወደ ICU ገብቷል አለን እና በተረጋጋ ሁኔታ የመጀመሪያውን 24 ሰአት ከባድ እንደሆነና እስኪነቃ ድረስ ተረጋግተን እንድንጠብቅ ነገሩን። እኔም የምማርበት ሰፈር ሩቅ መሆኑን የተረዱት ነርሶች ሁሉም ነገር ሰላም እንደሆነና ትንሽ ሰአታት እንደሚቀሩት

ነካረው ወደቤት ሄድ አሉኝ፡፡ እኔም በዚያ ሰአት የሚያስገርኝ ወንድሜ ብቻ ሳይሆን እቤቱም ነበረ፡፡

ነገር ግን ምንም ማድረግ ስለማልችል ትቻቸው ወደቤት አመራሁ። ልክ የቤቴን በር ከፍቼ ስገባ አቦቱ ደውሎ ነቅቷል አሉኝ። ይህን ስሰማ ሰፈሩን በጩኸት ቀወጥኩት። ጠዋት እንደቢያ 12:00 ሰአት ተነስቼ ጸሎት አድርጌ አይኑን ለማየት ወደ ፅኑ ማከሚያ አቀናሁ። ወደ ውስጥ መግባት የሚችለው ከረና የተመረመረ ብቻ ነው። የእኔንና የወንድሜን ፍቅርና ያሳለፍነውን የመከራ ጊዜ ካላሚያውቁ ወደ ውስጥ ገብቼ እንዳየሁ የ ICU ዶክተሮችና ነርሶች ዕድሌን ቀይሬ መግባት እንዳለብኝ ነገሩኝ። ገብቼ ገና እንዳየሁት ተደሰትኩኝ። እሱም ቀና ብሎ አየኝና "ወንድሜ ቁርሴን አብላኝ" አለኝ። እኔም እየተደሰትኩኝ ቁርሱን አበላሁትና ወደስራ ተመለስኩኝ።

ከዚያ በኋላ ዶ/ር ፈቄ እና ባልደረቦቹ የደከሙበት ስራ ውጤታማ እንደሆነና እሱም እንደተሻለው፣ እሱም እንደሌሎቹ አልቀረም ሁሉም ነገር ሰላም ሆነ። ከዚያ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ዶ/ር ፈቄ የዮሴፍን ጤንነት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ስለሚከታተለው እና ከእግዚአብሔር በታች ሆኖ ወንድሜን ስላዳነልኝ ለእሱ እና ለመላው ቤተሰቦቹ፣ ለስራ ባልደረቦቹ ረጅም እድሜና ጤና ይስጥልኝ።

ዶክተር ከምናወራው ወይም ከምንሰማው በላይ ነህ። እኔ ላደረከው ነገር ሁሉም ወይም በዘይወግም አላረሳውም። አመሰግናለሁ። ለእኔም ቢቻ ሳይሆን ለመላው ሀገራችን ወይም ለኢትዮጵያ ከፈጣሪ የተላከ ነህና እንከራብሀለን።

ከበኢታሪዎቹ አንዱ
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ
The right hand man of God





በእኔ ላይ እንዲሆን እና ህይወቴ እንደገና እንዲቀጥል ላረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው

ምስጋና፦

በእግዚአብሔር በታች የአንበሰውን ድርሻ የሚወስደው እውቀትን ከብቃት ጋር ያያዘው፣ ትህትናን ከፍቅር ጋር ለተቸረው ለዶክተር ፈቀደ ይሁንልኝ!!! እንዲሁም በተመላላሽነት ስታከም ይከታተለኝ ለነበረውና በደም ስር ለሚሰጠው ህክምና በከንትራስት አለርጂ ምክንያት ላይሳካለት ለቀረው፣ በኋላም ለቀዶ ህክምና ላዘጋጀኝና ላበረታታኝ ቅን ሰው ዶክተር ከፍያለው ይሁንልኝ።

በመጨረሻ ለዶክተር ፈቀደ ሰላም እና ለመላው ሆስፒታሉ ባለሙያዎች ይሁንልኝ።

ከባለ ታሪኩ አንዱ፤



## የፅሁፍ ማጣቀሻዎች፤

1. Cox JL, Schuessler RB, D'Agostino HJ, Stone CM, Chang BC, Cain ME, et al. The surgical treatment of atrial fibrillation. Devel- opment of a definitive surgical proce- dure. III. J Thorac Cardio- vasc Surg. 1991;101:406–26

2. Gibbon JH, Jr. Application of a mechanical heart and lung apparatus
to cardiac surgery. Minn Med 1954; 37: 171–185.

3. Gibbon JH, Jr. Development of the artificial heart and lung extracor- poreal blood circuit. JAMA 1968; 206: 1983–1986.

4.https://www.friendsofchfe.org/ethiopia-team-per- forms-first-surgery

M. Results of open heart surgery in Jehovah's Witness patients. Single centre experience. Kardiochir Torakochirurgia Pol. 2017 Sep;14(3):164-169

13. Müller H, Ratschiller T, Schimetta W, Meier J, Gombotz H, Zierer A. Open Heart Surgery in Jehovah's Witnesses: A Propensity Score Analysis. Ann Thorac Surg. 2020 Feb;109(2):526-533

14. Juraszek A, Dziodzio T, Roedler S, Kral A, Hutschala D, Wolner E, Grimm M, Czerny M. Results of open heart surgery in Jehovah's Witnesses patients. J Cardiovasc Surg (Torino). 2009 Apr;50(2):247-50

15. Bentall H, De Bono A. A technique for complete replacement of the ascending aorta. Thorax. 1968;23:338-339. 10.1136/thx.23.4.338

16. Ludovic Melly, Gianluca Torregrossa, Timothy Lee, Jean-Luc Jansens, John D. Puskas
J Thorac Dis. 2018 Mar; 10(3): 1960-1967



17. Imran Hamid U, Digney R, Soo L, Leung S, Graham AN. Incidence and outcome of re-entry injury in redo cardiac surgery: benefits of preoperative planning. Eur J Cardiothorac Surg. 2015 May;47(5):819-23

18. Denton AC. The first Blalock–Taussig shunt. J Thorac Cardiovasc Surg 2010;140:750-1

19. Dr. Helen Brooke Taussig , Living Legend in Cardiology Clin. Cardiol. 8, 372-374 (1985)

20. Gultekin B, Ozkan S, Uguz E, Atalay H, Akay T, Arslan A, Sezgin A, Ozdemir N, Tasdelen A, Aslamaci S. Valve replacement surgery in patients with end-stage renal disease: long-term results. Artif Organs. 2005 Dec;29(12):972-5.

21. Edwards MB, Taylor KM. A profile of valve replacement surgery in the UK (1986-1997): a study from the UK Heart Valve Registry. J Heart Valve Dis. 1999 Nov;8(6):697-701

CamScanner

22. Will CS. Hypothermia: Its Possible Role in Cardiac Surgery. Ann Thorac Surg 1989;47:788-91

23. ALEXI-MESKISHVILI AND KONSTANTINOV HISTORY OF ATRIAL SEPTAL DEFECT SURGERY. Ann Thorac Surg 2003;76:322–7

2013 ዓ.ም



ስለ መፅሀፉ፡-

ይህ መፅሀፍ የተዋቀረው በአስራሰባት ታሪኮች ቢሆንም ፤ የመጨረሻዎቹ ሶስት ታሪኮች ግን የአንድ አላማ መዳረሻ ቅርንጫፎች ናቸው። ታድያ እነዚህ ታሪኮች ምንም እንኳን በልብወለድ መልክ ቢቀርቡም እውነት ከመሆንም ባሻገር በሀገራችን ልጆች እውቀት የልብ ቀዶ ጥገና እንዴት እንደተደፈረ፤ በመቀጠልም ትልልቅ የሚባሉ የልብ ቀዶ ጥገናዎች እንዴት እንደተጀመረ በትረካ መልክ ያቀርባል።

በመፅሀፉ ፍፃሜ ላይ እነዚሁ ታካሚዎች ያንን አስቸጋሪ ጊዜ አልፈው፤ ዛሬ ላይ ይህንን ጽሁፍ ባነበቡ ወቅት የተሰማቸውን ስሜት አስፍረነዋል። አሁን ያለውም ሆነ መጪው ትውልድ የልብ ቀዶ ጥገና ከውጭ ዜጎች ግባትነት እንዴት ወደ ሀገር በቀል እውቀት እንደተሸጋገረ ቁልጭ አድርጎ ያመላክታል ብዬ አምናለሁ። ከሁሉም ባሻገር በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የሚንጸባረቁ ብዙ ስብዕናዎች ትውልደን ያነቃቃሉ፤ ያነጋግራሉ ብዬ አምናለሁ።

ፈቀደ አግዋር (የልብ ቀዶ ጠጋኝ)

ዋጋው፡
200 ብር 25 (USD)

+251 111 565 352

ብሔረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮጵያ📚
public channel
id: 1215311843

ብሔረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮ
37126 subscribers

Description

በዚህ ቻናል ውስጥ የተ
በPDF መልክ ያገኛሉ::
📖ማንበብ ወደ ሙሉነ
አያደርግም!📖

nned Message #127
ርዕስ፦ ዳግማዊ ሚኒልክ 📝ደራሲ፦ አፈወርቅ ገ

May 23

መፅሐፍትን በ pdf ለመላክና ለማንኛውም ለሃሳብ አስተያት
@bollaye

join us on telegram
@ETHIO_PDF_BOOKS

CamScanner